# ዐምስቱ

የእግዚአብሔርን
ጸጋ በጥልቀት
ለመለማመድ

# የጸጋ አስተምህሮች

ዮሐንስ ፓይፐር

# ዐምስቱ
# የጸጋ አስተምህሮች

ትርጒም --------------------- በሶዶ ባፕቲስት ቤተ ክርስቲያን
አዘጋጆች---------------------1.ያሬድ ሞላ
2.ዮናታን ንጉሤ
አርታዒ ---------------------1.ዳንኤል ክፍሌ
2.ክርስቲያን አዎል
የሽፋን እና ገጽ ቅንብር ----በጸጋአብ ስምኦን

ዐምስቱ የጸጋ አስተምህሮች

ትርጉም በሶዶ ባፕቲስት ቤተ ክርስቲያን © 2015

የአሳታሚዉ መብት በሕግ የተጠበቀ ነዉ።

ያለ ደራሲዉ ፈቃድ ይህን መጽሐፍ በማናቸዉም መንገድ ማባዛት ወይም ማተም በሕግ የተከለከለ ነዉ። ከመጽሐፉ ዐሳብ በተወሰደ ጊዜ ሁሉ፣ ወይም የመጽሐፉ ዐሳብ በቀጥታ ሲጠቀስ፣ አግባብነት ባለዉ መንገድ ሥነ ጽሑፋዊ የምንጭ አጠቃቀስን ተከትሎ መሆን አለበት።

በልዩ ሁኔታ ካልተጠቀሰ በስተቀር፣ ሁሉም ዘመኖች የተጠቀሱት እንደ አውሮፓውያኑ አቈጣጠር (እ.አ.አ) ነው።

ሁሉም የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች የተወሰዱት ከዐዲሱ መደበኛ ትርጉም ነው።

ከድሮው (ከነባሩ) ትርጉም የተወሰዱ ጥቅሶች "ቀ.ኃ.ሥ" የሚል መግለጫ ተጨምሮባቸዋል።

ለበለጠ መረጃ ወይንም ለተርጓሚዉ አስተያየት፣ ጥያቄ ወይም ሐሳብ ቢኖርዎ ከታች የተጠቀሱትን አድራሻዎች ይጠቀሙ።

የሽፋን እና ገጽ ቅንብር በጸጋአብ ስምኦን

Soddo Baptist church

@gbaptist

@soddobaptistchurch

# ማውጫ


መቅድም ........................................................................................ 1

ታሪካዊ ዳራ ...................................................................................... 7

አጠቃላይ ውድቀት ........................................................................... 15

የማይቋቋሙት ጸጋ............................................................................ 22

ውሱን ቤዝዎት ................................................................................ 36

ሁኔታ አልባ ምርጫ.......................................................................... 53

የቅዱሳን ጽናት................................................................................ 62

የግል ምስክርነት ............................................................................ 77

የማጠቃለያ ምስክርነት...................................................................... 88

መውጫ........................................................................................... 97

# መቅድም

ክርስቲያኖች እግዚአብሔርን እንወደዋለን። እርሱ ትልቁ ሀብታችን ነው፤ ደግሞም እርሱን ምንም አይስተካከለውም። ከቄዩ የእምነት መግለጫች አንዱ እንደሚለው፣ "እግዚአብሔር፤ በማንነቱ፣ በጥበቡ፣ በኀይሉ፣ በቅድስናው፣ በፍትሑ፣ በመልካምነቱ እና በእውነትነቱ መንፈስ ነው፤ ደግሞም ኢውሱን፣ ዘለላለማዊ እና የማይለወጥ ነው።" [1] እኛም የምንወደው ይህን እግዚአብሔር ነው። የምንወድለትም የፍጹምነቱን ሙሉ ገጽታ ነው። እርሱን ማወቅና በእርሱ መወደድ፣ ደግሞም እርሱን ወደ መምሰል ማደግ የነፍሳችን ፍለጋ ግብ ነው። እርሱ "ፍጹም ደስታችን ነው" (መዝ. 43፥4)።

እግዚአብሔር ኢውሱን ነው—ይህም ለሙሉነት ያለንን መሻት ይመልስልናል።

እርሱ ዘላለማዊ ነው—ይህም ዘላቂ ለመሆን ያለንን መሻት ይመልስልናል። እርሱ አይለወጤ ነው—ይህም ደግሞ ለመረጋጋት እና ለደኅንነት ያለንን መሻት ይመልስልናል። እንደ እግዚአብሔር ያለ ማንም የለም። ምንም ነገር ከእርሱ ጋር ሊስተካከል አይችልም። ሀብት፣ ወሲብ፣ ኀይል፣ ታዋቂነት፣ ገዢነት፣ ውጤታማነት፣ ክንውን —ምንም ነገር ከእግዚአብሔር ጋር ሊስተካከል አይችልም።

## ጭጋጉ ሲጠራ

እግዚአብሔርን ይበልጥ ባወቃችሁት መጠን፣ ይበልጥ ልታውቁት ትፈልጋላችሁ። በእርሱ የኅብረት ግብዣ ይበልጥ በተቀመጣችሁ መጠን፣ ጥልቅ ለሆነው እና ለበዛው ኅብረት የምትራቡ ትሆናላችሁ። ጥልቅ የሆነ እርካታ እግዚአብሔርን እንድንወደው፣ የእግዚአብሔርን ኀይል ለምናገኝበት ጊዜ ቅዱስ መሻት ይጨምርልናል። ይህም ኢየሱስ ስለ እኛ ወደ አባቱ የጸለየበት መንገድ ነው።

---

[1] ዐጭሩ የዌስት ሚንስተር እምነት መግለጫ ጥያቄ አራት

“ለእኔ ያለህ ፍቅር በእነርሱ እንዲሆን” (ዮሐንስ 17፥26)። መሻታችን ይህ ነው፤ አብ ለልጁ ያለውን ፍቅር በእኛ እንዲሞላ፣ ደግሞም በአብ ፍቅር ልኬትና ንጽሕና ወልድን መውደድ እንዲያስችለን ነው። ስለዚህም ስለ ጐዶሎ ፍቅራችን ያለን መብረክረክ ያከትማል።

እርሱን ይበልጥ ስታውቁት እና ስትወዱት ደግሞም ስታምኑት፣ አዎን ይበልጡን እርሱን ለማወቅ ትሻላችሁ። ይህችን ትንሽ መጽሐፍ የጻፍኩበት ምክንያት ይህ ነው። እግዚአብሔርን ለማወቅና በእርሱም ለመደሰት እናፍቃለሁ፤ ለእናንተም ይህንን እመኝላችኋለሁ። ትልቁ የቈየው የእምነት መግለጫ፣ “የሰው የመጨረሻ ግብ ምንድነው?” በማለት ጠይቆ፣ “የሰው የመጨረሻው ግብ እግዚአብሔርን ማክበርና በእርሱም ለዘላለም መደሰት ነው።”[2] በማለት ይመልሳል። በእግዚአብሔር መደሰት እርሱን የማክበርያ መንገድ ነው። ምክንያቱም እግዚአብሔር በእኛ ይበልጥ የሚከብረው፣ እኛ ይበልጥ በእርሱ በምንረካ ጊዜ ነው።

ነገር ግን በእርሱ ለመደሰት የግድ እርሱን ማወቅ አለብን። ማየት ማጣጣም ነው። እግዚአብሔር ድብዝዝ ያለ እና ጭጋግ የሸፈነው ሆኖ ቢቈይ፣ ለዘመናት ይመሰጠርብን ነበር፤ ነገር ግን ልክ ጭጋጉ ሲጠራ፣ ራሳችንን በትልቅ ገደል አፋፍ ብናገኝ እንደምንርበተበተው በደስታ አንርበተበትም።

## ረብ ያለው ትግል

ስለ እግዚአብሔር ከመጽሐፍ ቅዱስ የሆነ የጠራ ዕውቀት፣ ለእግዚአብሔር ያለንን የፍቅር እሳት የሚያስቀጥል ችቦ እንደሆነ ይህ የግል ተመክሮዬ ነው። እግዚአብሔር በድነት ሥራው ምን ይመስላል የሚለው ዕውቀት፣ ምናልባትም እጅግ ወሳኙ ዕውቀት ነው እላለሁ። የካልቪኒዝም ዐምስቱ ነጥቦችም የሚያወሱት ይህንን ነው። የእግዚአብሔርን ኀይልና ሉዓላዊነት በጥቅሉ አይደለም፤ ነገር ግን እርሱ ሰዎችን የሚያድንበትን ኀይሉን እና ሉዓላዊነቱን ነው። በዚሁ ምክንያት ነው እነዚህ ነጥቦች፣ “የጸጋ አስተምህሮች” በመባል የሚጠሩት።

---

[2] ዐጭሩ የዌስት ሚንስተር እምነት መግለጫ ጥያቄ አንድ

እግዚአብሔርን በሙላት ለመለማመድ ማወቅ ያለብን፣ እግዚአብሔር በአጠቃላይ እንዴት እንደሚሠራ ሳይሆን፣ በተለየ ሁኔታ እኛን እንዴት እንዳዳነን ነው— እኔን እንዴት ነው ያዳነኝ?

እንደ ካልቪኒስትና ደርዙን እንደሚመከት ሰው አልጀምርም፤ ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስን ከማንኛውም የአስተሳሰብ ደርዝ በላይ ለማስቀመጥ እንደሚፈልግ፣ የመጽሐፍ ቅዱስ አማኝ ክርስቲያን እጀምራለሁ። ሆኖም ግን ባለፉት ዓመታት፣ በብዙ የትግል ዓመታት፣ በዐምስቱ ነጥቦች ላይ ካልቪናዊ አስተምህሮች መጽሐፍ ቅዱሳዊ እንደሆኑ፣ በዚህም ምክንያት እውነት ደግሞም የእግዚአብሔርን ጸጋ በጥልቀት ወደ መለማመድ የምንገባባቸው ውድ መሸጋገሪያ መሆናቸውን በጽኑ በማመን ጠልቄበታለሁ።

የነበረኝ የግል ትግል፣ በዚህ መንገድ ላይ ያሉ ሌሎችን በእጅጉ እንድታገስ አድርጎኛል። በአንድ በኩል፣ ሁላችንም በዚህ ጕዳና ላይ ነን። ምንም ያህል ነገሮችን እንደ ቅዱስ ቃሉ ደግሞም በትክክል ብናውቅ፣ እስከንሞትላቸው ድረስ ነገሮች ግልጽ እና ውድ ቢሆኑልን እንኳ፣ አሁንም በመስተዋት በድንግዝግዝ የምናይ ነን (1 ቆሮንቶስ 13፥12)። እንደ እሳት በሚፈትነው በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ዐሳባችንን ለማሳለፍ ስንፈልግ፣ የሚወርዱ ብዙ እንባ ሊኖሩ ይችላሉ።

ሆኖም ግን መጽሐፍ ቅዱስ ስለ እግዚአብሔር የሚያስተምረውን ለመረዳት የምናደርገው ሁሉም ትግል እጅግን ረብ ያለው ነው። አሸዋ በሆነ ዓለም፣ እግዚአብሔር ጠንካራ ዐለት ነው። እግዚአብሔርን በሉዓላዊነቱ ማወቅ፣ በመከራ ነፋስ እና ውዥንብር ውስጥ እንደ በሉጥ ዛፍ መሆን ነው። ደግሞም ከጥንካሬ ጋር፣ ከሚታሰበው በላይ ጣፋጭነት እና ተወዳጅነት ነው። ሉዓላዊው የይሁዳ አንበሳ፣ ጨዋው የእግዚአብሔር በግ ነው።

## ጸሎቴ ለእናንተ

ተጠቃሚ እንድትሆኑ እጸልያለሁ። እነዚህን አጫጭር ምዕራፎች በሆነ ቅደም ተከተል ማንበብ እንዳለባችሁ አታስቡ። አብዛኞቻችሁ ታሪካዊ ዳራውን ለመዝለል ትፈልጋላችሁ፤ ምክንያቱም ከመጽሐፍ ቅዱሳዊ ጥያቄዎች ጋር ወዲያው የሚገናኝ ስላልሆነ ነው።

ለዚህ መጽሐፍ የታሰበለት የራሱ ቅደም ተከተል አለው፤ ቢሆንም ግን በጣም አንገብጋቢ መስሎ ከታያችሁ ከየትኛውም ስፍራ ለመጀመር ነጻ ሁኑ። በዚህ ከተጠቀማችሁ በመቀጠል ወደ ተቀሩት ትመለሳላችሁ። ያልተጠቀማችሁ እንደሆነ፣ ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ተመለሱና በሙሉ ኀይላችሁ አንብቡት። ለማንኛውም እንደምትደርሱ ተስፋ የማደርገው ቦታ ይህ ነው፡- የእኔን ሳይሆን የእግዚአብሔርን ቃል እንድታነቡ፣ እንድትረዱ፣ እንድትወዱት፣ እንድትደሰቱበት እና እንድትታዘዙት ነው። እዚህ በመገናኘታችን ምክንያት፣ “የእግዚአብሔርን ጸጋ በጥልቀት ወደ መለማመድ” እንድታልፉ እጸልይላችኋለሁ።

መጋቢ ዮሐንስ ፓይፐር (2013)

# መቅድም ለዐማርኛው ቅጂ

ነገረ ድኅነት፣ “መሠረታዊ” ከሚባሉ የቤተ ክርስቲያን አስተምህሮች ተጠቃሹ ነው። የወንጌሉ መልእክት ማዕከልም ድኅነት እንደመሆኑ፣ በቀላሉ ሊታይ ፈጽሞ የተገባ አይደለም። የእግዚአብሔር የቤዝዎት ታሪክ መረዳታችንም በዚሁ መረዳት ላይ ስለሚመሠረት፣ በብዙ ጥንቃቄ ሊያዝ የሚገባው ነው።

የእግዚአብሔር ቃል የሆነው መጽሐፍ ቅዱስ፣ በተለያዩ ጉዳዮች ላይ፣ በተለያዩ ዐውዶችና መጻሕፍት የሚያስተምረንን በማጠናከር አስተምህሮ ማደራጀት ከመጀመሪያው የሐዋርያት መግለጫ (ሐዋ. ሥራ 15) ጀምሮ፣ ቤተ ክርስቲያን የምትከተለው አካሄድ ነው። የመጽሐፍ ቅዱስን ዐሳብ ወጥነት ባለው መልኩ ለመረዳት፣ እምነታችንን ለሌሎች በቀላሉ ለመግለጥ፣ ተቃውሞ በገጠመም ጊዜ ምላሽ ለመስጠት፣ ደርዝ ባለው መልኩ ማጥናት ብዙ ትርፍ የሚገኝበት ነው። የምንደርስበትም ድምዳሜ ትክክለኛውን የሥነ አፈታት ዘዴ በመጠቀም፣ ዐሳባችንን ወደ ቃሉ ሳይሆን፣ ቃሉን የዐሳባችን መሪ ለማድረግ ትሑት በሆነ ልብ በማጥናት ሊሆን የተገባ መሆኑ እሙን ነው። በዚህ ረገድ፣ "የእውነትን ቃል በትክክል እንደሚያስረዳ የተመሠከረለት ሠራተኛ"(2 ጢሞቴዎስ 2፥15) በመሆን፣ በመላው ዓለም ላለፉት ጥቂት ዐሥርታት በአገልግሎቱ በቅዱሳን ዘንድ ከበሬታና ፍቅርን ያተረፈውን መጋቢ ጥንቁቅ ሥራ ልብ የሚያሳርፍ ሆኖ እናገኘዋለን።

በዘመናት ተፈትኖ ነጥሮ የወጣውን ነገረ ድኅነት ለመያዝ፣ ከዚህም በሚነሣ ፍጹም መሰጠት ጌታን ለማገልገል እና ወንጌልን በፍል-አምሮት እንድንሰብክ፣ ጊዜ እና ልባችንን በመስጠት ልናጠናው ይገባል።

በዚህ ርእሰ ጉዳይ በአገራችን ቋንቋ የተጻፉ መጻሕፍት ውስን መሆን፣ ለጥናታችን ዐጋዥ ፍለጋ እንድንባዝን ዳርጎናል ብንል አልተሳሳትንም። እናም በዚህ ወሳኝ ጉዳይ ላይ የራሳችንን ድርሻ ለመወጣት ስንል ይህን ወደ ቋንቋችን መልሰነዋል።

ከተከፈተ መጽሐፍ ቅዱሳችሁ ጋር እና በተሰጠ ልባችሁ በማጥናት፣ በዚህ ከወርቅ በሚጠራ፣ ከማርም በሚጣፍጥ እውነት እንደምትባረኩ ተስፋ በማድረግ ዐቀረብንላችሁ።

ውድ አንባቢ ሆይ፤ በዚህ ሥራ ውስጥ ድክመት ቢያገኙበት ታግሠው፣ ቢባረኩበት ደግሞ ክብርን ለክብር ጌታ እየሰጡ፣ ትጉህ የቃሉ ተማሪ ሊያደርገው እንደሚገባ፣ "ነገሩ እንደዚህ ይሆንን?" እያሉ መጻሕፍትን በየዕለቱ በመመርመር፣ ቃሉን በታላቅ ጉጉት እንዲቀበሉት እናበረታታለን። (ሐዋርያት ሥራ 17፥11)

በመጨረሻም ወደ ክብሩ በጸጋው ጠርቶን፣ ለመንግሥቱ ረብ ያለው ሥራ ላይ ሱታፌ እንዲኖረን ችሎታንና ትጋትን የሰጠንን፣ አነሳስቶ ስላስጀመረን፣ አስጀምሮም ስላስፈጸመን ምስጋናና ክብር ይሁን እንላለን።

ከቤተ ክርስቲያኒቱ መጋቢ (2016 ዓ.ም)

# ታሪካዊ ዳራ

እውቁ የሥነ መለኮት ሰው እና የጄኔቫ ቤተ ክርስቲያን መጋቢ የነበረው ጆን ካልቪን የሞተው በ1564 ነው። እርሱ በጀርመን ከነበረው ማሪቲን ሉተር ጋር፣ የፕሮቴስታንት ተሐድሶ ቊልፍ የተጽእኖ ዐቅም ነበረ። የመጽሐፍ ቅዱስ ማብራሪያዎቹ እና "Institutes of the Christian Religion" የተሰኘው መጽሐፉ፣ በዓለም ዙሪያ ባሉ አብያተ ክርስቲያናት እስከ ዛሬም ድረስ ከፍተኛ ተጽእኖ እያሳደሩ ነው።

የካልቪንን አስተምህሮች የወረሱ አብያተ ክርስቲያናት፣ የተሐድሶ ቅርንጫፎች ከሆኑት ሉተራን እና አንግሊካን/ኤጲስ ቆጶሳዊያን በሌላ ፈርጅ በመሆን፣ በተለምዶው ተሐድሶአውያን (Reformed) በመባል ይጠራሉ። ሁሉም መጥምቃዊያን (Baptist) የሆኑ አብያተ ክርስቲያናት ተሐድሶአዊ ነገረ መለኮትን የያዙ ባይሆንም፣ ጅረቱ ከዛው የሆነ እና ከተሐድሶው ተሐድሶአዊ ቅርንጫፍ የተወረሰውን ዋነኛውን አስተምህሮ በመጠበቅ የያዘ ትልቅ የመጥምቃዊያን ወግ አለ።

## አሪሚኒየስ እና ሪምንስትራንቶች[3]

በአርሚኒያኒዝም እና በካልቪኒዝም መካከል ያለው ሰጣገባ የተጀመረው፣ በሆላንድ አገር በ17ተኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ነበር። የአርሚንያን ቡድን መሥራች፣ ያዕቆብ አርሚኒየስ የተባለ ግለሰብ ሲሆን፣ የኖረውም ከ1560-1609 ነበር። እርሱም የካልቪን ተተኪ በነበረው በቴዎዶር ቤዛ እግር ሥር፣ በጄኔቫ ትምህርቱን ተከታትሎ፣ በኋላም በ1603 በበሌይደን ዩኒቨርስቲ የሥነ መለኮት ፕሮፌሰር ለመሆን በቃ።

[3]Remonstrants - *ዐምስቱን የአርሚኒያዚም አናቅጽ ያረቀቁ ሰዎች ናቸው።*

አርሚኒየስ በሂደት አንዳንድ ካልቪናዊ አስተምህሮችን ወደመተው መጣ። ውጥረቱ ተሐድሶአዊ አብያተ ክርስቲያናት በቊጥር በርካታ በሆኑባት በመላዋ ሆላንድ ተሠራጨ። አርሚኒያኖችም የራሳቸውን የእምነት አቋም በዐምስት አናቅጽ አረቀቁ፤ በመቀጠልም በ1610፣ Remonstrance (ማስረጃ) በሚል ስያሜ በአርባ ስድስት አገልጋዮች ፊርማ፣ ዐምስቱን አናቅጽ በመንግሥት ባለ ሥልጣኖች ፊት አስቀመጡ።

ዐምስቱን አናቅጽ ለመመርመር፣ ከኅዳር 13/1618 እስከ ግንቦት 9/1619 በተካሄደው የዶርት ስብሰባ ጉባኤ ይፋዊ የሆነ ካልቪናዊ ምላሽ ተሰጠ። ሰማንያ አራት አባላት እና ዐሥራ ስምንት የመንግሥት ተወካዮች ነበሩበት። ጉባኤውም የዶርት ቀኖና በመባል የሚታወቀውን አረቀቀ። የአሜሪካ ተሐድሶአዊ አብያተ ክርስቲያናት እና የክርስቲያን ተሐድሶአዊ አብያተ ክርስቲያናት ዛሬም ድረስ የእምነት አቋማቸው አንዱ ክፍል ነው። እነርሱም ለዐምስቱ የአርሚኒያን ሪሞንስትራንት አናቅጽ ምላሽ ይሆኑ ዘንድ የረቀቁትን ዐምስቱን የካልቪኒዚም ነጥቦች ይይዛሉ።

ስለዚህም ዐምስቱ ነጥቦች በመባል የሚጠሩት፣ ለአስተምህሮአቸው ማጠቃለያነት በካልቪኒስቶች የተመረጡ አይደሉም፤ ላለመስማማት ብለው ዐምስቱን ነጥቦች ለመረጡት አርሚኒያኖች ምላሽ እንዲሆኑ የቀረቡ ናቸው።

## በመጽሐፍ ቅዱሳዊ ሥነ መለኮት ልብ ላይ

መጀመርያ የነበረውን ክርክር ምንነት ከማወቅ ይልቅ፣ ለዐምስቱ ነጥቦች አውንታዊ የሆነ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ስፍራ መስጠቱ የተሻለ ነው። ዛሬም ቢሆን፣ እነዚህ ዐምስቱ ነጥቦች ለመጽሐፍ ቅዱሳዊ ሥነ መለኮት ልብ ላይ ያሉ ናቸው። አላስፈላጊም አይደሉም። እነዚህን ነጥቦች በተመለከተ ያለን አቋም ስለ እግዚአብሔር፣ ስለ ሰው፣ ስለ ድነት፣ ስለ ቤዝዎት፣ ስለ ዳግም ልደት፣ ስለ ድነት ዋስትና፣ ስለ አምልኮ እና ስለ ወንጌል ተልእኮ ያለንን እይታ በእጅጉ ይወስነዋል።

የሆነ ጊዜ ላይ (መቼ እና እንዴት እንደሆነ፣ ማንም በርግጠኝነት ባያውቅም) ፣ እነዚህ ዐምስቱ ነጥቦች በእንግሊዝኛው ኀጺሮተ ቃል ‘TULIP’ በመባል ወደ መጠራት መጡ።

T – Total Depravity — አጠቃላይ ውድቀት

U – Unconditional Election — ሁኔታ አልባ ምርጫ

L – Limited Atonement — ውሱን ቤዝዎት

I – Irresistible Grace — የማይቋቋሙት ጸጋ

P – Perseverance of Saints — የቅዱሳን ጽናት

እነዚህ ዐምስቱ ነጥቦች፣ የተሐድሶአዊ ነገረ መለኮትን ጥልቀት በሙላት ያትታሉ ብዬ አላምንም። ብዙ ጸሐፊያን፣ በተለይም ደግሞ የፕሪስቢቴሪያን ዝንባሌ ያላቸው ይህን ዐሳብ ይጋሩታል፤ ምክንያቱም ብዙ ሰዎች (ልክ እንደ እኔ ባፕቲስት የሆኑ) ተሐድሶአዊውን ወግ በሙላት ባይቀበሉም ካልቪኒስቶች ይባላሉና። ለምሳሌ ሪቻርድ ሙለር፣ "Calvin and the Reformed Tradition[4]" በተሰኘው መጽሐፉ እና ኬኔት ጄ. ስትዎርት፣ "Ten Myths About Calvinism[5]" በሚለው መጽሐፉ፣ ካልቪን እና ከትጋቱ የፈሰሱት የደርዝ ወንዞች፣ እኔ እዚህ ከማተኩርባቸው ዐምስት ጅረቶች ይልቅ የሰፉ እና የጠለቁ ደግሞም ብዙ ገጽታ ያላቸው መሆኑን ግልጽ ያደርጉታል። እነዚህ ዐምስቱ ነጥቦች፣ እግዚአብሔር ኀጢአተኞችን በሚያድንበት ማዕከላዊ ሥራ ላይ ያተኮሩ ናቸው። ለዐምስቱ የጸጋ አስተምህሮች የተሰጡት ርእሶችም እጅግ ምርጦቹ ናቸው አልልም። እንደ ማንኛውም ዐጠር ያለ የአስተምህሮ ሐተታ፣ እነዚህም ለተሳሳተ መረዳት የተጋለጡ ናቸው። ጀስቲን ቴይለር፣ እነዚህን እውነቶች በድጋሚ ለመናገር የተደረጉ የተለያዩ ሙከራዎችን ጠቃሚ ማጠቃለያ ይሰጣል።

---

[4] Richard Muller, Calvin and the Reformed Tradition (Grand Rapids: Baker Books, 2012), pp. 51-69.

[5] Kenneth J. Stewart, Ten Myths About Calvinism (Downers Grove, Illinois: InterVarsity Press, 2011), pp. 75-96.

ለምሳሌ፡- ቲምቲ ጆርጅ ከ “TULIP” ይልቅ “ROSES” ን ይመርጣል፤ Radical Depravity (ጥልቅ ውድቀት)፣ Overcoming Grace (አሸናፊ ጸጋ)፣ Sovereign Election (ሉዓላዊ ምርጫ)፣ Eternal life (ዘላለማዊ ሕይወት) እና Singular redemption (ነጠላ ቤዛዎት)። ሮጀር ኒኮል “GOSPEL” የሚለውን ኀጺሮተ ቃል ይመርጣል (ይህም ነጥቦቹን ስድስት ያደርጋል)፤ Grace (ጸጋ)፣ Obligatory grace (አስገዳጅ ጸጋ)፣ Sovereign Grace (ሉዓላዊ ጸጋ)፣ Provision–making Grace (ዐቅርቦታዊ ጸጋ)፣ Effectual Grace (ውጤታማ ጸጋ) እና Lasting Grace (ዘላቂ ጸጋ)።

ሌሎች ደግሞ ኀጺሮተ ቃላዊ ስያሜ የመስጠትን ጥረት በሙሉ ይተዉታል። ለምሳሌ ጀምስ ሞንትጎሜሪ ቦይስ፣ Radical Depravity (መሠረታዊ ውድቀት)፣ Unconditional Election (ሁኔታ አልባ ምርጫ)፣ Efficacious Grace (ውጤታማ ጸጋ) እና persevering Grace (የሚያጸና ጸጋን) ያቀርባል። ግሬግ ፎርስተር ደግሞ የሚከተለውን ያቀርባል፡-

- ከድነት በፊት የሰው ሁኔታ፣ በአጠቃላይ የተበከለ
- የአብ ሥራ በድነት ውስጥ፣ ሁኔታ አልባ ምርጫ
- የወልድ ሥራ በድነት ውስጥ፣ ግለሰባዊ ድነት
- የመንፈስ ቅዱስ ሥራ በድነት ውስጥ፣ ልዕለ ተፈጥሯዊ ለውጥ
- ከድነት በኋላ የሰው ሁኔታ፣ በእምነት መጽናት

አስተምህሮቹ ምን ማለት እንደሆኑ በምናስተምርበት ጊዜም ቢሆን፣ ይህ አሁን ያለው ቅደም ተከተል (T U L I P) የግድ በጣም ጠቃሚ ነው አልልም። በርግጥ ለዚህ ተለምዶአዊ ቅደም ተከተል ጥሩ የሆነ ምክንያታዊ መሠረት አለው። ድነት በሚያስፈልገው ሰው ይጀምራል (አጠቃላይ ውድቀት)፤ በመቀጠልም እግዚአብሔር የራሱን ሕዝብ ለማዳን የወሰዳቸውን እርምጃዎች፣ በክስተታቸው ቅደም ተከተል ይሰጣል።

ይመርጣል (ሁኔታ አልባ ምርጫ)፤ ከዚያም የምርጦቹን ኀጢአት ያስተሰርይ ዘንድ ኢየሱስን ላከው (ውሱን ቤዝዎት)፤ ከዚያም ደግሞ ሕዝቡን በማይቋቋሙት ሁኔታ ወደ እምነት ሳባቸው (አይቋቋሜ ጸጋ)፤ እናም በስተመጨረሻ እነዚያ እስከ መጨረሻው እንዲጸኑ ሊያደርጋቸው ይሠራል (የቅዱሳን ጽናት)።

እኛ ወደ ክርስትና በመጣንበት ተመክሮአዊ ቅደም ተከተል ብንሄድ፣ ሰዎች እነዚህን ነጥቦች በቀላሉ እንደሚቀበሉ ተገንዝቤአለሁ።

1. በመጀመርያ ውድቀታችንን እና ድነት እንደሚያስፈልገን ተገነዘብን።
2. በመቀጠል የማይቋቋሙት የእግዚአብሔር ጸጋ ወደ እምነት ሲመራን አገኘነው።
3. በመቀጠል ለኀጢአታችን የሆነውን የክርስቶስን ቤዝዎታዊ ሞት ብቁነትን አመንነው።
4. ደግሞም ኀጢአታችንን ለማስተሰረይ እና እኛን ወደ እምነት ለማምጣት ከሠራው የእግዚአብሔር ሥራ በስተጀርባ፣ የእግዚአብሔር ሁኔታ አልባ ምርጫ እንዳለ ግልጽ ሆነልን።
5. በስተመጨረሻም በእምነት እስከ ፍጻሜ እንድንጸና ብርታትን እና ፈቃደኝነትን እንዲሰጠን በመረጠው ጸጋ ላይ ዐረፍን።

ይህም በሚቀጥሉት ገጾች የምንከተለው ቅደም ተከተል ነው። ዐምስቱን ነጥቦች በተመለከተ ቅዱሳት መጻሕፍት ምን እንደሚያስተምሩ የማምነውን ግልጽ ለማድረግ እሞክራለሁ። ትልቁ መሻቴ የእግዚአብሔርን ጸጋ በመለማመድ እንድትጠልቁ እና በቅዱስ ቃሉ የተገለጠውን የእርሱን እውነት በመረዳት እና በማመን እርሱን እንድታከብሩት ነው። እኔም የቅዱስ ቃሉን እውነት የሚጣረሰውን የትኛውንም ዐሳቤን ለመቀየር ክፍት እንድሆን እጸልያለሁ። ለጆን ካልቪን የተሰጠ ምንም ዐይነት ፍላጎት የለኝም፤ ደግሞም እርሱ ያስተማራቸው አንዳንድ ነገሮች ስሕተት ሆነው አግኝቻለሁ።

ሆኖም ግን በጥቅሉ በእነዚህ በዐምስቱ ነጥቦች፣ ካልቪኒስት ተብዬ መጠራትን እመርጣለሁ፤ ምክንያቱም ይህ ስም ከእነዚህ ዐምስት ነጥቦች ጋር ለክፍለ ዘመናት ተያይዟል፤ ደግሞም ይህ ካልቪናዊ አቋም ለመጽሐፍ ቅዱስ ታማኝ ሆኖ አግኝቼዋለሁ። መጽሐፍ ቅዱስ የመጨረሻው ባለ ሥልጣናችን ነው።

ጆናታን ኤድዋርድስ፣ “The freedom of the Will (የፈቃድ ነጻነት)” በተሰኘው ትልቅ መጽሐፉ መቅድም ላይ ያለውን አስተያየት እኔም እጋራለሁ፤ “ምንም እንኳ በካልቪን ላይ ጥገኛ መሆንን፣ ወይም ደግሞ የያዝኳቸውን አስተምህሮች እርሱ ስላመነና ስላስተማረ ማመንን በፍጹም ባልቀበልም፣ ለልዩነት ሲባል ካልቪኒስት ተብሎ መጠራትን እንደ ስሕተት ልወስደው አይገባኝም። ደግሞም ሁሉንም ነገር እርሱ እንዳስተማረው የመቀበል ግዴታ ውስጥ ልሆን አልችልም።”[6]

ወደ ጠለቀው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማብራሪያ ከመሄዳችን በፊት፣ የዐምስቱን ነጥቦች ፍቺ በዐጭሩ ጠቅለል ማድረግ ለአንዳንድ አንባቢያን የሚጠቅም ይሆናል። ይህ ቅምሻ፣ ምናልባትም እኔ እነዚህን እውነቶች ማመኔ እንዴት የእግዚአብሔርን ውድ ጸጋ ያጐላዋል የሚልን ስሜት ይቀሰቅሰው ይሆናል፤ ደግሞም ራሳቸውን የማዳን ተስፋን ፈጽሞ ለቈረጡ ኀጢአተኞች፣ የማይነገርን ደስታ ይሰጣቸዋል።

## አጠቃላይ ውድቀት

ኀጢአታዊ ብክለታችን፣ የኀጢአት ባሮች እስኪያደርገን እና ዐመፀኝነታችንን እና ዕውርነታችንን መርታት የተሳነን እስክንሆን ድረስ፣ የጠለቀና የበረታ ነው። ይህ ራሳችንን ከራሳችን ማዳን አለመቻላችን አጠቃላይ ነው። ዐመፀኝነታችንን ይረታው ዘንድ፣ እንድናይ ዐይን ይሰጠን ዘንድ፣ እና ወደ አዳኛችን በውጤታማነት እንዲስበን ሙሉ በሙሉ በእግዚአብሔር ጸጋ ላይ ጥገኞች ነን።

[6] The Freedom of the Will (1754), ed. Paul Ramsey (New Haven, Conn. Yale University Press, 1957), p. 131.

## ሁኔታ አልባ ምርጫ

የእግዚአብሔር ምርጫ፣ ዓለም ከመፈጠሩ አስቀድሞ በልጁ በኢየሱስ በኩል የተሰጠ፣ በሁኔታ ያልተደገፈ፣ የነጻ ችሮታው ድርጊት ነው። በዚህ ድርጊቱ ዓለም ከመመሥረቱ አስቀድሞ እግዚአብሔር ከኀጢአት ባርነት የሚፈቱትን፣ ደግሞም ወደ ንስሓ እና በኢየሱስ ወደሚያድን እምነት የሚመጡትን ለራሱ መርጧል።

## ውሱን ቤዝዎት

የክርስቶስ ቤዛነት ለሁሉም ሰው የሚበቃ እና ለሚያምኑበት ውጤታማ የሆነ ነው። የሚያምኑትን ሁሉ ለማዳን፣ በዋጋው ወይም በብቁነቱ ውሱን አይደለም፤ ነገር ግን ኢየሱስ የፈጸመው ቤዛነት እና ማዳኑ በሙላት ውጤታማ የሚሆነው፣ የማዳን ሥራው ለተዘጋጀላቸው ሰዎች በመሆኑ ረገድ ውስን ነው። የቤዝዎቱ ሙሉ ብቃት የሚገኘው ለሁሉም ሰዎች ነው። ማንም ፈቃደኛ ቢሆን፣ ማንም ደግሞ ቢያምን፣ በክርስቶስ ደም ይሸፈናል። እንዲሁም ለተመረጠችው የክርስቶስ ሙሽሪት፣ የዐዲስ ኪዳን ተስፋዎችን በክርስቶስ ሞት ለመፈጸም መለኮታዊ የሆነ ዕቅድ አለ። ስለዚህም ክርስቶስ ለሁሉም ሰው ሞቷል፤ ነገር ግን ለሁሉም በተመሳሳይ መንገድ አይደለም።

## የማይቋቋሙት ጸጋ

ይህ ማለት የሰው ልጅ ሁሉ ዘወትር በእግዚአብሔር ላይ የሚያደርገው መቋቋም (ሮሜ 3፥10-12፤ ሐዋ 7፥51)፣ ለማዳን እርሱ በነጻ ከመረጣቸው፣ ማለትም ካልተገባቸው ዐመፀኞች ላይ፣ በሚያድነው የእግዚአብሔር ጸጋ፣ በግሩም ሁኔታ፣ በትክክለኛው ጊዜ ይሸነፋል ማለት ነው።

## የቅዱሳን ጽናት

ጽድቅን ያገኙ ሁሉ፣ የእምነትን ገድል በድል እንደሚያጠናቅቁ እናምናለን። በእምነት ይጸናሉ፤ ደግሞም በስተመጨረሻ በፍጹም ለነፍሳቸው ጠላት አይማረኩም። ይህም ጽናት በክርስቶስ ኢየሱስ ደም የተገኘ፣ እንድንከስም ሳይሆን ንቃታችንን ያበረታ እና ያበረታታ ዘንድ፣ በራሱ በእግዚአብሔር በውስጣችን የተሠራ የዐዲሱ ኪዳን ተስፋ ነው። በፍጻሜውም፣ “መልካሙን ገድል ተጋድዬአለሁ፤ ዳሩ ግን ከእኔ ጋር ያለው የእግዚአብሔር ጸጋ ነው እንጂ እኔ አይደለሁም” (2ኛ ጢሞ. 4፥7፤ 1 ቆሮ. 15፥10) እንላለን።

አሁን ለዐምስቱም ነጥቦች፣ ለእያንዳንዳቸው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማብራሪያ እና ማረጋገጫ ወደ መስጠት እንሻገራለን። እኔ ትክክል መሆኔ እንዲረጋገጥ አልጸልይም፤ ነገር ግን የእግዚአብሔር ቃል በእውነት እንዲብራራ እና በቃሉ ውስጥ ያለውን አእምሯችን ይቀበለው ዘንድ እንዲለሰልስ ነው።

# አጠቃላይ ውድቀት

ስለ ሰው ውድቀት ስንናገር፣ ሰውን ለመግታት ወይም ለመለወጥ በእግዚአብሔር ከተተገበረው ከየትኛውም ጸጋ ውጪ ያለን የሰውን ተፈጥሯዊ ሁኔታ ማለታችን ነው።

የውድቀቱም አጠቃላይነት ሰው ማድረግ የሚቻለውን ክፋት ሁሉ ያደርገዋል ማለት እንዳይደለ ግልጽ ነው። በርግጥ ሰው በባልንጀራው ላይ አሁን ከሚያደርገው በላይ ክፉ ድርጊቶችን መፈጸም እንደሚችል ጥርጥር የለውም፤ ነገር ግን ለእግዚአብሔር ፈቃድ በደስታ ከመገዛት ባልሆነ መነሻ (ሞቲቭ) ምክንያት እጅግ የከፉ ድርጊቶችን ከማድረግ ቢገደብ፣ መልካም ምግባሮቹ ጭምር በእግዚአብሔር እይታ ክፉ ናቸው። ሮሜ 14፥23 እንዲህ ይላል፣ "በእምነት ያልተደረገ ሁሉ ኀጢአት ነውና።" ይህም በእግዚአብሔር ጸጋ ላይ በትሕትና ከሚደገፍ ልብ የማይፈልቅ ተፈጥሯዊ 'ድርጊት' ሁሉ፣ ክፉ የመሆኑ መሠረታዊ ማረጋገጫ ነው።

አብዛኛው የሰው "መልካምነት" ክፉ የመሆኑን ማረጋገጫ አንድ ምሳሌ ግልጽ ያደርግልን ይሆናል። ዕድሜው በዐሥራዎቹ ያለ የአንድ ልጅ አባት እንደሆንክ ራስህን ዐስብ። ዛሬ ምሽት ወዳለው የቅርጫት ኳስ ውድድር ጓደኞቹን ጭኖ ለመሄድ ከመጠቀሙ አስቀድሞ መኪናዋን እንዲያጥብ ነገርከው፤ ያንንም ለማድረግ ተስማማ። በኋላም ተናደደ፤ እናም እንደዛ ማድረግ እንደማይፈልግ ነገረህ። አንተም በእርጋታ ግን ደግሞ ጠበቅ አድርገህ፣ ቀድሞ ቃል መግባቱን፣ አንተም ከእርሱ ምትጠብቀው ያንኑ እንደሆነ አስታወስከው፤ እንቢታውን ገለጻልህ። አንተም መልሰህ፣ "መልካም፤ ዛሬ ምሽት መኪናዋን የምትጠቀማት ከሆነ፣ ለማድረግ የተስማማህበት ያው ነው" አልከው። በመናደድ እየተወራጨ ከክፍሉ ወጣ፤ ኋላ ግን መኪናዋን እያጠባት ዐየኸው፤ ነገር ግን ይህን የሚያደርገው ለአንተ ካለው ፍቅር የተነሣ ወይም ክርስቶስን ከሚያከብር መሻት አንተን እንደ አባቱ ለማክበር አይደለም፤ ከጓደኞቹ ጋር ወደ ውድድሩ ስፍራ ለማቅናት ስለሚፈልግ እንጂ። "እንዲታዘዝ" ያስገደደውም ይኸው ነው፤ 'መታዘዝን' በትእምርተ ጥቅስ ውስጥ ያስቀመጥኩት ውጫዊ ብቻ በመሆኑ ነው።

ልቡ ግን የሳተ ነው። ይህን ስል፣ ምንም እንኳ ጠባዩ ከመጽሐፍ ቅዱስ ትእዛዛት ጋር የሚስማማ ቢሆንም፣ ለሰማዩ አባት ካለው የፍቅር ልብ ካልሆነ፣ የሰው ልጅ “በጎ ድርጊት” ሁሉ በክፋት የተበከለ ነው ማለቴ ነው።

እጅግ ክፉ የሆነውን የሰው ልብ፣ ከሌሎች ሰዎች ጋር ባለ ግንኙነት ብቻ ለሚገመግም ሰው ሁኔታው ተለይቶ አይታወቀውም። ልጅህ ጓደኞቹን ወደ ቅርጫት ኳስ ጨዋታ ስፍራ ይወስዳቸዋል፤ ይህም “ደግነት” ነው፤ እነርሱም እንደ ጥቅም ይወስዱታል። ስለዚህም የድርጊቶቻችን ክፋት፣ በሌሎች ላይ በሚያደርሰው ጉዳት ብቻ ሊለካ አይችልም ማለት ነው። ውድቀት በቅድሚያ እኛ ከእግዚአብሔር አንጻር ያለን ሁኔታ፣ በመቀጠል ከሰው አንጻር ያለን ሁኔታ መሆኑን ሮሜ 14፥23 ግልጽ ያደርገዋል። ከዚህ ካልጀመርነው በስተቀር፣ የተፈጥሯዊ ውድቀታችንን አጠቃላይነት በፍጹም አንረዳውም።

የሰው ውድቀት ቢያንስ በአራት መንገዶች አጠቃላይ (ሙሉ) ነው።

1. **የእኛ ዐመፃ በእግዚአብሔር ላይ አጠቃላይ ነው።**

ከእግዚአብሔር ጸጋ ተለይቶ በእግዚአብሔር ቅድስና ሐሤት ማድረግ የለም፤ ደግሞም ለእግዚአብሔር ሉዓላዊ ሥልጣን ወዶና ፈቅዶ መገዛትም የለም።

ርግጥ ነው በአጠቃላይ የወደቀ ሰው ሃይማኖታዊ እንዲሁም በጣም ሰው ወዳድ ሊሆን ይችላል። ኢየሱስም ማቴዎስ 6፥1-18 ላይ እንዳለው ይጸልዩ፣ ምጽዋት ይሰጡ እና ይጾሙ ይሆናል። ነገር ግን እንደ ሕፃናት ልብ፣ በእግዚአብሔር ነጻ ጸጋ ላይ ካላቸው እምነት ካልሆነ፣ ይኸው ሃይማኖታቸው በፈጣሪአቸው መብት ላይ የሚደረግ ዐመፃ ነው። ሃይማኖት፣ ሰው በራሱ መተማመኑን ለመዘንጋት እና ተስፋውን በሙሉ በእግዚአብሔር ላይ ለመጣል ፈቃደኛ አለመሆኑን ከሚደብቅበት ዋነኛ መንገዶች አንዱ ነው። (ሉቃ. 18፥9-14፤ ቈላ. 2፥20-23)

የዐመፃችን አጠቃላይነት በሮሜ 3፥9-11፡18 ላይ ይታያል። "አይሁድም ሆኑ አሕዛብ፣ ሁሉም ከኀጢአት በታች እንደ ሆኑ አስቀድመን ከሰናቸዋል፤ እንዲህ ተብሎ እንደተጻፈ፤ 'ጻድቅ ማንም የለም፤ አንድም እንኳ፤ አስተዋይ የለም፤ እግዚአብሔርንም የሚሻ አንድም የለም።' " … "በዐይናቸው ፊት የእግዚአብሔር ፍርሀት የለም።" የትኛውም እግዚአብሔርን የሚያከብር ለእርሱ ያለ መሻት፣ የእግዚአብሔር ስጦታ ነው። ይህም ተፈጥሯዊ መልካምነታችን አይደለም፤ ለእግዚአብሔር ያለንን ተፈጥሯዊ መቋቋም፣ እግዚአብሔር በምሕረቱ መርታቱን መግለጫ ነው።

## ፍጥረታዊ ሰው እግዚአብሔርን አይፈልግም

ሰው በተፈጥሯዊ ሁኔታው፣ እግዚአብሔርን በእውነትኛ መፈለግ ይፈልገዋል ማለት ተረት ነው። ሰዎች እግዚአብሔርን ይፈልጉታል፤ ነገር ግን እርሱን በማንነቱ አይፈልጉትም። የሚፈልጉት በአጣብቂኝ ጊዜ ከሞት እንዲጠብቃቸው፣ ወይም ደግሞ ዓለማዊ ደስታቸውን እንዲያበዛላቸው ነው። በዳግም ልደት ካልሆነ፣ ማንም ወደ እግዚአብሔር ብርሃን አይመጣም።

አንዳንዶች ወደ ብርሃኑ ይመጣሉ፤ ነገር ግን ዮሐንስ 3፥20-21 (ቀ.ኃ.ሥ) ስለ እነርሱ የሚለንን እንስማ፣ "ክፉ የሚያደርግ ሁሉ ብርሃንን ይጠላልና፥ *ሥራውም* እንዳይገለጥ ወደ ብርሃን አይመጣም፤ እውነትን የሚያደርግ ግን *ሥራው* በእግዚአብሔር ተደርጎ እንደ ሆነ ይገለጥ ዘንድ ወደ ብርሃን ይመጣል።" አዎን ወደ ብርሃኑ የሚመጡ አሉ፤ እነርሱም *ሥራዎቻቸው* በእግዚአብሔር የተሠራላቸው ናቸው። "በእግዚአብሔር የተደረገላቸው" ማለትም በእግዚአብሔር የተሠራላቸው ማለት ነው። በጸጋ ከሆነው ከዚህ የእግዚአብሔር *ሥራ* ውጪ፣ ሁሉም ሰው የእግዚአብሔርን ብርሃን ይጠላል፤ ደግሞም ከፋቱ እንዳይገለጥበት ስለሚፈራ ወደ እርሱ አይመጣም—ይህም አጠቃላይ የሆነ ዐመፅ ነው። "እግዚአብሔርን የሚፈልግ የለም… በዐይኖቻቸው ፊት እግዚአብሔርን መፍራት የለም።"

## 2. ሰው በአጠቃላይ ዐመፅ ውስጥ ሆኖ፣ የሚያደርገው ማናቸውም ነገር ኀጢአት ነው።

በሮሜ 14፥23 ጳውሎስ፣ "በእምነትም ያልተደረገ ሁሉ ኀጢአት ነውና" ይለናል። ስለዚህም ሁሉም ሰዎች በአጠቃላይ ዐመፀኝነት ውስጥ ያሉ ከሆነ፣ የሚያደርጉት ማናቸውም ድርጊት የዐመፃቸው ውጤት ነው፤ እናም ከኀጢአታዊ ዐመፃቸው መካከል አንዱ ይሆናል እንጂ፣ ለእግዚአብሔር ክብር አይሆንም። በርግጥ እነዚህ ከውስጣዊ አለማመን የሚመነጩ ድርጊቶች በውጭ ከተገለጠው ከእግዚአብሔር ፈቃድ ጋር ይስማማሉ (ለምሳሌ፡- ለወላጆች መታዘዝ ወይም እውነትን መናገር)። ነገር ግን በዚህ ውጫዊ መስማማት ምክንያት ብቻ ከእግዚአብሔር ፍጹም ፈቃድ ጋር የሚስማሙ አይሆኑም። ሐዋርያው፣ "በእናንተ ዘንድ ሁሉ በፍቅር ይሁን" (1ኛ ቆሮ. 16፥14) ይለናል፤ ፍቅር ደግሞ የእምነት ፍሬ ነው (ገላ. 5፥6፤ 1ኛ ጢሞ. 1፥5)። ስለሆነም አብዛኛው ውጫዊ መልካም ድርጊት ክርስቶስን የሚያከብር እምነት ከሌለው ልብ የሚወጣ ነው፤ ስለዚህም ፍቅር የሌለው ነው፤ በዚህም ምክንያት ከእግዚአብሔር ትእዛዝ ጋር የማይስማማ ነው፤ ስለዚህም ኀጢአት ነው።

አንድ ንጉሥ፣ የራሱን ሠልጣኞች እንዴት እንደሚዋጉ ቢያስተምራቸውና ሠልጣኞቹም በንጉሣቸው ላይ ዐምፀው፣ ንጉሡ ያስተማራቸውን ራሱን ዘዴ መልሰው በእርሱ ላይ ቢጠቀሙ፣ ምንም ያህል የላቀ፣ አስገራሚ እና "መልካም" ቢሆንም፣ ይኸው ዘዴአቸው ክፉ ይሆናል።

ሰው በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠረ በመሆኑ ብቻ ሊያደርጋቸው የሚችላቸውን ብዙ ነገሮች ያደርጋል፤ ደግሞም ይህ በእግዚአብሔር አገልግሎት ይመሰገን ይሆናል። ነገር ግን ሰው ራሱን በሚያጸድቅበት የዐመፅ አገልግሎቱ ኀጢአተኛ ነው። እነርሱን(መልካም ተግባራት)፣ የእግዚአብሔር ልህቀት ገደለማሚቱ በመሆናቸው ልናወድሳቸው እንችላለን፤ ነገር ግን እግዚአብሔርን ችላ ባለ ዐላማቸው ስለዘሞቱ እናለቅሳለን።

በሮሜ 7፥18 (ቀ.ኃ.ሥ) ጳውሎስ፣ "በእኔ ማለት በሥጋዬ በጎ ነገር እንዳይኖር ዐውቃለሁና፤" ይላል። ይህም በዐመፃችን ሆነን የምናስበው ወይም የሚሰማን

ስሜት፣ ማናቸውም መልካም ያለመሆናቸው እውነታ መሠረታዊ መገለጫው ነው።

ሁሉም የዐመፃችን ክፍል ነውና። ጳውሎስ የራሱን ውድቀት በእነዚህ ቃላት፣ “በእኔ ማለት በሥጋዬ” በማለት የማረጋገጡ እውነታ፣ የእግዚአብሔር መንፈስ በእርሱ የሚሠራውን የትኛውንም መልካም ነገር ለመቀበል ፈቃደኛ መሆኑን ያሳያል (ሮሜ 15፥18)። “ሥጋ” የሚለው የሚያመለክተው፣ ከእግዚአብሔር መንፈስ ሥራ ውጪ፣ በተፈጥሯዊ ሁኔታው ያለን ሰው ነው። ስለዚህ ሐዋርያው ጳውሎስ በሮሜ 7፥18 እያለን ያለው፣ ከእግዚአብሔር መንፈስ ሥራ ውጪ የምናስበው፣ የሚሰማን ስሜት እንዲሁም የምንሠራው ሁሉ መልካም አለመሆኑን ነው።

## ረብ ያለው መልካም

“መልካም” የሚለው ቃል ሰፊ ትርጉሞች እንዳሉት እናውቃለን። ከእግዚአብሔር አንጻር ሲታዩ መልካም የማይሆኑትን አብዛኞቹን የወደቀውን ሰው ድርጊቶች ለማመልከት በሚሆን ጊዜ፣ ቃሉን በተወሰነ መልኩ ነው መጠቀም ያለብን።

ለምሳሌ:- የአብዛኞቹ የማያምኑ ሰዎች አለመግደላቸው እና በጎ የሆኑ ተግባራትን ማከናወናቸው መልካም ነው ማለት አለብን። እነዚህን ተግባራት “መልካም” ስንል ግን ወጣም ወረደ፣ እግዚአብሔር በቅዱሳት መጻሕፍት ካዘዘው ውጫዊ ሥርዐት ጋር የሚስማሙ ናቸው ማለታችን ነው።

ሆኖም ግን፣ ይህ ከእግዚአብሔር የተገለጠ ፈቃድ ጋር ያለ ውጫዊ መስማማት፣ ከእግዚአብሔር ጋር ባለ ግንኙነት ጽድቅ አይሆንም። ምክንያቱም በእርሱ ላይ በመደገፍ ወይም ለእርሱ ክብር ተብሎ አልተደረገም። የግብአቶቹ ሁሉ ሰጪ ራሱ ቢሆንም፣ የሚታመነው ግን ስለ እነርሱ አይደለም። ደግሞም በሁሉ ነገር ፈቃዱ ያ ቢሆንም (1ኛ ቆሮ. 10፥31)፣ የእርሱ ክብር አልተመሰገነም። ስለዚህም እነዚያ “መልካም” ድርጊቶቻችንም የዐመፃችን ክፍል ስለሆኑ እና በመጨረሻ ከእግዚአብሔር ጋር ባለን ግንኙነት ረብ ባለው መልኩ “መልካም” አይደሉም።

3. **ሰው ራሱን ለእግዚአብሔር ማስገዛት እና መልካም ማድረግ አለመቻሉ አጠቃላይ ነው።**

ከላይ "*ሥጋ*" የሚለውን ቃል ብንወስድ (ሰው ከእግዚአብሔር ጸጋ ርቆ)፣ ሙሉ በሙሉ ለዐመፅ ባርነት እንደተሰጠ ጳውሎስ ሲያውጅ እናገኛለን። ሮሜ 8፥7-8(*ቀ.ት.ሥ*)፣ "ስለ *ሥጋ* ማሰብ በእግዚአብሔር ዘንድ ጥል ነውና፤ ለእግዚአብሔር ሕግ አይገዛምና፥ መገዛትም ተስኖታል፤ በ*ሥጋ* ያሉትም እግዚአብሔርን ደስ ሊያሰኙት አይችሉም።"

"ስለ *ሥጋ* ማሰብ" (በቁሙ፣ "የ*ሥጋ* አእምሮ") ውስጥ፣ ዐዳሪ ከሆነው ከእግዚአብሔር መንፈስ ውጪ የሆነው የሰው አእምሮ ነው ("እናንተ ግን፣ የእግዚአብሔር መንፈስ በውስጣችሁ የሚኖር ከሆነ፣ በ*ሥጋ* ሳይሆን በመንፈስ ናችሁ" ሮሜ 8፥9)። ስለዚህም የፍጥረታዊ ሰው አእምሮ ለእግዚአብሔር የማይገዛ እና መገዛትም የማይችል ነው። ሰው ራሱን ማደስ አይችልም።

ኤፌሶን 2፥1 እኛ ክርስቲያኖች ሁላችን በአንድ ወቅት፣ "በበደላችን እና በኀጢአታችን ሙታን" ነበርን ይለናል። የሞታችንም ዋናው ነጥብ ከእግዚአብሔር ጋር ምንም ዐይነት መንፈሳዊ ሕይወት መኖር አለመቻላችን ነው። ቁስ አካላዊ ሕይወት ነበረን፤ ነገር ግን ልባችን ለእግዚአብሔር እንደ ድንጋይ ያለ ነበር (ኤፌ. 4፥18፤ ሕዝ. 36፥26)። ልባችንም በክርስቶስ የእግዚአብሔርን ክብር እንዳያይ የታወረና ማየትም የተሳነው ነበር (2ኛ ቆሮ. 4፥4-6)። ራሳችንን ማደስ ሙሉ በሙሉ የተሳነን ነበርን።

4. **ዐመፃችን በአጠቃላይ ዘላለማዊ ቅጣት የሚገባው ነው።**

ኤፌሶን 2፥3 ደግሞ በሙታንነታችን "የቍጣ ልጆች" ነበርን ይለናል። ይህም እኛን በእግዚአብሔር ዘንድ ሙታን ባደረገን በልባችን ብክለት ምክንያት ከእግዚአብሔር ቍጣ በታች ነበርን ማለት ነው።

የሲኦል እውንነት ጥፋታችን ኢ-ውሱን ስለመሆኑ የእግዚአብሔር ግልጽ ማስረጃ ነው።

ብክለታችን ዘላለማዊ ቅጣት የተገባው ባይሆን ኖሮ፣ የዘላለም ሥቃይን በመሰለ ከባድ ቅጣት እኛን በመቅጣቱ እግዚአብሔር ኢ-ፍትሐዊ በሆነ ነበር፤ ነገር ግን እግዚአብሔር የማያምኑትን ለዘላለም እሳት በመኮነኑ ፍትሐዊ እንደሆነ ቅዱሳት መጻሕፍት ያስተምራሉ (2ኛ ተሰሎንቄ 1፥6-9፤ ማቴ. 5፥29-30፤ 10፥28፤ 13፥ 49-50፤ 18፥8-9፤ 25፥46፤ ራእ. 14፥9-11፤20-10)። ስለዚህም ሲአል የአጠቃላይ ፍርድ ቅጣት የሆነውን ያህል፣ እኛም ከሚያድነው ከእግዚአብሔር ጸጋ ውጪ፣ ሙሉ በሙሉ በዛው ልክ መኮነን የሚገባን እንደሆንን ማሰብ አለብን።

## የአጠቃላይ ብክለታችን አስከፊው እውነታ

ሳጠቃልል፣ አጠቃላይ ውድቀት ማለት ዐመፃችን በእግዚአብሔር ላይ አጠቃላይ ነው፤ በዚህም ዐመፅ ሆነን የምናደርገው ማንኛውም ነገር ቢሆን ኀጢአት ነው፤ ለእግዚአብሔር መገዛት እና ራሳችንን ማደስ አለመቻላችን አጠቃላይ ነው፤ ስለዚህም ሙሉ በሙሉ ዘላለማዊ ቅጣት የሚገባን ነን።

ሁኔታችን በዚህ መጠን የከፋ መሆኑን የመቀበልን ጥቅም ማጉላቱ ከባድ ነው። በመሠረታዊነት፣ ራሳችንን መልካም እንደሆንን እና ከእግዚአብሔር ጋር በፍጹም ጥላቻ ውስጥ መሆናችንን አሳንሰን ካሰብን፣ የእግዚአብሔር ቤዝዎታዊ ሥራ አረዳዳችን ሰንካላ ይሆናል። ነገር ግን ከዚህ አስከፊ የአጠቃላይ ብክለታችን እውነታ ሥር ራሳችንን ዝቅ ብናደርግ፣ በቀጣይ አራት ነጥቦች የምንዳስሰውን የእግዚአብሔርን ሥራ ክብር እና ተአምር ልናይ እና ልናደንቅ በምንችልበት ስፍራ እንቈማለን።

የዚህ መጽሐፍ ዐላማ የእግዚአብሔርን ጸጋ ተመክሮአችንን የጠለቀ ማድረግ ነው። ማስጨነቅ፣ ተስፋ ማስቈረጥ እና ማደንዘዝ፣ በፍጹም የዚህ መጽሐፍ ዐላማ አይደለም። የበሽታችንን አደገኛነት ማወቅ፣ ሁላችንም በሐኪማችን ትልቅነት የበለጠ እንድንገረም ያደርገናል። በውስጣችን ሰፍኖ ያለውን የዐመፃችንን ልኬት ማወቅ፣ እግዚአብሔር በእኛ ላይ ላለው ለጸጋው መቻል እና ትዕግሥት ንቁዎች ያደርገናል። እግዚአብሔርን የምናመልክበት እና ሌሎች ሰዎችን በተለይም ጠላቶቻችንን የምንገናኝበት መንገድ፣ ግሩም እና ጥልቅ በሆነ ሁኔታ፣ ውድቀታችንን በሙላት በማወቅ ላይ ይደገፋሉ።

# የማይቋቋሙት ጸጋ

ተለምዶአዊውን የ “T U L I P” ቅደም ተከተል መቀየሬን ትገነዘባላችሁ። “I” የማይቋቋሙትን ጸጋ የሚወክል እና በተለምዶ አራተኛ ላይ የሚመጣ ቢሆንም፣ እኔ ግን አጠቃላይ ውድቀትን ከሚወክለው “T” በመቀጠል በሁለተኛነት አስቀምጬዋለሁ። ለዚህም ምክንያቴ፣ ባለፉት አመታት እንዳየሁት ብዙ ክርስቲያኖች “የማይቋቋሙት ጸጋ” ብለው ባይጠሩት እንኳ፣ የግል የሆነ ተመክሮ እና መረዳት አላቸው። የማይቋቋሙትን ጸጋ እውነትነት በግል መለማመድ፣ ሰዎች የእነዚህን ዐምስት ነጥቦች ምንነት ቶሎ እንዲያገኙ ይረዳቸዋል። ይህም ደግሞ እነርሱን ለሌሎቹ ነጥቦች መጽሐፍ ቅዱሳዊ ተኣማኒነት ክፍት ያደርጋቸዋል።

በተለይ ደግሞ፣ የመለወጣቸውን (ዳግም የመወለዳቸውን) ምስጋና ለራሳቸው ሊወስዱ የሚፈልጉ ጥቂት ክርስቲያኖችም አጋጥመውኛል። ሁሉንም ክብር ለእግዚአብሔር መስጠት እንድንፈልግ የሚያደርገን፣ ስለ እውነተኛው ጸጋ የሆነ ነገር በአማኝ ልብ ውስጥ አለ። ለምሳሌ አንድን አማኝ፣ “ጓደኞችህ ወንጌል ሰምተው ያላመኑብኝ፣ አንተ ግን ወንጌልን ሰምተህ ያመንክብኝ ለምንድነው?” የሚለውን የኢየሱስን የመጨረሻ ፍርድ ጥያቄ እንዴት እንደሚመልስ ብጠይቀው፣ እጅግ ጥቂት አማኞች ብቻ ናቸው እንዲህ በማለት የሚመልሱት፣ “ምክንያቱም እኔ የተሻልኩ ብልኅ፣ ምርጥ ወይም እጅግ መንፈሳዊ፣ ሥልጡን ወይም እጅግ ትሑት ስለ ነበርኩ ነው።” ነገር ግን አብዛኞቻችን፣ “ከእግዚአብሔር ጸጋ የተነሣ ነው” በማለት ለእግዚአብሔር ጸጋ ክብር መስጠት እንዳለብን በደመ-ነፍሳዊ ሁኔታ ይሰማናል። በሌላ አነጋገር፣ በእኛ መለወጥ ላይ የእግዚአብሔር ጸጋ ወሳኝ እንደነበር በማስተዋል እናውቃለን ማለት ነው። የማይቋቋሙት ጸጋ ስንልም ይህንን ማለታችን ነው።

## ግን እኮ ጸጋውን እንቋቋመዋለን

የማይቋቋሙት ጸጋ አስተምህሮ፣ ሁሉም የመንፈስ ቅዱስ ተጽእኖ ሊቋቋሙት የማይቻል ነው ማለት አይደለም። ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በወደደው ጊዜ፣

የትኛውንም መቋቋም ሊረታ እና የራሱን ተጽእኖ የማይቋቋሙት ሊያደርገው ይችላል ማለት ነው።

በሐዋርያት *ሥራ* 7፥51(*ቀ.ት.ሥ*) እስጢፋኖስ ለአይሁድ መሪዎች እንዲህ ይላቸዋል፣ "እናንተ አንገተ ደንዳኖች ልባችሁና ጆሮአችሁም ያልተገረዘ፣ እናንተ ሁልጊዜ መንፈስ ቅዱስን ትቃወማላችሁ፤ አባቶቻችሁ እንደተቃወሙት እናንተ ደግሞ።" ሐዋርያው ጳውሎስም መንፈስ ቅዱስን ስለ ማሳዘን እና መንፈስን ስለማጥፋት ይናገራል (ኤፌ. 4፥30፤ 1ኛ ተሰ. 5፥19)። እግዚአብሔር፣ ሰው የሚቋቋማቸውን ብዙ ልመናዎች እና ትእዛዛት ይሰጣል። በርግጥ የክፉዎቹ ገበሬዎች ምሳሌ እንደሚያሳየን (ማቴ. 21፥33-43፤ ሮሜ 10፥21)፣ በብሉይ ኪዳኑ ሙሉው የእስራኤል ታሪክ፣ ሰው የእግዚአብሔርን ሕግጋትና ተስፋዎች የሚቋቋምበትና የሚገፋበት አንድ ወጥ ታሪክ ነው። ይህ መቋቋም የእግዚአብሔርን ሉዓላዊነት አይጣረስም። እግዚአብሔር ይፈቅደዋል፤ በወደደው ጊዜ ደግሞ ይረታዋል።

የማይቋቋሙት ጸጋ አስተምህሮ ማለት እግዚአብሔር ሉዓላዊ ነው ስለዚህም በፈቀደው ጊዜ የትኛውንም መቋቋም ድል ማድረግ ይችላል ማለት ነው። "በሰማይ ኀይላት፣ በምድርም ሕዝቦች ላይ፣ የወደደውን ያደርጋል፤ እጁን መከልከል የሚችል የለም" (ዳን. 4፥35)። "አምላካችን በላይ በሰማይ ነው፤ በሰማይም በምደርም የፈቀደውን ሁሉ አደረገ" (መዝ. 115፥3—*ቀ.ት.ሥ*)። እግዚአብሔር ሉዓላዊ ዕቅዱን ለመተግበር በተነሣ ጊዜ፣ ማንም ተሳክቶለት ሊቋቋመው አይችልም። "ሁሉን ታደርግ ዘንድ ቻይ እንደሆንህ፥ አሳብህም ይከለከል ዘንድ ከቶ እንደማይቻል አወቅሁ።" (ኢዮ 42፥2—*ቀ.ት.ሥ*)።

## የእግዚአብሔር እኛን ወደ እምነት የማምጣት ሥራ

ይህ ሐዋርያው ጳውሎስ በሮሜ 9፥14-18 ያስተማረው ሲሆን፣ ተቃዋሚዎቹም "እንግዲህ ስለምን እስከ አሁን ይነቅፋል? ፈቃዱንስ የሚቃወም ማን ነው?" እንዲሉ ያደረጋቸው ነው፤ ጳውሎስም እንዲህ ብሎ ይመልሳል፣ "ነገር ግን አንተ ሰው ሆይ ለእግዚአብሔር የምትመልስ ማን ነህ? *ሥራ* ሠሪውን ስለምን እንዲህ አድርገህ ሠራኸኝ ይለዋልን? ወይም ሸክላ ሠሪ ከአንዱ ጭቃ ክፍል አንዱን ዕቃ

ለክብር አንዱንም ለውርደት ሊሠራ በጭቃ ላይ ሥልጣን የለውምን?" (ሮሜ 9፥ 20-21—*ቀ.ቃ.ሥ*) ።

በዋናነት፣ የማይቋቋሙት ጸጋ እኛ እንድን ዘንድ የልቦናችንን ዐመፀኝነት ለመርታት እና በክርስቶስ ወደማመን የሚያመጣንን የእግዚአብሔርን ሉዓላዊ ሥራ የሚያመለክት ነው። በቀደመው ምዕራፍ ላይ እንዳየነው የአጠቃላይ ውድቀት አስተምህሮ እውነት ከሆነ፣ ያለ ማይቋቋሙት ጸጋ እውነትነት ድነት ከቶ ሊኖር አይችልም። በኀጢአታችን ሙታን እና በዐመፀኛው ተፈጥሮአችን ምክንያት ለእግዚአብሔር መገዛት የተሳነን ከሆንን፣ እግዚአብሔር ይህንን ዐመፀኝነታችንን ካላሸነፈው በስተቀር በፍጹም በክርስቶስ አናምንም።

"አዎን፤ መንፈስ ቅዱስ እኛን ወደ እግዚአብሔር ይስበናል፤ ነገር ግን ፈቃዳችንን በመጠቀም ይህንን ስበት መቃወምም ሆነ መቀበል እንችላለን" የሚል ሰው ይኖራል። መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስተምረን ግን ይህን አይደለም። ቀጣይ ከሆነው የሚያድን ጸጋ ተጽእኖ ውጪ፣ ሁሌም ነጻነታችንን እግዚአብሔርን ለመቋቋም እንጠቀማለን። "ለእግዚአብሔርም መገዛት ተስኖታል" ማለት ይኸው ነው። "ስለ ሥጋ ማሰብ በእግዚአብሔር ዘንድ ጥል ነውና፤ ለእግዚአብሔር ሕግ አይገዛምና፣ መገዛትም ተስኖታል፤ በሥጋ ያሉትም እግዚአብሔርን ደስ ሊያሰኙት አይችሉም" (ሮሜ 8፥7-8)።

አንድ ሰው ራሱን ለእግዚአብሔር ለማስገዛት ትሑት መሆን ከቻለ፣ ለዚያ ሰው እግዚአብሔር ዐዲስና ትሑት ተፈጥሮን ስለሰጠው ነው። አንድ ሰው በልቡ ድንዳኔ የሚጸና እና ለእግዚአብሔር ለመገዛት ዕቡይ ከሆነ፣ ይህ ሰው የሚመለስ ልብ ስላልተሰጠው ነው። ይህንን በአሳማኝ መልኩ ለማየት ግን ቅዱሳት መጻሕፍትን መመልከት ያስፈልጋል።

## አብ ካልሳበው በቀር

ኢየሱስ በዮሐንስ 6፥44፣ "የላከኝ አብ ካልሳበው በቀር ማንም ወደ እኔ መምጣት አይችልም" ብሎናል። ይህ መሳብ የጸጋ ሉዓላዊ ሥራ ነው፤ ያለ እርሱ ማናችንም በእግዚአብሔር ላይ ካለን ዐመፃ ልንድን አንችልም። አንድ ሰው ደግሞ፣ "እርሱ

የተወሰኑ ሰዎችን ሳይሆን፣ ሁሉንም ነው የሚስበው” ብሎ ይቃወም ይሆናል። ከዚያም ዮሐንስ 12፥32 ይጠቅስ ይሆናል፤ “እኔ ግን ከምድር ከፍ ከፍ ባልሁ ጊዜ *ሰውን ሁሉ ወደ ራሴ እስባለሁ።”*

ነገር ግን ይህ ቅዋሜ ከበድ ያሉ ብዙ ችግሮች አሉበት። ከችግሮቹ አንዱ፣ “ሰውን ሁሉ” በማለት የተተረጐመው ቃል (በግሪኩ - ፓንታስ) ሲሆን፣ ትርጒሙም “ሁሉ” ማለት ነው። “ሰው” የሚለው ቃል የለም። በቀላሉ ኢየሱስ ያለው እንዲህ ነው፣ “እኔ ግን ከምድር ከፍ ከፍ ባልሁ ጊዜ ሁሉን ወደ ራሴ እስባለሁ።” ይህንንም ባየን ጊዜ ይህ “ሁሉ” ምን ሊሆን እንደሚችል ከዮሐንስ ወንጌል ተመሳሳይ ዐውዶች መጠየቅ አለብን።

አንድ ተመሳሳይ ዐውድ ከዚህ በሚቀድመው ምዕራፍ ያለ ሲሆን (ዮሐ. 11፥50-52—*ቀ.ኃ.ሥ*)፣ ሊቀ ካህኑ ቀያፋ ከሚያውቀው ይልቅ እውነቱን እየተናገረ እንደሆነ ዮሐንስ ይነግረናል።

> “...ሕዝቡም ሁሉ ከሚጠፋ አንድ ሰው ስለ ሕዝቡ ይሞት ዘንድ እንዲሻለን አታስቡም አላቸው። ይህንም የተናገረው ከራሱ አይደለም፥ ነገር ግን በዚያች ዓመት ሊቀ ካህናት ነበረና ኢየሱስ ስለ ሕዝቡ ሊሞት እንዳለው ትንቢት ተናገረ፤ ስለ ሕዝቡም ብቻ አይደለም፥ ነገር ግን የተበተኑትን የእግዚአብሔርን ልጆች በአንድነት እንዲሰበስባቸው ነው።”

ዮሐንስ በዚህ ወንጌል እንዳቀረበው፣ እነዚህ የመጨረሻ ዐረፍተ ነገሮች፣ የኢየሱስን ሞት ስፋት የሚገልጹ ናቸው። ኢየሱስ የሞተው ለአንድ ብሔር አይደለም፤ “ነገር ግን የተበተኑትን የእግዚአብሔር ልጆች በአንድነት ለመሰብሰብ ነው"—ሁሉንም። ይህም ወንጌሉን በሰሙ ጊዜ እግዚአብሔር በውጤታማነት ወደ ራሱ የሚስባቸውን አሕዛብ የሚያመለክት ነው። “የእግዚአብሔር ልጆች” ተብለው ይጠራሉ፤ ምክንያቱም ጳውሎስ ኤፌሶን 1፥4-5 ላይ እንደሚለው እግዚአብሔር የራሱ ልጆች አድርጎ ለመውሰድ መርጧቸዋል።

ስለዚህ ይህ ጥሩ ትይዩ ከሆነን፣ ዮሐንስ 12፥32 ላይ “*ሁሉ”* የሚለው ሁሉንም ሰው ሳይሆን፣ “ሁሉንም የእግዚአብሔር ልጆች” ነው። “እኔ ግን ከምድር ከፍ ከፍ

ባልሁ ጊዜ ሁሉንም *የእግዚአብሔርን ልጆች* ወደ ራሴ እስባለሁ።" ከነገድ ሁሉ፣ ከቋንቋ ሁሉ፣ ከሕዝብ ሁሉ፣ ከወገንም ሁሉ ነው (ራእ. 5፥9)።

ወይም እንዲህ ማለት ትችላላችሁ፣ "በጎቼን ሁሉ ወደ ራሴ እስባለሁ" ምክንያቱም ኢየሱስ እንዲህ ይላል፣ በዮሐንስ 10፥15፣ "ሕይወቴንም ስለ በጎቼ አሳልፌ እሰጣለሁ።"—ስለ ሁሉም። ደግሞም ዮሐንስ 10፥27(ቀ.ኃ.ሥ)፣ "በጎቼ ድምጼን ይሰማሉ እኔም አውቃቸዋለሁ ይከተሉኝማል"—እነርሱ ሁሉም። ወይም እንዲህ ማለት ትችላላችሁ፣ "ከእውነት የሆነን ሁሉ እስበዋለሁ" ምክንያቱም ኢየሱስ በዮሐንስ 18፥37 ላይ እንዲህ ብሏል፣ "ከእውነት የሆነ ሁሉ ይሰማኛል።" ወይም እንዲህ ማለት ትችላላችሁ፣ "ከእግዚአብሔር የሆነን ሁሉ እስበዋለሁ" ምክንያቱም ኢየሱስ በዮሐንስ 8፥47 "ከእግዚአብሔር የሆነ እግዚአብሔር የሚናገረውን ይሰማል።" እንዲህ ማለትም ትችላላችሁ፣ "አብ የሚሰጠኝን ሁሉ እስበዋለሁ" ምክንያቱም ዮሐንስ 6፥37፣ "አብ የሚሰጠኝ ሁሉ ወደ እኔ ይመጣል" ይላልና።

በሌላ አነጋገር፣ የዮሐንስን ወንጌል በማንበብ መዝለቅ ማለት እግዚአብሔር አብ እና እግዚአብሔር ወልድ ሰዎችን ከጨለማ ወደ ብርሃን የመሳባቸው እውነታ ነው። ደግሞም ክርስቶስ የሞተው ለዚህ ነው። ወደ ላይ ከፍ ከፍ ያለውም ለዚሁ ነው—እነርሱ ሁሉ ወደ እርሱ ይሳቡ ዘንድ—ሁሉም ልጆቹ፣ ሁሉም በጎቹ፣ ከእውነት የሆኑ ሁሉም፣ አብ ለልጁ የሰጣቸው ሁሉም። ዮሐንስ 12፥32 ተጨማሪ የሚያደርገው፣ መላውን ዓለም ወደ ተሰቀለው ክርስቶስ በመጠቆም እና ማንም በእርሱ የሚያምን እንደሚድን የምሥራቹን ቃል በመስበክ፣ ይህ ዛሬም በታሪክ የሚከሰት መሆኑን ነው። ከፍ ስላለው ክርስቶስ በሚሰበከው በዚያ ስብከት፣ እግዚአብሔር የደንቆሮችን ጆሮ ይከፍታል። በጎቹ ድምፁን ይሰማሉ፤ ደግሞም ኢየሱስን ይከተላሉ (ዮሐንስ 10፥16፣27)።

ነገር ግን፣ "የላከኝ አብ ካልሳበው በቀር ማንም ወደ እኔ መምጣት አይችልም" የሚለው የዮሐንስ 6፥44 መሳብ፣ ወደ እርሱ መምጣትን በተግባር የሚከስት መሆኑን ለመካድ፣ ዮሐንስ 12፥32 ("ሁሉን እስባለሁ") የሚለውን ለመጠቀም ዋነኛው መከራከሪያ፣ በእግዚአብሔር መሳብ እና ይሁዳ ኢየሱስን እስከ ፍጻሜው መከተል ባለመቻሉ መካከል ያለውን ትስስር ዮሐንስ የሚገልጽበት መንገድ ነው።

ኢየሱስ በዮሐንስ 6፥64-65 እንዲህ ይላል፣

> “ይሁን እንጂ ከእናንተ የማያምኑ አንዳንዶች አሉ።” (ኢየሱስ እነማን እንደማያምኑ እና ማን አሳልፎ እንደሚሰጠው ቀድሞውኑ ያውቅ ስለነበረ ነው።) ቀጥሎም እንዲህ አለ፣ “ከአብ ካልተሰጠው በቀር፣ ማንም ወደ እኔ ሊመጣ አይችልም ያልኋችሁ ለዚህ ነው።”

ልብ በሉ፤ ኢየሱስ በዮሐንስ 6፥44፣ “የላከኝ አብ ካልሳበው በቀር ማንም ወደ እኔ መምጣት አይችልም” ያለበት ምክንያት፣ ከእነርሱ “የማያምኑ አንዳንዶች” የኖሩበትን ምክንያት ለመግለጽ ነው። በሌላ አገላለጽ እንዲህ ማለት እንችላለን፤ የተሰጠው ትምህርትና ግብዣ ሁሉ እያለ ይሁዳ በእርሱ እንደማያምን ኢየሱስ ከመጀመሪያም ያውቅ ነበር። ይህንንም ያውቅ ስለ ነበር ነገሩን በእነዚህ ቃላት ይገልጻል፣ “ከአብ ካልተሰጠው በቀር ማንም ወደ እኔ ሊመጣ አይችልም።”

በይሁዳ ሕይወት ብዙ ተጽእኖች ነበሩ። በዚህ ረገድ ይሁዳ ለሦስት ዓመታት ተለምኗል፤ ተጋብዟል፤ ደግሞም ተስቧል። በዮሐንስ 6፥44 እና 6፥65 ላይ የኢየሱስ ዐሳብ፣ ይሁዳ ጸጋን መቋቋሙ የመጨረሻው ወሳኝ ተግባር እንዳልሆነ ነው። የመጨረሻው ወሳኝ የነበረው ነገር እርሱ እንዲመጣ “ያልተሰጠው” መሆኑ ነው። እርሱ በአብ “አልተሳበም።” ደግሞም ወሳኙ የማይቋቋመው የጸጋ ስጦታ አልተሰጠውም። “ስለማይቋቋሙት ጸጋ” የምንናገረው በዚህ ምክንያት ነው። ሁላችንም በራሳችን እንደ ይሁዳ ጸጋን የምንቋቋም ነን። ማናችንም ብንሆን ወደ ኢየሱስ የመጣንበት ምክንያት ከይሁዳ ይልቅ ንቁዎች፣ ወይም ብልኆች፣ ወይም ብቁዎች ስለሆንን አይደለም፤ ነገር ግን አብ መቋቋማችንን በመርታት ወደ ክርስቶስ ስለሳበን ነው።

ሁላችንም የዳንነው ልንቋቋመው በማይቻል ጸጋ ነው—አስደናቂ ጸጋ!

ቢተኛም መንፈሴ ለዘመናት ታስሮ

በተፈጥሮ ጽልመት በኀጢአት ተጠፍሮ

ዐይኖችህ ረጩ የብርሃን ጮራ

እኔን አነቃኝ፤ እስር ቤቱም በራ

ሰንሰለቴ ወደቀ፤ ልቤም ነጻ ሆነ

ተነሣሁ፤ ተራመድኩ፤ አንተንም ተከተልኩ።

አብ ልንቋቋመው በማንችል እና በአስተማማኝ ሁኔታ ወደ ኢየሱስ “በሳበን” ጊዜ የሆነው ይህ ነው።

## የድነት መስፈርቶችም የእግዚአብሔር ስጦታ ናቸው

ሐዋርያው ጳውሎስ ንስሓ የእግዚአብሔር ስጦታ እንደሆነ የሚገልጽበትን መንገድ አስተውሉ። በ2ኛ ጢሞ. 2፥24-25 እንዲህ ይላል፣ “የጌታም አገልጋይ ሊጣላ አይገባውም፤ ይልቁን ለሰው ሁሉ ገር፣ ለማስተማር ብቃት ያለው፣ ትዕግሥተኛም መሆን ይገባዋል፤ እውነትን ወደ ማወቅ ይደርሱ ዘንድ፣ እግዚአብሔር *ንስሓን እንደሚሰጣቸው* ተስፋ በማድረግ የሚቃወሙትን በየዋህነት የሚያቃና መሆን ይኖርበታል።”

ልክ ኢየሱስ ዮሐንስ 6፥65 ላይ ወደ እርሱ መምጣት ከአብ “የሚሰጥ” ነው እንዳለው፣ እንዲሁ ጳውሎስም ንስሓ ከእግዚአብሔር “የሚሰጥ” ነው ይለናል፣ “እግዚአብሔር ንስሓን እንደሚሰጣቸው”። ድነት ብቻ የእግዚአብሔር ስጦታ ነው እያለ አይደለም፤ የድነት መስፈርቶችም ስጦታዎች ናቸው እያለ ነው። አንድ ሰባኪ፣ “ንስሓ ግቡ፤ ወደ ክርስቶስም ኑ” ሲል የሆነ ሰው በሰማ ጊዜ፣ ይህን ጥሪ

መቋቋም ደግሞም አለመታዘዝ ይችላል። “በፍጹም ንስሓ አልገባም” ሊልም ይችላል።

ነገር ግን እግዚአብሔር ንስሓን ከሰጠው ሊቋቋመው አይችልም፤ ምክንያቱም የንስሓ ስጦታ እግዚአብሔር ልባችንን ቀይሮታል ደግሞም ንስሓ ለመግባት ፈቃደኛ አድርጎታል ማለታችን ነው። በሌላ አገላለጽ፣ የንስሓ ስጦታ ማለት ለንስሓ ያለን መቋቋም መረታት ነው። ይህንን የእግዚአብሔር ሥራ “የማይቋቋሙት ጸጋ” በማለት የምንጠራው በዚህ ምክንያት ነው። ሁላችንም ወደ ንስሓ የመጣነው እንዲህ ነው።

እውነተኛ ንስሓን የተቀበሉ በሺዎች የሚቈጠሩ ሰዎች ይህንን አያውቁም። በእንዴት እንደተለወጡ የተሳሳቱ ነገሮችን ሲማሩ ቈይተዋል፤ ስለዚህም አምልኳቸው እና ፍቅራቸው የቀነጨረ ነው። ምናልባት አንተም ከእነርሱ አንዱ ልትሆን ትችላለህ። ይህ እውነት ከሆነ በአስተማሪዎችህ ላይ እንዳትቈጣ፤ ነገር ግን 2ኛ ጢሞ. 2፥25ን በማየትህ ሐሤት አድርግ፤ ደግሞም የንስሓን አስደናቂነት እንደ ዐዲስ በማወቅህ፣ ልብህ በምስጋና እና በትሑት ደስታ ይትረፍረፍ። ይህ ንስሓ ፍጹም ነጻ የሆነ የእግዚአብሔር ጸጋ ስጦታ ነው። ይህም ማለት እግዚአብሔር ከምታስበው በላይ በልዩ ሁኔታ ይወድሃል ማለት ነው።

## ከፈቃዳችን ጋር አይጣረስም

የማይቋቋሙት ጸጋ፣ እግዚአብሔር ንስሓ እንድንገባ ወይም እንድናምን እና ኢየሱስን እንድንከተል ፈቃዳችንን በመጣስ፣ የሚያስገድደን መሆኑን እንደማያመለክት ግልጽ መሆን አለበት። እንደዚያ ቢሆንማ ቃሎቹም ተጣርሷዊ በሆኑ ነበር፤ ምክንያቱም ማመን፣ ንስሓ መግባት እና መከተል ሁሌም ፈቃደኝነት ናቸው፤ አልያም ደግሞ ግብዝነት ናቸው። የማይቋቋሙት ጸጋ ፈቃደኛ የማይሆነውን ወደ እግዚአብሔር መንግሥት አይጎትትም፤ ነገር ግን ፈቃደኛ የማይሆነውን ፈቃደኛ እንዲሆን ያደርገዋል። እንደ መንጠቆና ሰንሰለት በውጪው ማስገደድ አይሠራም፤ የሚሠራውም ልክ እንደ ጥማት፣ ራብ እና እንደ አሳማኝ ፍላጎት ከውስጥ በሆነ ኀይል ነው።

ስለዚህ የማይቋቋሙት ጸጋ፣ ሰዎች ምክንያታዊ የሆነውንና ከውስጥ መሻታቸውም ጋር የሚጣጣመውን እንዲያደርጉ ለማሳመን ከሚሞክረው ስብከት እና ምስክርነት ጋር የሚስማማ ነው።

እግዚአብሔር በልብ ላይ የሚያከናውነውን ልዕለ ተፈጥሯዊ ለውጥ ለመከወን የቃሉን አገልግሎት ይጠቀማል። ይህም ለውጥ ንስሓን እና እምነትን ያመጣል።

ሐዋርያው ጳውሎስ በ 1ኛ ቆሮንቶስ 1፥23-24 “እኛ ግን የተሰቀለውን ክርስቶስን እንሰብካለን፤ ይህም ለአይሁድ መሰናከል፣ ለአሕዛብ ደግሞ ሞኝነት ነው። እግዚአብሔር ለጠራቸው ግን፣ አይሁድም ሆኑ ግሪኮች፣ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ኀይል፣ የእግዚአብሔርም ጥበብ ነው።” በዚህ ክፍል ውስጥ ያሉትን ሁለት ዐይነት “ጥሪዎች” ልብ በሉ።

የመጀመሪያው፣ የሐዋርያው ጳውሎስ ስብከት ለሁሉም ነው፤ ለአይሁድም ለግሪክ ሰዎችም። ይህም የወንጌሉ *አጠቃላይ* ጥሪ ነው። ድነትን ያለ አንዳች አድሎ እና መለያየት ለሁሉ ያቀርባል። በተሰቀለው ክርስቶስ የሚያምን ማንም ቢኖር፣ እርሱ አዳኙ እና ጌታው ይሆንለታል። ነገር ግን ይኸው ለሁሉም የሆነው አጠቃላይ ጥሪ ሁሌም በማይቀበሉት ጆሮዎች ላይ ያርፋል፤ ደግሞም ሞኝነት ተብሎ ይጠራል።

በሁለተኛነት፣ ሐዋርያው ጳውሎስ ሌላ ዐይነት ጥሪን እንደሚያመለክት አስተውሉ። እንዲህም ይለናል፤ ከሚሰሙቱ ከአይሁድና ከግሪክ ሰዎች መካከል፣ አጠቃላይ ጥሪን ከመስማት በተጨማሪ፣ በሌላ መንገድ “የተጠሩ” የተወሰኑ ሰዎች አሉ። “እግዚአብሔር ለጠራቸው ግን፣ አይሁድም ሆነ ግሪኮች ክርስቶስ የእግዚአብሔር ኀይል፣ የእግዚአብሔርም ጥበብ ነው” (ቁ. 24)። በሌላ አገላለጽ፣ መስቀሉን እንደ ሞኝነት ሳይሆን እንደ እግዚአብሔር ኀይል እና ጥበብ በሚቈጥሩበት አጠራር ተጠርተዋል ማለት ነው።

ክርስቶስን የሚያዩበትን መንገድ የቀየረ ነገር በልባቸው ተከስቷል። ይህንንም እንደ አጠቃላይ ጥሪ ሳይሆን፣ የእግዚአብሔር ውጤታማው ጥሪ እንደሆነ መግለጽ አለብን። ይህም ልክ እንደ አልዓዛር ከመቃብር መጠራት ዐይነት ነው። ኢየሱስም በታላቅ ድምፅ “አልዓዛር ሆይ፥ ወደ ውጭ ና!” ብሎ ተጣራ (ዮሐ. 11፥

43—ቀ.ኃ.ሥ)። የሞተውም ሰው ወደ ውጭ ወጣ። ይህ ዐይነቱ ጥሪ የሚጠራውን ነገር የሚፈጥር ጥሪ ነው። “ሕያው ሁኑ!” ካለ ሕይወትን ይፈጥራል። “ንስሓ ግቡ!” ካለ ንስሓን ይፈጥራል። “እመኑ” ካለ እምነትን ይፈጥራል። “ተከተሉኝ!” ካለ ደግሞ መታዘዝን ይፈጥራል።

ሐዋርያው ጳውሎስ በዚህ መንገድ የተጠሩ ሰዎች መስቀሉን እንደ ሞኝነት ሳይሆን፣ እንደ እግዚአብሔር ኀይል እንደሚቈጥሩት ይነግረናል። ወደ ክርስቶስ የሚመጡት በግዴታ አይደለም። ያለ ልክ ውድ እንደሆነ የቈጠሩትን ነገር በነጻነት እየመረጡ ነው። በእነርሱ የተከሠተው ይኸው ነው። ለመስቀሉም ያላቸው መቋቋም የተረታበት ምክንያት፣ የእግዚአብሔር ጥሪ መንፈሳዊ ዕውርነታቸውን ስለገፈፈው፣ ደግሞም መስቀሉን እንደ ጥበብ እና ኀይል እንዲያዩት ስለሰጣቸው ነው። የማይቋቋሙት ጸጋ ስንል ይህንን ማለታችን ነው።

## በፈቃዳችን ውስጥ የሚሠራ ሥራ

እግዚአብሔር ፈቃዳችንን ሳያስገድድ፣ ፈቃዳችንን ለመለወጥ እንዴት እንደሚሠራ በ2ኛ ቆሮንቶስ 4፥4-6 በሰፊው ተገልጿል።

> “የእግዚአብሔር አምሳል የሆነው የክርስቶስ፣ የክብሩን ወንጌል ብርሃን እንዳያዩ የዚህ ዓለም አምላክ የማያምኑትን ሰዎች ልቡና አሳውሯል። እኛ የምንሰብከው ክርስቶስ ኢየሱስ ጌታ መሆኑን እንጂ ራሳችንን አይደለምና፤ እኛም ራሳችን ስለ ኢየሱስ ስንል የእናንተ አገልጋዮች ሆነናል። በክርስቶስ ፊት እግዚአብሔር የክብሩን ዕውቀት ብርሃን ይሰጠን ዘንድ፣ ‘በጨለማ ብርሃን ይብራ’ ያለው እግዚአብሔር ብርሃኑን በልባችን አብርቷልና።”

ሰዎች ለክርስቶስ ክብር የታወሩ ስለሆኑ፣ ወደ ማየት እንዲመጡና እንዲያምኑ የግድ ተአምር ያስፈልጋቸዋል። ጳውሎስ ይህንን ተአምር እግዚአብሔር በመጀመሪያው የፍጥረት ቀን “ብርሃን ይሁን” ካለው ጋር ያመሳስለዋል። እኛ ሁላችን ከዕውርነት ወደ ማየት፣ ከባርነት ወደ ነጻነት፣ ከሞት ወደ ሕይወት እንዴት እንደመጣን ከሚናገሩ አስደናቂ ዐሳቦች አንዱ፣ “በክርስቶስ ፊት እግዚአብሔር የክብሩን ዕውቀት ብርሃን ይሰጠን ዘንድ፣ ‘በጨለማ ብርሃን ይብራ’

ያለው እግዚአብሔር ብርሃኑን በልባችን አብርቷልና" የሚለው ነው። እውነተኛ የሆነ መንፈሳዊ ብርሃን በልባችን በርቷል። ይህም፣ "በክርስቶስ ፊት የእግዚአብሔር የክብሩ ዕውቀት ብርሃን" ነው (ቊ. 6)። ወይም ደግሞ ቊጥር 4 እንደሚያስቀምጠው፣ "የእግዚአብሔር አምሳል የሆነው የክርስቶስ የክብሩ ወንጌል ብርሃን" ነው።

በሌላ አገላለጽ፣ እግዚአብሔር የክርስቶስን ክብር ማለትም ስለ ራሱ መስካሪ የሆነውን እውነቱን እና ውበቱን በልባችን እንድናየው እና እንድናጣጥመው አደረገ።

ክርስቶስን በተመለከተ ከዚያች ቅጽበት ጀምሮ፣ ፈቃዳችን በመሠረታዊነት ተለወጠ። ይህም ደግሞ በርግጥ ዐዲስ ፍጥረት—ዐዲስም ልደት ነው። ይህም በ፲ኛ ቆሮንቶስ ፲፥24 ላይ ካየነው ውጤታማ ጥሪ ጋር በመሠረታዊነት ተመሳሳይ የሆነ መለኮታዊ ድርጊት ነው፤ "እግዚአብሔር ለጠራቸው ግን፣ …ክርስቶስ የእግዚአብሔር ኀይል፣ የእግዚአብሔርም ጥበብ [እንደሆነ ይታያቸዋል።]" የተጠሩቱ ከእንግዲህ ወዲህ መስቀሉን እንደ እግዚአብሔር ኀይልና ጥበብ እንጂ፣ እንደ ሞኝነት እንዳያዩት ሉዓላዊ እና ፈጣሪ በሆነው በእግዚአብሔር ኀይል ዐይኖቻቸው ተከፍተውላቸዋል። ውጤታማው ጥሪም ዕውርነታችን የተወገደበት ተአምር ነው። እግዚአብሔር፣ የክርስቶስ ክብር ልንቋቋመው በማይቻል ውበት እንዲያበራ ያደርገዋል። ይህ የማይቋቋሙት ጸጋ ነው።

## ጌታ ልቧን ከፈተላት

ሌላው ምሳሌ ደግሞ በሐዋ. ፲6፥፲4 ላይ፣ ልድያ የሐዋርያው ጳውሎስን ስብከት በምትሰማበት ስፍራ ይገኛል። ሉቃስ እንዲህ ይላል፣ "ጌታም፣ ጳውሎስ የሚናገረውን በማስተዋል ትሰማ ዘንድ፣ ልቧን ከፈተላት።" እግዚአብሔር ልባችንን ካልከፈተው በስተቀር፣ በወንጌሉ መልእክት ውስጥ ያለውን የክርስቶስ እውነት እና ውበት በፍጹም አንሰማም። እንግዲህ ይህን የልብ መከፈት ነው እኛ የማይቋቋሙት ጸጋ የምንለው። የማይቋቋሙት ጸጋ፣ ለምሥራቹ ዜና ውበት ያለንን የዕውርነት እና ለዜናው መልካምነት ያለንን የደንቈሮነት ፈቃዳዊ መቋቋም ይረታዋል።

ይህንን ለመግለጽ ሌላው መንገድ “ዐዲስ ልደት” ወይም ዳግመኛ መወለድ ነው። ዐዲስ ልደት፣ አስቀድሞ “ሙት” የነበረ ሰው ክርስቶስን መቀበል እና መዳን የሚያስችለው ተአምራዊ የእግዚአብሔር ሥራ ነው። ይህን ዐዲስ ልደት በራሳችን እምነት ልናመጣው አንችልም፤ ነገር ግን እግዚአብሔር በዐዲስ ልደት እምነታችንን ያመጣዋል።

ሐዋርያው ዮሐንስ በ1ኛ ዮሐንስ 5፥1 ላይ ይህን ተዛምዶ የገለጸበትን መንገድ አስተውሉ፤ “ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ እንደሆነ የሚያምን ሁሉ ከእግዚአብሔር ተወልዶአል።” ይህም ማለት ከእግዚአብሔር መወለድ ቀዳሚ፣ ማመን ደግሞ ተከታይ ነው ማለት ነው። በኢየሱስ ማመናችን ዳግም የመወለዳችን ምክንያት አይደለም፤ ይልቁንም “ከእግዚአብሔር የተወለድን” ለመሆናችን ማረጋገጫው ነው።

## ዐዲስ ልደት፤ የሉዓላዊ ፍጥረት ግብር

ይህንን ለማረጋገጥ፣ ክርስቶስን መቀበላችን ከእግዚአብሔር ከመወለዳችን ጋር እንዴት እንደሚዛመድ ከዮሐንስ ወንጌል እንመልከት። “ለተቀበሉትና በስሙ ላመኑት ሁሉ ግን የእግዚአብሔር ልጆች የመሆን መብት ሰጣቸው። እነዚህም ከእግዚአብሔር ተወለዱ እንጂ ከደም ወይም ከሥጋ ፈቃድ ወይም ከወንድ ፈቃድ አልተወለዱም።” (ዮሐንስ 1፥12-13)። ስለዚህ ዮሐንስ፣ እግዚአብሔር ክርስቶስን ለሚቀበሉ ሁሉ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው ይለናል (ቁ. 12)። በመቀጠልም እነዚያ ክርስቶስን የሚቀበሉት፣ “ከእግዚአብሔር ተወለዱ እንጂ፣ ከደም ወይም ከሥጋ ፈቃድ ወይም ከወንድ ፈቃድ አልተወለዱም” ይለናል። በሌላ አገላለጽ፣ የእግዚአብሔር ልጅ ለመሆን ክርስቶስን መቀበሉ ወሳኝ ነገር ነው፤ ነገር ግን አንድን ሰው ወደ እግዚአብሔር ቤተሰብ የሚያመጣው ውልደት በሰው ፈቃድ በፍጹም የሚቻል አይደለም። እግዚአብሔር ብቻ ነው ማድረግ የሚችለው።

ሰው በበደሎች እና በኀጢአቶች የሞተ ነው (ኤፌሶን 2፥1)። ራሱን ዐዲስ ማድረግ ሆነ ዐዲስን ሕይወት በውስጡ ሊፈጥር አይችልም። የግድ ከእግዚአብሔር መወለድ አለበት። በመቀጠልም የእግዚአብሔር በሆነው ዐዲሱ ተፈጥሮው፣ ክርስቶስ በርግጥ ማን እንደሆነ ያየዋል፤ ደግሞም ከሆነው ሁሉ ጋር ክርስቶስን

በነጻነት ይቀበለዋል። ሁለቱ ድርጊቶች (ዐዲስ ልደትና እና እምነት) በተመክሮ ደረጃ መለየት እስከማንችል ድረስ እጅግ የተጋመዱ ናቸው። እግዚአብሔር ዐዲስ አድርጎ ወለደን፤ ዐዲስ ለተወለደው ልጅ የመጀመሪያው የሕይወቱ ብልጭታ እምነት ነው። ዐዲስ ልደት የማይቋቋሙት ጸጋ ውጤት ነው፤ ምክንያቱም ዐዲስ ልደት "ከሰው ሳይሆን ከእግዚአብሔር ፈቃድ የሆነ" የሉዓላዊ ፍጥረት ሥራ ነው።

ይህ ግርማዊው የዳግም ልደት እውነት እና በእንዴት መከሰቱ እጅግ የሚደንቅ ነው፤ እኔም ይህን በተመለከተ "Finally Alive, What Happens When We Are Born Again." (በስተመጨረሻ ሕያው፤ ዳግም ስንወለድ ምን ይከሰታል) የሚል ሙሉ መጽሐፍ ጽፌአለሁ። ወደ ማይቋቋሙት ጸጋ ድንቆች በጥልቀት መሄድ ከፈለጋችሁ፣ ያ መጽሐፍ መሄድ ያለባችሁ ጥሩ ስፍራ ሊሆን ይችላል።

ይህን ምዕራፍ ስንጀምር፣ ለውጣችንን (መለወጣችንን) በመከሰት ረገድ፣ የእግዚአብሔር ጸጋ እጅግ ወሳኝ መሆኑን ብዙ ክርስቲያኖች በማስተዋል ያውቁታል ብለናል። ወንጌሉን የተቋቋሙትን ተመልከተን፣ በመንቀጥቀጥ፣ "ያመንኩት ከእግዚአብሔር ጸጋ የተነሣ ነው" ብለናል። አሁን በምዕራፉ መጨረሻ ይህ ለምን እንደሆነ ግልጽ ነው ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ። እግዚአብሔር መቋቋማችንን በርግጥ አሸንፏል። በርግጥ ወደ ራሱ ስቦናል። በርግጥ ንስሓን ሰጥቶናል። በርግጥም ዳግም እንድንወለድ አድርጎናል፤ በዚህም ምክንያት ክርስቶስን ተቀብለናል። የክርስቶስ የክብሩን ብርሃን ይሰጠን ዘንድ፣ በርግጥ እርሱ በልባችን አብርቷል። እንደ አልዓዛር እኛንም ከሞት ወደ ሕይወት በርግጥ ጠርቶናል። እውነተኛ ክርስቲያኖች ሁሉ፣ እነዚህን ነገሮች ከመማራችን በፊት እንኳ፣ እኛን ወደ ክርስቶስ በማምጣት ረገድ፣ ጸጋ እጅግ ወሳኝ እንደሆነ በልቦናቸው ማወቃችን የሚደንቅ አይደለም።

ብዙ ጊዜ ለእውነት፣ ከጭንቅላት ይልቅ ልብ ይቀድማል። የማይቋቋሙትን ጸጋ በተመለከተ ለብዙ ክርስቲያኖች ይህ እውነት ነው። አሁን ግን ይህን እውነት ከእግዚአብሔር ቃል ለራሳችን አይተነዋል። ከዚህ የተነሣ በእግዚአብሔር ጸጋ ልምምዳችሁ እጅግ ጠልቃችሁ እንድትሄዱ ጸሎቴ ነው። ከድሮው በላይ

እግዚአብሔርን እንድታመልኩ እና ሰውንም እንድታፈቅሩ ነው። የሉዓላዊው ጸጋ ጥልቅ ልምምድ የሚያደርገው ይህን ነው።

# ውሱን ቤዝዎት

ቤዝዎት፣ እግዚአብሔር ፍጹም የሆነን የጽድቅ ሕይወት ሥራን የፈጸመበት፣ የኀጢአታችንን ዕዳ የሰረዘበት፣ በእኛ ላይ የነበረውን የራሱን ቍጣ ያበረደበት እና የድነትን ትሩፋት ሁሉ ለእኛ ያሸነፈበት፣ በክርስቶስ በመስቀል ላይ የሠራው ታላቅ ሥራው ነው። የክርስቶስ ሞት የግድ አስፈላጊ ነበር፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር ኀጢአትን ያለ ምንም ክፍያ በመሸፈኛ ውስጥ የሚተወው ቢሆን ኖሮ፣ ለክብሩ ያለውን ትክክለኛ ስፍራ ባላሳየ ነበር። የሮሜ 3፥25-26 ዐሳብም ይኸው ነው፣

> *"በደሙም በሆነው እምነት፣ እግዚአብሔር የማስተስሪያ መሥዋዕት አድርጎ አቅርቦታል፤ ይህንም ያደረገው ቀድሞ የተፈጸመውን ኀጢአት ሳይቀጣ በትዕግሥት በማለፍ ጽድቁን ለማሳየት ነው፤ በአሁኑ ዘመን ይህን ያደረገው፣ ጽድቁን ይኸውም እርሱ ራሱ ጻድቅ ሆኖ፣ በኢየሱስ የሚያምነውን የሚያጸድቅ መሆኑን፣ ለማሳየት ነው።"*

ኀጥኡን በእምነት በማጽደቁ የእግዚአብሔር ጽድቅ ይረጋገጥ ዘንድ፣ የክርስቶስ ሞት የግድ አስፈላጊ የነበረ መሆኑን ከላይ አንክሮ በተሰጠባቸው ቃላት መመልከት ትችላላችሁ። ግን ለምን? ምክንያቱም ኀጢአት በእግዚአብሔር ክብር ላይ የሚደረግ ዘለፋ ሆኖ ሳለ፣ ኀጢአተኞችን ኀጢአታቸው ምንም እንዳልሆነ በማሰብ፣ በነጻ መልቀቁ ዐመፃ ይሆን ስለነበር ነው። ደግሞም የእግዚአብሔር ክብር ልኬት ወሰን አልባ ስለሆነ፣ የተደረገውም ዐመፃ በዚያው መጠን እጅግ የከፋ ነው። ስለዚህም እኛ እንድንጸድቅ እና የእግዚአብሔርም ጽድቅ እንዲረጋገጥ፣ ኢየሱስ በእኛ በደል ምክንያት የመጣውን ርግማን ተሸከመ።

## በርግጥ ክርስቶስ ምን አሳካ?

"ውሱን ቤዝዎት" የሚለው ስያሜ፣ "ክርስቶስ ይህንን ሁሉ ያደረገው ለማን ነው?"፣ "እርሱ የሞተውስ ለማን ነው?"፣ "ያስተሰረየውስ የማንን ኀጢአት ነው?"፣ "የድነትን ትሩፋትስ የገዛው ለማን ነው?" የሚሉ ጥያቄዎችን የሚመልስ ነው።

ሆኖም ግን ከእነዚህ የቤዝዎቱ *ሰፋት* ጥያቄዎች ኋላ በእኩል ደረጃ አስፈላጊ የሆነ የቤዝዎቱ “ምንነት” ጥያቄ ይገኛል። በርግጥ ክርስቶስ ለሞተላቸው ለእነዚያ ሰዎች ያከናወነው ነገር ምንድን ነው? ይህ ጥያቄ ለሌሎቹም ጥያቄዎች ትክክለኛ ወደሆነ መልስ ይመራናል።

ክርስቶስ ለሁሉም ሰው *በተመሳሳይ መንገድ* ሞቷል የምትሉ ከሆነ፣ ክርስቶስ አሁን እርሱን ለሚያምኑ ሰዎች *በልዩ መንገድ* እንደሞተላቸው ብታምኑ ከምትሰጡት የቤዝዎቱን ምንነት ፍቺ፣ ፍጹም በተለየ መንገድ መፍታት አለባችሁ። እንደ መጀመሪያው ዐሳብ ከሆነ፣ የክርስቶስ ሞት የማንንም ድነት *በወሳኝነት ኢያረጋግጥም፤* ይልቁንስ እነርሱን በማዳን ረገድ ሌላ ነገር (ማለትም የራሳቸው ምርጫ) ወሳኝ ይሆን ዘንድ ሁሉንም ሰዎች ሊድኑ የሚችሉ ያደርጋቸዋል። ይህ እንዲህ ከሆነ ደግሞ፣ የክርስቶስ ሞት የማንንም የሞት ቅጣት በተግባር አላስወገደም፤ ደግሞም ዐዲስን ሕይወት ለማንም አላረጋገጠም ማለት ነው። ይልቁን ድነትን ሊከስት የሚችልን የራሳቸውን ወሳኝ መንስኤ (ማለትም የራሳቸውን እምነት) በሚያቀርቡ ሰዎች እውን ሊሆን የሚችልን የድነት ምናልባታዊነትን ፈጠረ። በዚህኛው የቤዝዎት አረዳድ፣ እምነትና ንስሓ ለተወሰኑ ኀጢአተኞች በክርስቶስ ደም የተገዙ የእግዚአብሔር ስጦታዎች አይደሉም፤ ነገር ግን የክርስቶስን ደም ለእነርሱ እንዲሠራ የሚያደርጉ የአንዳንድ ኀጢአተኞች ድርጊቶች ናቸው።

ይህ የቤዝዎት አስተምህሮ፣ አስቀድመን ካየነው ከማይቋቋሙት ጸጋ ጋር በእጅጉ የተቈራኘ መሆኑን ተመልከት። መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚያስተምር የማስበው፣ ይህ የማይቋቋሙት ጸጋ ራሱ በኢየሱስ ደም የተገዛ መሆኑን ነው። ዐዲሱ ልደት በደም የተገዛ ነው። ውጤታማው ጥሪ በደም የተገዛ ነው። የንስሓ ስጦታ በደም የተገዛ ነው። ከእነዚህ የማይቋቋሙት ጸጋ ድርጊቶች አንዳቸውም የተገቡን አይደሉም። ወደ እኛ የመጡትም ክርስቶስ በደሙ እና በጽድቁ ስላረጋገጠልን ነው። ይህ ማለት እርሱ ለሁሉም በተመሳሳይ መንገድ አላረጋገጠም ማለት ነው። እንዲህ ባይሆንማ ሁሉም ሰው ዳግመኛ በተወለደ ነበር፤ ደግሞም ሁሉም ሰው በውጤታማው ጥሪ በተጠራ እና የንስሓንም ስጦታ በተቀበለ ነበር።

ስለዚህ፣ በዚህ ምዕራፍ ጅማሬ የሚገጥሙን ግላዊና ተመክሮአዊ ጥያቄዎች እነዚህ ናቸው፤ ክርስቶስ አሁን ያሉኝን ማለትም ጥሪን፣ ሕይወትን፣ እምነትን እና ንስሓን በትክክል እንዳረጋገጠልኝ አምናለሁ? ወይስ ደግሞ እርሱ በሞቱ ያስገኘልኝ ነገሮች ለእኔ እንዲቆጠሩ የራሴን አስተዋጽኦ አድርጌአለሁ? ክርስቶስ ለሁሉም ሰው በተመሳሳይ መንገድ የሞተ ቢሆን፣ የእርሱ ሞት ለዳኑ ሰዎች የዳግም ልደት ጸጋን፣ እምነትን እና ንስሓን ፍጹም በሆነ ሁኔታ ባላስገኘ ነበር። በደም ከተገዛው የክርስቶስ ተአምር ውጭ ራሳችንን ሕያው እንድናደርግ ግድ በሆነብን ነበር፤ ደግሞም በደም ከተገዛው የእምነትና የንስሓ ስጦታ ውጪ በራሳችን ወደ እምነትና ንስሓ እንድንመጣ ግድ በሆነብን ነበር።

በሌላ አገላለጽ፣ ክርስቶስ ለሁሉም ሰው በተመሳሳይ መንገድ እንደሞተ የምናምን ከሆነ፣ የመስቀሉ ትሩፋት እኛ ወደ እምነት የመጣንበትን ምሕረት ሊያካትት አይችልም። ምክንያቱም እንደዛ ቢሆን ሁሉም ሰው ወደ እምነት በመጣ ነበር፤ ነገር ግን ሁሉ ሰው አልመጣም። እኛ ወደ እምነት የመጣንበት ምሕረት ማለትም የማይቋቋሙት ጸጋ፣ ክርስቶስ በመስቀሉ ከገዛቸው ትሩፋት መካከል ካልሆነ፣ እኛ ከሞታችን እና ከዕውርነታችን ደግሞ ከዐመፀኝነታችን መዳንን በራሳችን በሌላ መንገድ እንድናገኝ ተትተናል ማለት ነው። ክርስቶስ ሲሞት ይህን መግቢያ (ዐዲስ ልደት፣ እምነት እና ንስሓ) ካላስገኘልን፣ በክርስቶስ ወዳለው ድኅነት በሌላ መንገድ እንድንደርስ ተትተናል ማለት ነው።

## በርግጥ ቤዝዎቱን ውስን የሚያደርገው ማነው?

ስለዚህ ቤዝዎቱን የሚገድቡት ካልቪናውያን እንዳልሆኑ ግልጽ ይሆናል። ይልቁንስ ቤዝዎቱን ውስን የሚያደርጉት፣ እኛ እጅጉን የሚያስፈልገንን ማለትም ከሙትነት፣ ከድንዳኔ እና በእግዚአብሔር ቊጣ ሥር ሆነን ከመታወር መዳንን፣ የክርስቶስ ሞት በፍጹም እንዳጠናቀቀው የሚክዱት ናቸው። እነርሱ የቤዝዎቱን ዐቅም እና ውጤታማነት ውስን ያደርጉታል፤ ስለዚህም ቤዝዎቱ ባለማመን ለሞቱት እና ለተኮነኑትም ጭምር የተፈጸመ ነው ማለት ይችላሉ። ክርስቶስ ለሁሉም ሰዎች በተመሳሳይ መንገድ ሞቷል ለማለት፣ የወደቁ ሰዎች ከመስቀሉ ባልሆነ መንገድ ከምውትነታቸው እና ዐመፀኝነታቸው መውጣት ደግሞም እምነትን በውጤታማነት ማግኘት ይችላሉ በማለት ቤዝዎቱን ወደ ድነት ዕድልነት ወይም ምናልባትነት የግድ ውስን ማድረግ አለባቸው።

በሌላ በኩል፣ እኛ የቤዝዎቱን ዐቅም እና ውጤታማነት ውስን አናደርገውም። ይልቁን እኛ የምንለው፣ በመስቀሉ ላይ እግዚአብሔር ይመለከት የነበረው የእርሱን ልጆች ከሚያጠፋቸው ነገር ሁሉ፣ ከራሳቸው አለማመን ጭምር በተግባራዊነት እና በውጤታማነት ሲቤዣቸው ነው። ደግሞም ክርስቶስ ለሙሽሪት በልዩነት ሲሞትላት፣ የድነትን ዕድል ወይም ምናልባትነትን አይደለም የፈጠረላት፤ ለድነት አስፈላጊ የሆነውን ነገር ሁሉ፣ የዳግም ልደት ጸጋን እና የእምነትን ስጦታ ጭምር በርግጥ እንደገዛላት እና በአስተማማኝነት እንዳስጠበቀላት እናምናለን።

ክርስቶስ በተወሰነ መልኩ ሁሉንም ሰው ለማዳን እንደሞተ አንክድም። ጳውሎስ በ1ኛ ጢሞ. 4፥10 እግዚአብሔር በክርስቶስ፣ “ለሰዎች ሁሉ በተለይም ለሚያምኑት አዳኝ” ነው ይለናል። እኛ የምንክደው የክርስቶስ ሞት ለሁሉም ሰው በተመሳሳይ መልኩ ነው የሚለውን ነው። እግዚአብሔር በተወሰነ መልክ *ሁሉንም* እንዲያድን ክርስቶስን ልኮታል። የሚያምኑትን *በተለየ መልኩ* እንዲያድን ክርስቶስን ልኮታል። የእግዚአብሔር ዐሳብ ለእያንዳንዱ ይለያያል። ይህ የ 1ኛ ጢሞቴዎስ 4፥10 ተፈጥሯዊ አነባብ ነው።

ለ “ሁሉም ሰዎች” የክርስቶስ ሞት የወንጌል ነጻ ግብዣ መሠረት ነው። የዮሐንስ 3፥16 ፍቺም ይህ ነው፣ “በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንዲያ ልጁን እስከ መስጠት ድረስ ዓለምን እንዲሁ ወዶአልና።” የልጁ መላክ *በእርሱ የሚያምን ሁሉ እንዳይጠፋ* እንደሆነ፣ ኢየሱስ ግልጽ ባደረገው መልኩ ለመላው ዓለም ነው። በዚህ ረገድ እግዚአብሔር ኢየሱስን ለእያንዳንዱ ልኳል። ወይም የ 1ኛ ጢሞቴዎስ 4፥10ን ቃል ለመጠቀም፣ ክርስቶስ የሚያምኑበት በሙሉ ያለ አንዳች መገለል እንዲድኑ፣ ፍጹም አስተማማኝ እና ትክክለኛ የሆነ የንስሓ ጥሪ ለሁሉም ሰው ይደረግ ዘንድ በመሞቱ እግዚአብሔር “የሰዎች ሁሉ አዳኝ” ነው።

ወንጌል ሲሰበክ ክርስቶስ ያለ አንዳች ልዩነት ለሁሉም ይቀርባል። ይህም ለሁሉም ፍጹም እውነተኛ የሆነ ግብዣ ነው። እንዲቀበሉት በግብዣ የቀረበው ክርስቶስ ነው፤ ስለዚህም ክርስቶስን የተቀበለ ማንም ይሁን ማን እርሱ ለበጎቹ፣ ለሙሽሪት የገዛውን ሁሉ ይቀበላል። ወንጌሉ ድነትን *ሊሆን የሚችል* አድርጎ አያቀርብም።

ወንጌሉ የድነት መቻል(possibility) ነው፤ ነገር ግን በግብዣ የሚቀርበው ክርስቶስ ነው። በእርሱም በኩል በሞቱ እና በትንሣኤው ለራሱ ሰዎች የፈጸማቸው ወሰን አልባ ክንውኖቹ ናቸው።

## የዐዲሱ ኪዳን ወሳኝ ሚና[7]

ክርስቶስ የሞተው ለሚያምኑ ሁሉ ድነትን የሚቻል ለማድረግ ሳይሆን፣ የምርጦቹን እምነት በርግጥ ሊገዛ ነው ለማለታችን መጽሐፍ ቅዱሳዊው መሠረት፣ የኢየሱስ ደም የዐዲሱን ኪዳን በረከቶች ለራሱ ሕዝብ ያስጠበቀ በመሆኑ ነው። እግዚአብሔር የመረጣቸው እና የጠራቸው ሰዎች እምነት በ "ኪዳን ደም" የተገዛ ነው (ማቴዎስ 26፥28)።

የአርሚኒያኖች አመለካከት ኀጢአተኞች ያምኑ ዘንድ መለኮታዊ እገዛ እንደሚያስፈልጋቸው ያቀርባል። ደግሞም እውነት ነው። እገዛ ያስፈልገናል፤ ነገር ግን አርሚኒያኒዝም ከሚያስበው የበለጠ እገዛ ነው የሚያስፈልገን። በዚያ አመለካከት፣ ኀጢአተኛው በእግዚአብሔር ከታገዘ በኋላ ወሳኝ የሆነን ኀይል (impulse) ከራሱ ያቀርባል። እግዚአብሔር ማገዝን ብቻ ያግዛል፤ ኀጢአተኛው ደግሞ ይወስናል። እንዲህ ከሆነ፣ "የኪዳኑ ደም" እምነታችንን በወሳኝነት አያስጠብቀውም። ወሳኙ የእምነት መንስኤ፣ የሰው ግለ ውሳኔ ነው። የክርስቶስ ቤዛዎታዊ ሥራ ይህንን ዕድል ያመቻቻል እንጂ የመጨረሻውን ውጤት አያስጠብቀውም ይላሉ። ነገር ግን በክርስቶስ ደም የተገዛው ዐዲሱ ኪዳን ከዚህ በጣም የተለየ ነገር ያስተምረናል። የዐዲሱን ኪዳን ትምህርት በፊታችን እናኑረው።

---

[7] የሚከተለው ሙግት ይበልጥ በሙላት የደረጀው በጆን ፓይፐር በተጻፈው፥ ["My Glory I will not give to another preaching the fullness of definite atonement for the Glory of God." In David and Jonathan Gibson, Eds, From Heaven He came and sought her; definite atonement in historical, biblical, theological and pastoral perspective (wheaton, Illinois፥ crossway, 2013).]

እግዚአብሔር የዐዲሱን ኪዳን ቃሎች በኤርምያስ በኩል እንዲህ ተናግሯል፤

> “ከእስራኤል ቤትና ከይሁዳ ቤት ጋር” ይላል እግዚአብሔር፤ “ዐዲስ ቃል ኪዳን የምገባበት፣ ጊዜ ይመጣል። ... ከአባቶቻቸው ጋር እንደገባሁት ኪዳን አይደለም፤ የእነርሱ ባል ሆኜ ሳለሁ፣ ቃል ኪዳኔን አፍርሰዋልና። ” ይላል እግዚአብሔር። “ነገር ግን ከዚያ ጊዜ በኋላ፣ ከእስራኤል ቤት ጋር የምገባው ኪዳን ይህ ነው” ይላል እግዚአብሔር፤ ሕጌን በልቡናቸው አኖራለሁ፤ በልባቸውም እጽፈዋለሁ። ...“በደላቸውን ይቅር እላለሁ፤ ኀጢአታቸውንም መልሼ አላስብም” (ኤር. 31፥31-34)።

ቃል በተገባው ዐዲስ ኪዳን እና “ከአባቶቻቸው ጋር በተገባው” አሮጌው ኪዳን መካከል ያለው መሠረታዊ ልዩነት፣ እነርሱ አሮጌውን ኪዳን አፍርሰዋል፤ ነገር ግን በዐዲሱ ኪዳን እግዚአብሔር፣ “ሕጉን በውስጣቸው ያኖረዋል” ደግሞም፣ “በልባቸው ይጽፈዋል” ይህም የሆነው የኪዳኑ ትእዛዛት በእግዚአብሔር ሉዓላዊ ተነሣሽነት እንዲጠበቁ ነው። ዐዲሱ ኪዳን አይፈርስም። ይህም የንድፉ አንድ አካል ነው። ኪዳኑ አባላቱን የራሱ ያደርጋቸዋል፤ ደግሞም ይጠብቃቸዋል።

እግዚአብሔር ይህንን ነጥብ በቀጣዩ የኤርምያስ ምዕራፍ ላይ ይበልጥ ግልጽ ያደርገዋል፤

> “ለእነርሱና ከእነርሱም በኋላ ለልጆቻቸው መልካም እንዲሆንላቸው ዘወትር ይፈሩኝ ዘንድ፣ አንድ ልብ አንድም ዐሳብ እሰጣቸዋለሁ። መልካምን ነገር ለእነርሱ ከማድረግ እንዳልቆጠብና ከእኔም ፈቀቅ እንዳይሉ መፈራቴን በውስጣቸው ላኖር ከእነርሱ ጋር የዘላለም ቃል ኪዳን እገባለሁ። ለእነርሱ መልካም በማድረግ ደስ ይለኛል” (ኤር. 32፥39-41)።

በዚህ ክፍል ቢያንስ ስድስት ያህል የተሰፋ ቃሎችን እግዚአብሔር ሰጥቷል፤ 1) ከእነርሱ ጋር የዘላለም ቃል ኪዳን እገባለሁ፤ 2) ዘወትር እኔን እንዲፈሩኝ የሚያደርግ ልብን እሰጣቸዋለሁ፤ 3) መልካምን ነገር ለእነርሱ ከማድረግ አልቆጠብም፤ 4) መፈራቴን በልባቸው አስቀምጣለሁ፤ 5) ከእኔ ፈቀቅ እንዲሉ አልተዋቸውም፤ እና 6) ለእነርሱ መልካም በማድረግ ደስ ይለኛል።

የኪዳኑን ስኬታማነት ለማረጋገጥ፣ እግዚአብሔር ሉዓላዊውን ተነሣሽነት እየወሰደ መሆኑ፣ ከኤርምያስ 31 ይልቅ፣ እዚህ ኤርሚያስ 32 ላይ በይበልጥ ግልጽ ነው። እግዚአብሔር የዐዲሱን ኪዳን አባልነት ማግኘት እና ማጽናት፣ በወደቁ ሰዎች የፈቃድ ኀይል እንዲወሰን በፍጹም አይተወውም። ዐዲስን ልብ ማለትም እግዚአብሔርን የሚፈራ ልብ ይሰጣቸዋል። ይህም በወሳኝነት የእግዚአብሔር ሥራ እንጂ የሰው አይሆንም። ደግሞም በዚህ ኪዳን ውስጥ የሚያደርገው እነርሱ "ከእኔም ፈቀቅ እንዳይሉ" ነው (ኤር. 32፥40)። ጆን ኦውን ዐሳቡን እንዲህ ሰጥቷል፣ "የእነዚህ የሁለቱ ኪዳናት መሠረታዊ ልዩነት ይህ ነው፤ እግዚአብሔር በአሮጌው ኪዳን የሚፈልገው የኪዳኑን ትእዛዛት እንዲጠብቁ ብቻ ነው፤ አሁን በዐዲሱ ኪዳን ግን፣ ይህ ኪዳን በሚያካትታቸው አባላት ሁሉ የትእዛዙን መጠበቅም ራሱ ይከስትላቸዋል።"[8]

ራሱ እግዚአብሔር ተነሣሽነትን እንደሚወስድ እና ዐዲስን ልብ ደግሞም ዐዲስን መንፈስ እንደሚሰጣቸው፣ ሕዝቅኤልም በተመሳሳይ መንገድ ትንቢትን ተናግሯል።

> "የማያወላውል ልብ እሰጣቸዋለሁ፤ ዐዲስ መንፈስ በውስጣቸው አኖራለሁ፤ ድንጋዩን ልብ ከውስጣቸው አወጣለሁ፤ ሥጋ ልብም እሰጣቸዋለሁ።" (ሕዝ. 11፥19)
>
> "ዐዲስ ልብ እሰጣችኋለሁ፤ ዐዲስ መንፈስም በውስጣችሁ አሳድራለሁ፤ የድንጋይ ልባችሁን ከእናንተ አስወግዳለሁ፤ የሥጋንም ልብ እሰጣችኋለሁ። መንፈሴን በውስጣችሁ አሳድራለሁ፤ ሥርዐቴን እንድትከተሉና ሕጌን በጥንቃቄ እንድትጠብቁ አደርጋለሁ።" (ሕዝ. 36፥26-27)

---

[8] John Owen, The Death of Death in the Death of Christ, in The Works of John Owen, ed. W. H. Goold, 16 vols. (Edinburgh: The Banner of Truth Trust, 1967 [1850-1853]), 10:237.

እስራኤል የእግዚአብሔርን ተስፋ ቃሎች ያለማመናቸው ወይም እርሱን በፍጹም ልባቸው፣ በፍጹም ነፍሳቸው፣ በፍጹም ዐሳባቸውና በፍጹም ኀይላቸው ያለመውደዳቸው ዋነኛው ምክንያት፣ ዳግም ያልተወለደ የድንጋይ ልብ ነው። ዐዲሱ ኪዳን ከአሮጌው ኪዳን ይልቅ የተሳካ እንዲሆን፣ እግዚአብሔር ከራሱ ሕዝብ የድንጋይን ልብ አውጥቶ እርሱን የሚወድ ዐዲስን ልብ ሊሰጣቸው ይገባል። ይህም ማለት በሌላ አገላለጽ፣ እግዚአብሔር የሕዝቡን እምነት እና ፍቅር ለማስጠበቅ ተአምራዊ የሆነ ተነሣሽነትን መውሰድ አለበት። እግዚአብሔር ያደርገዋል ብሎ ሙሴ የተናገረው በርግጥም ይኸው ነው፤

> “አምላክህን እግዚአብሔርን በፍጹም ልብህና በፍጹም ነፍስህ እንድትወደው፣ በሕይወትም እንድትኖር፣ አምላክህ እግዚአብሔር የአንተንና የዘርህን ልብ ይገርዛል።” (ዘዳ. 30፥6)

በሌላ አገላለጽ፣ እግዚአብሔር በዐዲሱ ኪዳን ተነሣሽነትን ራሱ እንደሚወስድ እና ዐዲስን ልብ እንደሚፈጥር ቃል ገብቷል፤ ስለዚህም በራሳቸው ሳይሆን በእግዚአብሔር ቀስቃሽነት፣ ሰዎች የኪዳኑ አባላት ይሆናሉ። ማንም ከነትሩፋቱ ሁሉ ጋር በዐዲስ ኪዳን መካፈልን ካገኘ፣ ይህ የሆነው እግዚአብሔር ኀጢአቱን ይቅር በማለቱ፣ የድንጋይንም ልብ በማስወገዱ፣ እግዚአብሔርንም የሚፈራና የሚወድ ሩኅሩኅ የሥጋን ልብ በመስጠቱ እና በሕጎቹ እንዲራመድ በማድረጉ ምክንያት ነው። በሌላ አገላለጽ፣ ዐዲሱ ኪዳን የዳግም ልደትን ተስፋ ሰጥቷል። አስቀድሞ ድንዳኔ ብቻ ባለበት ቦታ፣ እምነትን እና ፍቅርን ደግሞም መታዘዝን እንደሚፈጥር ቃል ገብቷል።

## የኢየሱስ ደም የዐዲሱን ኪዳን የተስፋ ቃሎች አስገኝቷል

ወደ ዐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ስንመለስም የምናገኘው፣ ይኸው ኢየሱስ የዚህ ዐዲስ ኪዳን መካከለኛ መሆኑን እና ኪዳኑንም በገዛ ደሙ ያስጠበቀ መሆኑን ነው። ይህም የቤዝዎቱ እና የዐዲሱ ኪዳን ግንኙነት ነው፤ የኢየሱስ ደም የኪዳኑ ደም ነው። የክርስቶስ ሞት ዐላማ እስከ አሁን ካየናቸው ቃሎች ሁሉ ጋር ይህን ኪዳን መመሥረት ነበረ።

በሉቃስ 22፥20 መሠረት፣ የመጨረሻውን እራት ከበሉም በኋላ ኢየሱስ ጽዋውን አንሥቶ እንዲህ አለ፣ “ይህ ጽዋ ስለ እናንተ በሚፈሰው ደሜ የሚመሠረት ዐዲስ ኪዳን ነው።” ጳውሎስም በ1ኛ ቆሮንቶስ 11፥25 ይህንኑ ያስታውሰናል፣ “እንዲሁም ከእራት በኋላ ጽዋውን አንሥቶ፣ ይህ ጽዋ በደሜ የሚሆን ዐዲስ ኪዳን ነው፤” ይህንንም የምወስደው የዐዲሱ ኪዳን ተስፋ ቃሎች ሁሉ በክርስቶስ ደም የተገዙ ናቸው ማለት እንደሆነ ነው። ወይም የዕብራዊያንን ቃል በመጠቀም፤ “ከዚህ መሓላ የተነሣ፣ ኢየሱስ ለተሻለ ኪዳን ዋስ ሆኗል” (ዕብ. 7፥22)። “ስለዚህም የተጠሩት፣ ተስፋ የተሰጠውን የዘላለም ርስት እንዲቀበሉ፣ ክርስቶስ የዐዲስ ኪዳን መካከለኛ ነው” (ዕብ. 9፥15)።

ስለዚህም፣ ሁሉም የዐዲሱ ኪዳን የተስፋ ቃሎች በደም የተገዙ ናቸው። እነርሱም ለእኛ እውን ሲሆኑ፣ እውን የሆኑበት ምክንያት፣ እውን እንዲሆኑ ኢየሱስ ስለሞተ ነው። ይህም ማለት የዐዲስ ኪዳን ልዩ የተስፋ ቃሎች፣ የእግዚአብሔር የሆነን ሕዝብ ለመፍጠር እና ለመጠበቅ ኢየሱስ የሞተላቸው ዐላሞች ናቸው።

እያደራጀሁ ያለሁት ዋናው ነጥብ፣ ሁሉም የዐዲስ ኪዳን የተስፋ ቃሎች በእምነት ሁኔታ ላይ እንደሚደገፉ አይደለም። ይልቁንም በዐዲስ ኪዳን ከተገቡት የተስፋ ቃሎች አንዱ፣ እምነት ራሱ በእግዚአብሔር እንደሚሰጥ ነው። የዐዲሱ ኪዳን ሰዎች የሚፈጠሩትም ሆነ የሚጠበቁት በእግዚአብሔር ነው የምለው ለዚህም ነው። “ከእኔም ፈቀቅ እንዳይሉ መፈራቴን በውስጣቸው ላኖር ከእነርሱ ጋር የዘላለም ቃል ኪዳን እገባለሁ” (ኤር. 32፥40)። በመጀመርያ እግዚአብሔር፣ ፈሪሀ እግዚአብሔርን በውስጣችን ያኖራል። ደግሞም ከእርሱ ፈቀቅ ከማለት ይጠብቀናል። የራሱ የሆነን ዐዲስ ሕዝብ ይፈጥራል ደግሞም ይጠብቃል። ይህንንም በሉቃስ 22፥20 ላይ ኢየሱስ የራሱ ደም እንደሆነ ባለው በኪዳኑ ደም ያደርገዋል።

የዚህ የዐዲሱ ኪዳን መረዳት ማሳረጊያው፣ ለዐዲሱ ኪዳን ሰዎች የተረጋገጠ ቤዝዎት አላቸው የሚል ነው። እግዚአብሔር፣ አንዳች ያልተገባቸው የተወሰኑ ኀጢአተኞች ሊጠብቋቸው የሚገቡ ግዴታዎችን፣ በክርስቶስ ሞት አማካይነት በመግዛት እና በማስጠበቅ የራሱ ሕዝብ ያደርጋቸዋል። የኪዳኑ ደም—የክርስቶስ ደም—የእምነትን እና የንስሓን ዐዲስ ልብ ይገዛል ደግሞም ያስጠብቃል። ይህንን

ደግሞ እግዚአብሔር ለሁሉም ሰው አላደረገውም። ያደረገው "ለተወሰኑ" ሰዎች በልዩነት ነው፤ ይኸውም ከራሳቸው በሆነ በአንዳች ነገር አይደለም። ይህንንም ነፍሱን ስለ በጎቹ ባኖረው በታላቁ እረኛ በክርስቶስ በኩል ያደረገው ከሆነ እኛም፣ "ለእርሱ እስከ ዘላለም ድረስ ክብር ይሁን" (ዕብ. 13፥21) እንላለን። ይህም ስኬት የክርስቶስ መስቀል ክብር ትልቁ ክፍል ነው።

## ኢየሱስ ነፍሱን ስለ በጎቹ ያኖራል

እስከ አሁን ያየነውን የሚደግፉ እና የእግዚአብሔር ዐላማ በክርስቶስ ሞት የዐዲሱን ኪዳን ሰዎች በማይቋቋሙት ጸጋው በኩል መሰብሰብን የሚያካትት እንደሆነ፣ የሚያስተምሩ አያሌ የቅዱሳት መጻሕፍት ክፍሎች አሉ።

ለምሳሌ፦ ኢየሱስ በዮሐንስ 10፥15 ላይ፣ "ሕይወቴንም ስለ በጎቼ አሳልፌ እሰጣለሁ" ይላል። ይህም ሕይወቴን ስለ ሰዎች ሁሉ እሰጣለሁ ከማለት ጋር ተመሳሳይ አይደለም። በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ "በጎቹ" ሁሉም ሰዎች አይደሉም። ወይም ደግሞ "በጎች" የሚለው ቃል እምነትን ለመፍጠር የመወሰን ዐቅማቸውን የሚጠቀሙትን አያመለክትም። ይልቁንስ እነዚህ እግዚአብሔር የመረጣቸው እና ለልጁ የሰጣቸው ናቸው (ዮሐንስ 6፥37፡44)። በጎች ስለሆኑም ማመን ይቻላቸዋል።

ይህንንም በዮሐንስ 10፥26 ኢየሱስ፣ "እናንተ ከበጎቼ ስላልሆናችሁ አታምኑኝም" ባለው ክፍል እንመለከታለን። በሌላ አገላለጽ፣ በግ መሆናችን እንድናምን ያስችለናል፤ ተገላቢጦሹ ግን አይደለም። ስለዚህም በጎች በማመን አይደለም ራሳቸውን በግ የሚያደርጉት፤ እነርሱ አስቀድመውም በጎች ስለሆኑ ማመን የቻሉት። ስለዚህም ኢየሱስ፣ "ሕይወቴን ስለ በጎቼ እሰጣለሁ" በማለቱ፣ አባቴ ለእኔ የሰጣቸውን ሰዎች በደሜ እዋጀዋለሁ ደግሞም እምነታቸውን እና ከእኔ ጋር ኅብረት ላላቸው ሁሉ የሚመጣውን ትሩፋት አስጠብቃለሁ ማለቱ ነው።

ዮሐንስ 17 ወደ ተመሳሳይ አቅጣጫ ይጠቁመናል። በዮሐንስ 17 ኢየሱስ ጸሎቱን አባቱ ለሰጣቸው በጎች ብቻ በማድረግ ይወስነዋል።

> “ለእነዚህ ከዓለም ለሰጠኸኝ ሰዎች ስምህን ገልጬላቸዋለሁ። የአንተ ነበሩ፤ ለእኔ ሰጠኸኝ፤ ... እነርሱ የአንተ ለሆኑት እንጂ ለዓለም አልጸልይም። ... እነርሱ በእውነት የተቀደሱ እንዲሆኑ፣ ራሴን ስለ እነርሱ ቀድሻለሁ።” (ዮሐ. 17፥6፡9፡19)

በዚህ ክፍል የምንመለከተው መቀደስ፣ ኢየሱስ ሊቀበለው ያለ ሞቱ ነው። ስለዚህም የእርሱ ሞት የተዘጋጀው በልዩነት እየጸለየላቸው ላሉት መሆኑን እያለ ነው። “ለሰጠኸኝና የአንተ ለሆኑት እንጂ ለዓለም አልጸልይም” (ዮሐ. 17፥9)። ራሱን የሚቀድሰው ለእነዚህ ነው። ደግሞም ሕይወቱን አሳልፎ የሚሰጠው ለእነዚህ ነው።

## ኢየሱስ የሞተው የእግዚአብሔርን ልጆች ለመሰበሰብ ነው

ዮሐንስ ከሊቀ ካህናቱ የመጣውን፣ ተመሳሳይ ነጥብ የሚናገረውን ትንቢት ይነግረናል።

> “ሕዝቡ ሁሉ ከሚጠፉ ስለ ሕዝቡ አንድ ሰው ቢሞት የሚሻላችሁ መሆኑን አታስተውሉም። ይህን ያለው ከራሱ አልነበረም፤ ነገር ግን በዚያች ዓመት ሊቀ ካህናት እንደ መሆኑ፣ ኢየሱስ ለአይሁድ ሕዝብ እንደሚሞት ትንቢት መናገሩ ነበር፤ ለዚያም ሕዝብ ብቻ ሳይሆን፣ የተበተኑትን የእግዚአብሔርን ልጆች በአንድነት ለመሰብሰብ ነው። ” (ዮሐንስ 11፥50-52)

በዓለም ሁሉ የተበተኑ “የእግዚአብሔር ልጆች” አሉ። እነዚህም አብ ለወልድ የሰጣቸው እና ወደ ኢየሱስም በማይቋቋሙት ሁኔታ የሚስባቸው “በጎቹ” ናቸው። ኢየሱስ የሞተው እነዚህን በጎች ወደ አንድ መንጋ ለመሰብሰብ ነው። ይህ ዐሳብ ከዮሐንስ 10፥15-16 ጋር ተመሳሳይ ነው፣ “ሕይወቴንም ስለ በጎቼ አሳልፌ እሰጣለሁ። ከዚህ ጒረኖ ያልሆኑ ሌሎች በጎች አሉኝ፤ *እነርሱንም ማምጣት አለብኝ።* እነርሱም ድምፄን ይሰማሉ።" የ ዮሐንስ 11፥52 “መሰብሰብ” እና የዮሐንስ 10፥16 “ማምጣት” ተመሳሳይ የእግዚአብሔር *ሥራዎች* ናቸው።

እነዚህ ሁለቱም የክርስቶስ መስቀል መለኮታዊ ዕቅድ ናቸው። ክርስቶስ ይህ እንዲከሰት ለማድረግ እንጂ፣ መከሰት የሚቻል (possible) ለማድረግ አልሞተም።

ይህ ዐሳብ ሰማይ ለክርስቶስ በሚዘምርበት በራእይ 5፥9 ላይ፣ ዳግም በዮሐንስ ተገልጾአል፤ "መጽሐፉን ልትወስድ፣ ማኅተሞቹንም ልትፈታ ይገባሃል፤ ምክንያቱም ታርደሃል፤ በደምህም ከነገድ ሁሉ፣ ከቋንቋ ሁሉ፣ ከሕዝብ ሁሉ ሰዎችን ለእግዚአብሔር ዋጅተሃል።" ከዮሐንስ 10፥16 ጋር በሚስማማ ሁኔታ ዮሐንስ የክርስቶስ ሞት ሰዎችን ሁሉ ዋጅቷል አይልም፤ ነገር ግን ከዓለም ነገዶች ሁሉ ሰዎችን ለራሱ ዋጅቷል ይላል።

ይህም እንደ 1ኛ ዮሐንስ 2፥2 ያሉ ክፍሎችን የምንረዳበት መንገድ ነው፤ በርግጥ አንዳንዶች የውሱን ቤዝዎት አስተምህሮን ለመቃወም ክፍሉን ይጠቀሙታል። ዮሐንስ 11፥52ን በደንብ በሚያስታውሱን ቃላት ዮሐንስ እንዲህ ይላል፣ "[ክርስቶስ] የኀጢአታችን ማስተስሪያ ነው፤ ይኸውም ለዓለም ሁሉ ኀጢአት እንጂ ለእኛ ብቻ አይደለም።" ዋናው ጥያቄ ይህ ነው፤ ይህ ማለት ክርስቶስ የሞተው በዓለም ላለ ለእያንዳንዱ ሰው የእግዚአብሔርን ቊጣ ለማብረድ በማሰብ ነው ማለት ነው? እስከ አሁን ካየናቸው ከዮሐንስ ጽሑፎች፣ እንዲህ ዐይነት ፍቺ ይኖረዋል ማለት የሚቻል ነገር አይደለም። ይልቁንስ በዮሐንስ 11፥52 እና በ 1ዮሐንስ 2፥2 መካከል ያለው ቃላዊ ትይዩነት በጣም የተቀራረበ በመሆኑ፣ በሁለቱ የዮሐንስ ጥቅሶች ውስጥ ተመሳሳይ ነገር የመታሰቡን እውነት ማምለጥ አስቸጋሪ ነው።

> "ኢየሱስ ስለ ሕዝቡ እንደሚሞት ትንቢት ተናገረ፤ ለዚያም ሕዝብ ብቻ ሳይሆን፣ የተበተኑትን የእግዚአብሔርን ልጆች በአንድነት ለመሰብሰብ ነው።" (ዮሐንስ 11፥51-52)

> "እርሱም የኀጢአታችን ማስተስሪያ ነው፤ ይኸውም ለዓለም ሁሉ ኀጢአት እንጂ ለእኛ ብቻ አይደለም።" (1ኛ ዮሐንስ 2፥2)

“ዓለም ሁሉ” የሚለው፣ “የተበተኑ የእግዚአብሔር ልጆች” ከሚለው ጋር ትይዩ ነው። ስለዚህም በ1ኛ ዮሐንስ 2፥2 የዮሐንስ ዐሳብ በክርስቶስ የሆነው የእግዚአብሔር የማስተስሪያ ሥራ በአይሁድ ወይም በአንድ ወገን ወይም ጎሣ ብቻ ያልተገደበ መሆኑን አበክሮ እንደተናገረ ማሰቡ ትክክል ነው። የትኛውም የሰዎች ቡድን፣ “ክርስቶስ ለእኛ ኀጢአት ብቻ ነው ማስተስሪያ የሆነው” ማለት የለበትም፤ በፍጹም ማለት የለበትም። የእርሱ ስርየታዊ ሥራ “ከመላው ዓለም” ሰዎችን ለመሰብሰብ ነው። በመላው ዓለም—“ከዚህ ጒረኖ ያልሆኑ ሌሎች በጎች አሉኝ!” (ዮሐንስ 10፥16)። እነዚህም እርሱ የሞተላቸው “በጎች"፣ የተቤዣቸው ተበትነው ያሉ “የእግዚአብሔር ልጆች”፣ እና “ከነገድ፣ ከቋንቋ፣ ከሕዝብ” የተዋጁ ሰዎች ናቸው።

## ለብዙዎች የሆነ መሥዋዕት

እስከ አሁን ካየነው (ለምሳሌ ራእይ 5፥9፣ “በደምህም ከነገድ ሁሉ፣ ከቋንቋ ሁሉ፣ ከወገን ሁሉ፣ ከሕዝብ ሁሉ ሰዎችን ለእግዚአብሔር ዋጅተሃል”) ከሚለው ጋር በሚስማማ መልኩ ኢየሱስ በ ማር. 10፥45 እንዲህ ብሏል፤ “የሰው ልጅ ሊያገለግልና ሕይወቱን ለብዙዎች ቤዛ አድርጎ ሊሰጥ መጣ እንጂ ሊገለገል አልመጣምና።” ራእ. 5፥9፣ “ከነገድ ሁሉ ዋጅተሃልና” እንደሚለው እዚህም “ለብዙዎች ቤዛ” አለ እንጂ “ለሁሉ ቤዛ” አላለም። “ብዙ” የሚለው ቃል ሙግቴን እንደማያረጋግጥልኝ ዐውቃለሁ። በአመክንዮ “ብዙ” ማለት “ሁሉ” ማለት ሊሆን ይችላል። የእኔ ነጥብ “ብዙ” የሚለው (“ሁሉ” ከሚለው ይልቅ) አስቀድመን በዚህ ምዕራፍ ውስን እንደሆነ ካየነው ጋር የሚገጥም መሆኑን ለማሳየት ነው።

በተመሳሳይ በማቴዎስ 26፥28 የመጨረሻው እራት ላይ ኢየሱስ እንዲህ አላቸው፣ “ስለ ብዙዎች የኀጢአት ይቅርታ የሚፈስ የዐዲስ ኪዳን ደሜ ይህ ነው።” ደግሞም ዕብራውያን 9፥28 እንዲህ ይላል፣ “ክርስቶስ *የብዙ ሰዎችን ኀጢአት* ለመሸከም፣ እንዲሁ አንድ ጊዜ መሥዋዕት ሆኗል፤ ሁለተኛ ጊዜም ይገለጣል፤ ይህም ለሚጠባበቁት ድነትን ለማምጣት እንጂ ኀጢአትን ለመሸከም አይደለም። ” እንዲሁም ኢሳይያስ 53፥12 ላይ *ሥቅዩ* አገልጋይ *“የብዙዎችን* ኀጢአት ተሸከመ” ይለናል።

## ክርስቶስ ራሱን ለቤተ ክርስቲያን ሰጠ

በክርስቶስ ሞት እግዚአብሔር ሊያደርግ ያሰበውን ልዩ ዐሳብ በግልጽ ከሚናገሩ ክፍሎች አንዱ ኤፌሶን 5፥25-27 ነው።

> “ባሎች ሆይ፤ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን እንደ ወደዳትና ራሱንም ስለ እርሷ አሳልፎ እንደ ሰጠ፣ እናንተም ሚስቶቻችሁን ውደዱ፤ በቃሉ አማካይነት በውሃ ዐጥቦ በማንጻት እንድትቀደስ፣ እንዲሁም ጒድፍ ወይም የፊት መጨማደድ ወይም አንዳች እንከን ሳይገኝባት ቅድስትና ነውር አልባ የሆነች ክብርት ቤተ ክርስቲያን አድርጎ ለራሱ ሊያቀርባት ነው።”

ጳውሎስ፣ የክርስቶስ ሞት ተጠቃሚ እንድትሆን የታሰበችው፣ የክርስቶስ ሙሽሪት የሆነችው ቤተ ክርስቲያን ነች ይላል። ለዚህ ለውሱን ቤዝዎት አስተምህሮ ቀናተኛ ከምሆንባቸው ምክንያቶች አንዱ፣ የክርስቶስ ሙሽሪት ክርስቶስ በሞተ ጊዜ፣ ለእርሷ ባለው ልዩ ፍቅር በአግባቡ እንድትመራ፣ በመፈለጌ ነው። ይህም ዓለምን ሁሉ የሚያቅፍ ፍቅር አይደለም፤ ሙሽሪትን የሚዋጅ ፍቅር ነው። እግዚአብሔር የእርሱ የሆኑትን ያውቃል፤ ደግሞም ለልጁ ይህችን ሙሽሪት ለማስገኘት ልጁን ላከ።

> እርሱ ከሰማይ መጣ ደግሞም ዐያት፣
>
> ቅድስት ሙሽሪት እንድትሆንለት፤
>
> በገዛ ደሙ እርሷን ዋጃት፤
>
> ለእርሷ ሕይወት ሲል እርሱ ሞተላት።[9]

[9] Samuel J. Stone, “The Church’s One Foundation”, (http://www.hymnsite.com/lyrics/umh545.sht)

እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያንን በልጁ ደም በዋጃት ጊዜ፣ እርሱ በአእምሮው ያሰበው ልዩ ሕዝብ እንዳልነበረ ስታስብ፣ ቤተ ክርስቲያን የምታጣው ለሙሽሪት የሆነ ልዩ ፍቅር በዚህ መሥዋዕትነት ውስጥ አለ።

ለማገለግልባት ቤተ ክርስቲያን እንዲህ እላቸው ነበር፤ “የዚህችን ቤተ ክርስቲያን ሴቶች ሁሉ እወዳቸዋለሁ፤ ነገር ግን ሚስቴን እጅግ በተለየ መንገድ እወዳታለሁ። ” ኖዌል፣ እኔ ሁሉንም ሴቶች ስለምወድ እና እርሷም ከእነርሱ አንዷ በመሆኗ፣ እንደተወደደች እንድታስብ አልፈልግም። በእግዚአብሔር እና በዓለም ባሉ ሰዎች መካከልም እንዲሁ ነው። ለሁሉም የሆነ መላለማዊ ፍቅር አለው፤ ነገር ግን ለሙሽሪት ብቻ የሆነ ልዩ ፍቅር አለው። ክርስቶስም በሞተ ጊዜ፣ በሞቱ ለእርሷ የተለየ ዐላማ ነበረው። ዓለም ከመፈጠሩ አስቀድሞም ዐወቃት፤ ደግሞም እርሷን ለማግኘት ሞተ።

## አሰደናቂው የሮሜ 8፥32 አመክንዮ

በቤዝዎቱ ዐላማ እና ስፋት ጉዳይ ላይ ሌላኛው አስፈላጊ ክፍል ሮሜ 8፥32 ነው። ይህም በመጽሐፍ ቅዱሳችን ውስጥ ለእግዚአብሔር ሕዝብ ከተገቡ እጅግ ውድ ከሆኑ የተስፋ ቃሎች ውስጥ አንዱ ነው። ጳውሎስ እንዲህ ይለናል፣ “ለገዛ ልጁ ያልሳሳለት፣ ነገር ግን ለሁላችንም አሳልፎ የሰጠው እርሱ፣ ሁሉንስ ነገር ከእርሱ ጋር እንደምን በልግስና አይሰጠን?” ይህ ያልተመለሰው ጥያቄ፣ እንድንመልሰው እና እንደ ዐለት ወደ ጠነከረ የተስፋ ቃል እንድናዞረው ዕድል ይሰጠናል። “ለገዛ ልጁ ያልሳሳለት፣ ነገር ግን ለሁላችንም አሳልፎ የሰጠው ከሆነ፣ በርግጠኝነት ከእርሱ ጋር ሁሉንም ነገር በልግስና ይሰጠናል።” በዚህ ክፍል “ሁላችን” የተባሉት እነማን ናቸው? እነርሱም የቊ. 29-31 ሰዎች ናቸው፤

> “እግዚአብሔር አስቀድሞ ያወቃቸውን የልጁን መልክ እንዲመስሉ አስቀድሞ ወሰናቸው፤ ይኸውም ከብዙ ወንድሞች መካከል እርሱ በኩር እንዲሆን ነው። አስቀድሞ የወሰናቸውን ጠራቸው፤ የጠራቸውን አጸደቃቸው፤ ያጸደቃቸውን አከበራቸው። ታዲያ ለዚህ ምን እንመልሳለን? እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ከሆነ፣ ማን ሊቃወመን ይችላል?”

ጳውሎስ በቍጥር 32 እንዲህ ያለ አስገራሚ የተስፋ ቃል— “ለእኛ፤ እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር በልግስና በርግጥ ይሰጠናል”— የማለቱ ምክንያት፣ ተደራሲያኑ አስቀድመው የታወቁ፣ አስቀድመው የተወሰኑ፣ የተጠሩ እንዲሁም የጸደቁ በመሆናቸው ነው። እነዚህም “በጎቹ” ደግሞም “የተበተኑ የእግዚአብሔር ልጆች” ናቸው። ጳውሎስም የክርስቶስ ሞት ለእነዚህ ሰዎች፣ ከእርሱ ጋር ሁሉን ነገር እንደሚቀበሉ የማይናወጥ እና ፍጹም ርግጥ የሆነ ዋስትናቸው ነው ይላል። ይህም አስገራሚው የሮሜ 8፥32 አመክንዮ ነው።

በዚህ መንገድ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ሁሉን ለማይቀበሉ ነገር ግን ለሚጠፉት፣ ለብዙ ሺዎች ልጁን ሰጥቶ ቢሆን ይህ አመክንዮ ምን ይሆናል? በርግጠኝነት ይፈርሳል። እንዲህም ይሆናል፣ “እግዚአብሔር ለገዛ ልጁ ያልሳሳለት ነገር ግን በዓለም ላሉ ሰዎች ሁሉ እርሱን ከሰጠ፣ ከእነርሱም ደግሞ ብዙዎች የሚጠፉ ከሆነ፣ ከእርሱ ጋር ሁሉን ነገር በርግጥ መቀበላቸው እውነት ሊሆን አይችልም።” ይህም ፈጽሞ የክፍሉ ዐሳብ አይደለም።

ክፍሉ የሚለው ይህን ነው፤ እግዚአብሔር ለራሱ ሰዎች ልጁን በመስጠቱ ምክንያት እነዚያ—ማለትም ዓለም ከመመሥረቱ አስቀድሞ የታወቁ እና የተወሰኑ—እግዚአብሔር ሊሰጥ ያለውን ነገር ሁሉ በርግጥ ይቀበላሉ። ስለዚህም እግዚአብሔር ልጁን በመስጠቱ ያለው ዐላማ ለመላው ዓለም የሆነ አጠቃላይ ግብዣ ብቻ ሳይሆን፣ ነገር ግን ለራሱ ሕዝብ ወሰን አልባ ትሩፋትን በጽናት ማስጠበቅ ነው። የእኔም ናፍቆት የእግዚአብሔር የሆኑ ሰዎች ይህንን እንዲመለከቱት እና ወደ ውሱን ቤዝዎት ጸጋ ጠልቀው እንዲገቡ ነው። እኛ በቤዝዎቱ በአጠቃላይ ሳይሆን በልዩነት ተወደናል። ወደ ፊታችንም በክርስቶስ ደም በልዩነት የተጠበቀ ነው።

ሳጠቃልል፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊው የውሱን ቤዝዎት ዐሳብ፣ እግዚአብሔር በክርስቶስ ሞት ለምርጦቹ ልዩ ዐላማ ነበረው የሚል ነው። እርሱ የገዛላቸው አምነው የሚድኑበትን ዕድል አይደለም፤ ነገር ግን እምነትን ራሱን ነበር። የእግዚአብሔር ምርጦች መለወጥ (ዳግም ልደት) በደም የተገዛ ነው። የሞታችን እና በእግዚአብሔር ላይ ያለን ዐመፀኝነታችን መረታት፣ እኛ ለቤዝዎቱ ብቁዎች እንሆን ዘንድ በእኛ የተከናወነ አይደለም።

የእግዚአብሔር ሉዓላዊ ጸጋ፣ ሞታችንን እና ዐመፀኝነታችንን አሸንፎታል። ይህም ጸጋ ደግሞ በክርስቶስ ሞት ተገዝቶልናል።

የእግዚአብሔርን ጸጋ በመለማመድ ጠልቀን መሄድ ከፈለግን፣ እንድንደሰትበት ይህ የፍቅር ውቅያኖስ ነው። እግዚአብሔር፣ የልጁ ሙሽሪት ዓለምን ሁሉ ባቀፈ አጠቃላይ ፍቅር እንደተወደደች እንዲሰማት አይፈልግም፤ የሚፈልገው ዓለም ከመፈጠሩ አስቀድሞ በተለየ ፍቅር እንደወደዳት እንድታስብ ነው። እኛም እንዲህ እንድናስብ ይፈልጋል፣ “እኔ መረጥኳችሁ፤ ደግሞም እናንተን አገኝ ዘንድ ልጄ እንዲሞት ላክሁላችሁ።”

ለዓለም የምናቀርበው ይህንን ነው። ለራሳችን ተስገብግበን አናከማቸውም። እንዲሁም ደግሞ ለሰው ሁሉ የሆነውን አጠቃላዩን የእግዚአብሔር ፍቅር፣ ለዓለም ማቅረብ አለብን በማለት ልዩ ፍቅሩን አንተወውም። በፍጹም! ሙሉ፣ ፍጹም እና ርግጥ የሆነውን ቤዝዎት እናቀርባለን፤ ክርስቶስን እናቀርባለን። ወደ ዕድሉ ኑ አንልም፤ ነገር ግን ወደ ክርስቶስ ኑ፤ እርሱንም ተቀበሉት እንላለን። የሚመጡም ከሆነ፣ ከክርስቶስ እና ከሙሽሪት ጋር አንድ እንደሚሆኑ ቃል እንገባላቸዋለን። ለሙሽሪት የገዛላት ሁሉ የእነርሱ ይሆናል። ደግሞም በፍጹም ርግጠኝነት ያስጠበቀው ሁሉ፣ ለዘላለም ዕድል ፈንታቸው ይሆናል።

ማመናቸውም ከምርጦቹ መካከል መሆናቸውን ይመሰክርላቸዋል። ወደ ክርስቶስ መምጣታቸው ደግሞ፣ የልዩ ቤዝዎት እና የተረጋገጠው መዋጀት ልዩ ጥቅም ወራሾች መሆናቸውን ይገልጠዋል።

የእግዚአብሔርን ጸጋ በመለማመድ መጥለቃችንን ለማጽናት፣ አሁን ወደ ምርጫ አስተምህሮ እንሻገራለን፤ ምክንያቱም እርሱ በዚህ ከልኬት በሚያልፍ ዘላለማዊ የፍቅር ዐላማ የሞተው ለምርጦቹ ነውና።

# ሁኔታ አልባ ምርጫ

እኛ ሁላችንም በኀጢአት ሙሉ ለሙሉ የተበከልን ስለሆንን፣ በእግዚአብሔር የማይቋቋሙት ጸጋ ዳግም ካልተወለድን በስተቀር ወደ እግዚአብሔር ፊጽመን ልንቀርብ የማንችል ከሆነ፣ ደግሞም ይህ ልዩ ጸጋ በኢየሱስ ክርስቶስ የመስቀል ላይ መሥዋዕትነት የተገኘ ከሆነ፣ ለሁላችንም ድነት ምክንያቱ የእግዚአብሔር ምርጫ መሆኑ ግልጽ ነው። የማይቋቋሙትን ይህን ጸጋ የሚያሳያቸውን እና ጸጋውንም የሚገዛላቸውን እነዚያን እግዚአብሔር መርጧቸዋል።

ምርጫ እግዚአብሔር ማንን ለማዳን እንደወደደ የሚያሳይ ነው። ይህ ምርጫ ሰው ለድነት በእግዚአብሔር ከመመረጡ በፊት ሊያሟላ የሚገባው ምንም ቅድመ ሁኔታ ባለመኖሩ፣ ሁኔታ አልባ ነው። ሰው በኀጢአት እና በመተላለፍ የሞተ ነው። ስለዚህ ሰውን እግዚአብሔር በሉዓላዊ ምርጫው ከሙትነቱ ከማዳኑ በፊት፣ ሰው ማሟላት የሚችለው ምንም ዐይነት ሁኔታ የለም።

የመጨረሻው ድነት ቅድመ ሁኔታ የለውም እያልን አይደለም፤ እንደዛ አይደለም። ለምሳሌ፣ የዘላለምን ሕይወት ለማግኘት በክርስቶስ የማመንን ሁኔታ የግድ ማሟላት ይገባናል። ይሁን እንጂ እምነት ለመመረጥ ቅድመ ሁኔታ አይደለም፤ ተገላቢጦሹ ነው። መመረጥ ለእምነት ቅድመ ሁኔታ ነው። ምክንያቱም እግዚአብሔር ዓለም ሳይፈጠር አስቀድሞ መርጦናል፤ በመስቀሉ ቤዝዎትን አስገኝቶልናል፤ በማይቋቋሙት ጸጋው ዳግም ወልዶናል፤ ወደ እምነትም አምጥቶናል።

## ምርጫ ከእምነት በፊት

ሐዋ. 13፥48 በአንጾኪያ ጲስድያ አሕዛብ ለወንጌል ስብከት እንዴት ምላሽ እንደሰጡ ይነግረናል፤ “አሕዛብ ይህን በሰሙ ጊዜ ደስ አላቸው፤ ለእግዚአብሔርም ቃል ክብርን ሰጡ፤ *ለዘላለም ሕይወት የተዘጋጁትም ሁሉ አመኑ።*” ልብ በሉ፤ ያመኑ ሁሉ ለዘላለም ሕይወት ለመዘጋጀት[ለመመደብ] ተመረጡ አይልም፤ ለዘላለም ሕይወት የተዘጋጁ [እግዚአብሔር የመረጣቸው] አመኑ ነው የሚለው።

የእግዚአብሔር ሉዓላዊ ምርጫ ከእምነት ይቀድማል፤ እምነትንም ያስከትላል። አንዳንዶች የሚያምኑበት ሌሎች የማያምኑበት ወሳኙ ምክንያት ይህ ነው።

በተመሳሳይ ዮሐንስ 10፥26 ላይ ኢየሱስ ለአይሁድ እንዲህ ይላል፣ *"እናንተ ግን በጎቼ ስላልሆናችሁ አታምኑም።"* አሁንም አስተውሉ፤ "በእኔ ስላላመናችሁ ከበጎቼ አይደላችሁም" አላለም። በጎቹ እነማን እንደሚሆኑ እግዚአብሔር እኛ ከማመናችን አስቀድሞ የሚወስነው ነው። ይህ ምርጫ የእምነታችን መሠረት እና እንድናምን የሚያስችለን ነው። "ከበጎቼ ስላልሆናችሁ አታምኑም" የምናምነው በእግዚአብሔር የተመረጡ በጎቹ ስለሆንን እንጂ በጎቹ ለመሆን አይደለም። (ዮሐንስ 8፥27፤ 18፥37)

## ሁኔታ አልባ ምርጫ በሮሜ 9[10]

ጳውሎስ በሮሜ ምዕራፍ 9 የእግዚአብሔር ምርጫ ሁኔታ አልባ መሆኑ ላይ አጽንዖት ይሰጣል። ቍጥር 11 እና 12 ላይ እግዚአብሔር ኤሳውን ሳይሆን ያዕቆብን ለመምረጥ የተጠቀመበትን መርህ ይገልጻል፤ *"መንትዮቹ ገና ሳይወለዱ፣ ወይም በጎም ሆነ ክፉ ሳያደርጉ፣ የእግዚአብሔር ዐሳብ በምርጫ ይጸና ዘንድ፣ በሥራ ሳይሆን ከጠሪው በመሆኑ፣ 'ታላቁ ታናሹን ያገለግላል' ተብሎ* [ለርብቃ] *ተነገራት።"* የእግዚአብሔር ምርጫ በቅድመ ሁኔታ አልባነቱ ይጸናል፤ ምክንያቱም ምርጫው እኛ ከመወለዳችን አስቀድሞ፣ ወይም በጎም ሆነ ክፉ ከማድረጋችን በፊት የተጠናቀቀ ነው።

አንዳንድ ተርጓሚዎች፣ ሮሜ 9 ሰዎች ለዘላለማዊ ፍጻሜ ከመመረጣቸው ጋር የሚያገናኘው ነገር የለም፤ ይልቁንም ስለ አንድ ማኅበረሰብ ታሪካዊ ሚና የሚናገር ነው እንደሚሉ ዐውቃለሁ። እንግዲህ ይህ አስተሳሰብ ፍጹም ስሕተት እንደሆነ የማምንበት ዋነኛው ምክንያት፣ ጳውሎስ በዚህ ምዕራፍ እያብራራ ካለው ዐሳብ ፈጽሞ የራቀ በመሆኑ ነው። የመጀመሪያዎቹን የሮሜ 9 ዐምስት ቍጥሮች በማንበብ ብቻ፣ ይህን በራሳችሁ መመልከት ትችላላችሁ። ሮሜ 9፥6

---

[10] ሮሜ ምዕራፍ 9 ለሁኔታ አልባ ምርጫ መሠረታዊ ነው፤ ስለዚህም ከቍጥር 1-23 ድረስ ማብራሪያ መጽሐፍ አዘጋጅቼለታለሁ፤ John Piper, *The Justification of God: An Exegetical and Theological Study of Romans 9:1-23* (Grand Rapids: Baker Academic, 1993).

ላይ ጳውሎስ፣ “ነገር ግን የእግዚአብሔር ቃል ተሽሮአል ማለት አይደለም” ሲል ግልጽ የሆነው ነገር፣ የእግዚአብሔር ቃል የተሻረ እንዲመስል ያደረገ፣ የሆነ ነገር መኖሩ ነው። ያ ነገር ምንድር ነው?

መልሱ በቍጥር 2 እና 3 ላይ ይገኛል። ጳውሎስ፣ “ታላቅ ኀዘንና የማያቋርጥ ጭንቀት በልቤ አለ። ለወገኖቼ ስል ስለ ወንድሞቼ እኔ ራሴ የተረገምሁና ከክርስቶስ ተለይቼ የተጣልሁ እንድሆን እንኳ እወድ ነበር” ይላል። ጳውሎስ እየገለጸ የሚገኘው እና እርሱን ያስጨነቀው ዋና ዐሳብ፣ እስራኤል እንደ አገር ለምን ይህ ወይም ያ ሚና ኖራት የሚለው አይደለም፤ ነገር ግን በእስራኤላውያን መካከል ከክርስቶስ ተለይተው የሚጠፉት ግለሰቦች ጒዳይ ነው። በሌላ አነጋገር፣ በርግጥም የግለሰቦች ዘላለማዊ ፍጻሜ አደጋ ላይ ነው። የጳውሎስ ሙግት ባሕርይ ይህን ያረጋግጣል፤ ምክንያቱም የእግዚአብሔር ቃል እንዳልተሻረ ለማሳየት የሚያቀርበው የመጀመሪያው መግት እንዲህ የሚል ነው፣ “ከእስራኤል የተወለደ ሁሉ እስራኤል አይደለምና” (ሮሜ 9፥6)። በሌላ አባባል፣ ከእስራኤላውያን መካከል የሚጠፉት ግለሰቦች የእውነተኛው እስራኤል ቤተሰብ አልነበሩም። ከዚያም በእስራኤል መካከል የእግዚአብሔር ሁኔታ አልባ ምርጫ እንዴት እንደሚሠራ ወደማሳየት ይዞራል።[11]

የእግዚአብሔር ምርጫ ሁኔታ አልባነት በሮሜ 9፥15-16 ላይም በድጋሚ አጽንዖት ተሰጥቶታል፤ “ለሙሴ፣ የምምረውን እምረዋለሁ፤ ለምራራለትም እራራለታለሁ ይላልና። እንግዲህ ይህ ከሰው ፍላጎት ወይም ጥረት ሳይሆን፣ ከእግዚአብሔር ምሕረት የተነሣ ነው።” እኛ የሚያስፈልገን ምሕረት፣ ፈቃዳችንን የሚያነቃ እና ፈቃዳችንን የሚለውጥ ምሕረት ነው። እኛ ሁላችን እግዚአብሔርን መውደድ፣ ማመን እና መከተል የሚያስችል ዝንባሌ የሌለን እንደሆንን፣ በማይቋቋሙት ጸጋ እና በአጠቃላይ ውድቀት ምዕራፎች ተመልክተናል። ስለዚህ ብቸኛው ተስፋችን ሉዓላዊው ምሕረት፣ የማይቋቋሙት ምሕረት ነው። ይህ እውነት ከሆነ፣ ጳውሎስ እዚህ ጋር የሚለው ነገር ትርጒም ይሰጣል። ምሕረት ለመቀበል ወይም ለማምጣት የተገባን ሰዎች አይደለንም።

---

[11] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 38-54 ለዚህ መረዳት ተጨማሪ ሙግቶች ተሰጥተዋል።

ምሕረት የምንቀበለው በእግዚአብሔር ነጻ ምርጫ ነው። ጳውሎስ የሚለው ይህንን ነው፤ “የምምረውን እምረዋለሁ፤ ለምራራለትም እራራለታለሁ” ይላልና።

ጳውሎስ በሮሜ 11፥7 በእስራኤል መካከል የምርጫን ግለሰባዊ ባሕርይ በድጋሚ ያሰምራል፤ “እንግዲህ ምንድን ነው? እስራኤል የፈለጉትን አላገኙትም፤ የተመረጡት ግን አገኙት፤ የተቀሩትም ልባቸው ደነደነ።” ስለዚህ ጳውሎስ ከሮሜ 9-11 ድረስ፣ ምርጫ ግለሰቦችን እና ዘላለማዊ ፍጻሜአቸውን እንዲሁም ሁኔታ አልባ መሆኑን ይቀበላል። የእስራኤልን ዳግም ማንሰራራት አስመልክቶ መለኮታዊ ኪዳን እንዳለ አምናለሁ፤ ይህ ግን የሮሜ 9ን ግለሰባዊ ድነት የሚጣረስ ወይንም የሚሽር አይደለም። የእግዚአብሔር ምርጫ ሁኔታ አልባነት በሮሜ 9፥11 በግልጽ ተቀምጧል። “መንትዮቹ ገና ሳይወለዱ፣ ወይም በጎም ሆነ ክፉ ሳያደርጉ፣ የእግዚአብሔር ዐሳብ በምርጫ ይጸና ዘንድ” እግዚአብሔር የሚመርጠው በዚህ መልክ ነው።

## የሁኔታ አልባነት ሌላ ጠንካራ ምንባብ

ኤፌሶን 1፥3-6 ለልጅነት የመመረጥና የመወሰንን ሁኔታ አልባነት የሚያስረዳን እጅግ ጠንካራ ምንባብ ነው።

> “በሰማያዊ ስፍራ በመንፈሳዊ በረከት ሁሉ በክርስቶስ የባረከን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አባት ይባረክ። በፊቱ ቅዱሳንና ነውር አልባ እንድንሆን ዓለም ከመፈጠሩ አስቀድሞ በእርሱ መርጦናልና። በፍቅር፣ በኢየሱስ ክርስቶስ እንሆን ዘንድ፣ እንደ በጎ ፈቃዱ አስቀድሞ ወሰነን፤ ይኸውም፣ በሚወደው በእርሱ በኩል በነጻ የተሰጠን ክቡር የሆነው ጸጋው እንዲመሰገን ነው።”

አንዳንድ ተርጓሚዎች ይህ ዓለም ከመፈጠሩ አስቀድሞ የተደረገው ምርጫ የክርስቶስ እንጂ፣ በክርስቶስ የሚድኑ ግለሰቦች ምርጫ አይደለም ሲሉ ይሞግታሉ። ይህ በቀላሉ፣ ያለ ቅድመ ሁኔታ ለድነት የተደረገ የግለሰቦች ምርጫ የለም ከማለት ጋር እኩል ነው።

ክርስቶስ በእግዚአብሔር የተመረጠው ሆኖ ቀርቧል፤ የግለሰቦች ድነት ደግሞ፣ ከኀጢአት ውድቀት ለመላቀቅ እና በእምነት ወደ ክርስቶስ ለመቅረብ ባላቸው በራሳቸው ተነሣሽነት ላይ የተመሠረተ ነው። እግዚአብሔርም አልመረጣቸውም፤ ስለሆነም እነርሱን በውጤታማነት ሊለውጣቸው አይችልም፤ መረዳትን ማስጀመር ብቻ ነው የሚችለው። በመጨረሻ እነማን ራሳቸውን ከሞት ለማስነሣት ወስነው እርሱን እንደሚመርጡ ለማየት ይጠባበቃል።

ይህ አፈታት ቍጥር 11 ላይ፣ *"ሁሉን በፈቃዱ ምክር መሠረት እንደሚሠራው* እንደ እርሱ ዕቅድ አስቀድሞ የተወሰንን እኛ ደግሞ በእርሱ ተመርጠናል" ከሚለው ጋር በአግባቡ አይገጥምም። ከቍጥር 4 የቃላት አጠቃቀም ጋር አይስማማም። ቍጥር 4 ላይ "መረጠን" የሚለው ቃል መደበኛ ትርጉም፣ ከብዙኃን መካከል ጥቂቱን መውሰድ ነው (ሉቃስ 6፥13፤ 14፥7፤ ዮሐንስ 13፥18፤ 15፥16፣ 19)። ስለዚህ የቍጥር 4 ትክክለኛ ትርጉም፣ እግዚአብሔር ዓለም ከመፈጠሩ አስቀድሞ በአዳኙ በክርስቶስ በኩል የራሱን ሕዝብ ከሰዎች መካከል መርጧል። የጥቅሱ ትክክለኛ አነባበብ ይህ ነው።

ሁሉም ምርጫ በክርስቶስ በኩል መሆኑ እውነት ነው። ዓለም ከመፈጠሩ አስቀድሞ ክርስቶስ በእግዚአብሔር ዐሳብ ውስጥ ተሰቅሏል (ራዕ. 13፥8)። ክርስቶስ ለኀጢአታቸው እንዲሞት ባይመረጥ፣ የኀጢአተኞች ለድነት መመረጥ አይኖርም ነበር። ስለዚህ በዚህ አኳያ እነርሱ *በክርስቶስ በኩል* ምርጦች ናቸው፤ ነገር ግን በክርስቶስ እንዲሆኑ ከዓለም የተመረጡት *እነርሱ* ናቸው።

የቍጥር 5 የቃል አጠቃቀም የሚያሳየን እንዲሁ የክርስቶስን መመረጥ ሳይሆን፣ የሰዎችን ለድነት መመረጥ ነው። ቍጥር 5 ቃል በቃል እንዲህ ይቀመጣል፤ "በኢየሱስ ክርስቶስ ልጆቹ እንሆን ዘንድ፣ እንደ በጎ ፈቃዱ አስቀድሞ ወሰነን።" አስቀድሞ የተወሰንነው እኛ ነን እንጂ ክርስቶስ አይደለም። የኀጢአተኞችን ቅድመ ውሳኔ እና ምርጫ እንዲሁም ልጅነትን የሚሠራው እርሱ ነው፤ ስለዚህ ምርጫው "በእርሱ በኩል" ነው፤ ነገር ግን እግዚአብሔር በምርጫ ክርስቶስን ብቻ ተመልክቷል የሚል ንግግር የለም። ክርስቲያኖች ዓለም ሳይፈጠር በፊት ቅዱሳን ለመሆን ስለተመረጥን ወደ ማመን እንመጣለን፤ ከክርስቶስ ጋር አንድ እንሆናለን፤ እንዲሁም በደሙ እንሸፈናለን።

## ምናልባትም በጣም አስፈላጊው ምንባብ

ሮሜ 8፥28-33 የሁኔታ አልባ ምርጫ ትምህርትን በተመለከተ ምናልባትም ከሁሉም በላይ በጣም አስፈላጊው ምንባብ ነው።

> “እግዚአብሔር፣ ለሚወዱትና እንደ ዐሳቡ ለተጠሩት፣ ነገር ሁሉ ተያይዞ ለበጎ እንዲሠራ እንደሚያደርግላቸው እናውቃለን። እግዚአብሔር አስቀድሞ ያወቃቸውን የልጁን መልክ እንዲመስሉ አስቀድሞ ወሰናቸው፤ ይኸውም ከብዙ ወንድሞች መካከል እርሱ በኵር እንዲሆን ነው። አስቀድሞም የወሰናቸውን ጠራቸው፤ የጠራቸውንም አጸደቃቸው፤ ያጸደቃቸውን አከበራቸው። ታዲያ ለዚህ ምን እንመልሳለን? እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ከሆነ፣ ማን ሊቃወመን ይችላል? ለገዛ ልጁ ያልሳሳለት፣ ነገር ግን ለሁላችን አሳልፎ የሰጠው እርሱ፣ ሁሉንስ ነገር ከእርሱ ጋር እንደምን በልግስና አይሰጠንም? እግዚአብሔር የመረጣቸውን የሚከስ ማን ነው? የሚያጸድቅ እግዚአብሔር ነው፤ ታዲያ የሚፈርድ ማን ነው?

በቍጥር 29፣ “እግዚአብሔር አስቀድሞ ያወቃቸውን የልጁን መልክ እንዲመስሉ አስቀድሞ ወሰናቸው” የሚለውን መሠረት በማድረግ ይህ ምንባብ ብዙ ጊዜ ሁኔታ አልባ ምርጫን ለመቃወም ይቀርባል። አንዳንዶች፣ ሰዎች ለድነት የሚመረጡት ያለ ቅድመ ሁኔታ አይደለም ይላሉ፤ ያለ ሉዓላዊው ጸጋ ርዳታ በራሳቸው በሚፈጥሩት እና አስቀድሞ በታወቀው እምነታቸው መሠረት ነው የተመረጡት። እግዚአብሔር አስቀድሞ የሚያየው ይህን ነው።

ነገር ግን ይህ አስተሳሰብ ጳውሎስ ሙግቱን ከሚያደረጅበት መንገድ ጋር አይጣጣምም። ሮሜ 8፥30 የሚለውን አስተውል፤ “አስቀድሞም የወሰናቸውን ጠራቸው፤ የጠራቸውንም አጸደቃቸው፤ ያጸደቃቸውን አከበራቸው።” ለጊዜው እግዚአብሔር የሚጠራቸውን ሁሉ በማጽደቁ እውነት ላይ ትኩረት አድርጉ።

በቍጥር 30 ላይ የተገለጸው ይህ ጥሪ ለሁሉም የተሰጠ አይደለም፤ ምክንያቱም የጠራቸው ሁሉ እነዚያ ጸድቀዋል።

በተጠሩት እና በጸደቁት መካከል የማይሻር ትስስር አለ። “የጠራቸውንም አጸደቃቸው።” ነገር ግን ሁሉ ሰው አይጸድቅም። ስለዚህ ሁሉም ሰዎች የተጠሩ አይደሉም። ይህ ጥሪ ሰባኪዎች የሚያቀርቡት ወይም እግዚአብሔር በፍጥረቱ ክብር አማካይነት የሚያቀርበው አጠቃላይ የሆነ ጥሪ አይደለም። እንዲህ ያለው አጠቃላይ ጥሪ ለሁሉም ሰው የሚደረግ ነው። የቍጥር 30 ጥሪ እግዚአብሔር የልጁን መልክ እንዲመስሉ ለወሰናቸው ብቻ የተሰጠ ጥሪ ነው (ቍ.29)። የግድ ወደ መጽደቅ የሚወስድ ጥሪ ነው። “የጠራቸውንም አጸደቃቸው”

ጽድቅ በእምነት ብቻ እንደሆነ እናውቃለን። “ማንም ሰው ሕግን በመፈጸም ሳይሆን፣ በእምነት እንደሚጸድቅ እናረጋግጣለን” (ሮሜ 3፥28፤ 5፥1)። አስቀድሞ ለተወሰኑት ብቻ የተሰጠው እና በርግጠኝነት ወደ ጽድቅ የሚያደርሰው ይህ ጥሪ ምንድን ነው? በምዕራፍ 4 የማይቋቋሙት ጸጋን ስንወያይ አስቀድመን ተመልክተነዋል። ይህ የ1ኛ ቆሮንቶስ 1፥23-24 ጥሪ ነው፤ “እኛ ግን የተሰቀለውን ክርስቶስን እንሰብካለን፤ ይህም ለአይሁድ መሰናክል፣ ለአሕዛብ ደግሞ ሞኝነት ነው። *እግዚአብሔር ለጠራቸው ግን*፣ አይሁድም ሆኑ ግሪኮች፣ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ኀይል፣ የእግዚአብሔርም ጥበብ ነው።” በሌላ አነጋገር፣ ስብከት ለሁሉም አይሁድ እና አሕዛብ እስከሆነ ድረስ፣ ጥሪው የወንጌል ስብከት አይደለም። ይልቁንም በስብከት በኩል፣ በጥቂት አድማጮች ልብ ወስጥ ጥሪው ይከሰታል። ጥሪው አድማጮቹን ከሙታን ያነቃቸዋል፤ የእግዚአብሔር ጥበብ እና ኀይል መሆኑን እንዲቀበሉ ለክርስቶስ መስቀል ያላቸውን እይታ ይቀይራል። በሌላ አነጋገር፣ የሮሜ 8፥30 ጥሪ እምነትን የሚፈጥር፣ የማይቋቋሙት ጸጋ ነው።

አሁን እንደገና በሮሜ 8፥30 የጳውሎስን የዐሳብ ፍሰት አስተውሉ። “አስቀድሞም የወሰናቸውን ጠራቸው፤ የጠራቸውንም አጸደቃቸው፤ ያጸደቃቸውን አከበራቸው።” በቅድመ ውሳኔ እና በጽድቅ መካከል ጥሪ አለ። ጽድቅ በእምነት ብቻ ስለሆነ፣ ይህ ጥሪ እግዚአብሔር እምነትን ወደ መኖር የሚጠራበት ተግባር መሆኑ ግድ ነው። ጥሪው ሁልጊዜ ጽድቅን የሚያስከትል ስለሆነ (የተጠሩ ሁሉ እነዚያ ስለሚጸድድቁ)፣ ሉዓላዊ መሆኑ ግድ ነው። ይህም መንገድ ላይ የሚገባን ማንኛውንም እንቢተኝነት የሚረታ ነው። ስለሆነም የቍጥር 30 ጥሪ፣ ሰዎችን ወደሚያጸድቅ እምነት የሚያደርሳቸው ሉዓላዊ የእግዚአብሔር ሥራ ነው።

አሁን ይህን በቍጥር 29 ቅድመ ዕውቀት ትርጓሜ ላይ ያለውን ምልከታ አስተውሉ። ቍጥር 29 ላይ ጳውሎስ፣ “አስቀድሞ ያወቃቸውን የልጁን መልክ እንዲመስሉ አስቀድሞ ወሰናቸው” ብሎ ሲናገር፣ [ብዙዎች ጳውሎስ ብሏል ብለው እንደሚናገሩት] ወደ እምነት ለመምጣት ነጻ ፈቃዳቸውን የሚጠቀሙትን እግዚአብሔር አስቀድሞ ያውቃል፤ ስለዚህ ለልጅነት ሊወስናቸው ይችላል ምክንያቱም በራሳቸው ነጻ ምርጫ አድርገዋል ሊል አይችልም። እንደዚህ ሊሆን አይችልም፤ ምክንያቱም ለጸደቁት ሰዎች እምነት ወሳኙ ምክንያት የሰው ፈቃድ ሳይሆን፣ የእግዚአብሔር ሉዓላዊ ጥሪ እንደሆነ ከቍጥር 30 ተመልክተናል።

እግዚአብሔር እምነትን ከሚፈጥርበት መንገድ ውጪ፣ ወደ እርሱ የሚመጡትን አስቀድሞ አያውቃቸውም፤ ምክንያቱም እንደዚህ ዐይነት ሰዎች የሉም። የሚያምን ሁሉ በእግዚአብሔር ሉዓላዊ ጸጋ ወደ እምነት የተጠራ ነው። ከዘላለም ዘመናት በፊት፣ እግዚአብሔር መጪውን ጊዜ ሲመለከት እና የምርጦቹን እምነት ሲያይ፣ የሚያየው የራሱን *ሥራ* ነው። ይህንንም *ሥራ* የሠራው ሙታን፣ ዕውር እና ዐመፀኛ ለሆኑ ኀጢአተኞች ያለ ቅድመ ሁኔታ ነው። የእምነትን ቅድመ ሁኔታ ማሟላት አንችልም ነበር። መንፈሳዊ ሞት የሞትን እና የታወርን ነበርን።

ስለሆነም የሮሜ 8፥29 ቅድመ ዕውቀት፣ ወደ ፊት ስለሚሆነው ነገር እግዚአብሔር ከራሱ ቅድመ ብያኔ ውጭ የሚያውቅበት መደበኛ ዕውቀት አይደለም። በብሉይ ኪዳን ምንባቦች ከተገለጸው ጋር ተመሳሳይ ዕውቀት ነው። ዘፍ 18፥19 (“የእግዚአብሔርን መንገድ ይጠብቁ ዘንድ ልጆቹን... እንዲያዝ [አብርሃምን] መርጬዋለሁ [ቃል በቃል፣ *አውቄዋለው*]”)፣ ኤርምያስ 1፥5 (“በማሕፀን ሳልሠራህ ዐወቅሁህ፤ ከመወለድህ በፊት ለየሁህ፤ ለሕዝቦችም ነቢይ እንድትሆን ሾምኩህ”)፣ አሞጽ 3፥2 (“እኔ ከምድር ወገን ሁሉ እናንተን [እስራኤልን] ብቻችሁን *አውቄአችኋለሁ”-ቀ.ኃ.ሥ*)፣ በአንድ በኩል እግዚአብሔር የምድር ወገኖችን ሁሉ “*ያውቃል*”፤ ነገር ግን እዚህ ጋር ትርጉሙ እንዲህ ነው፤ እስራኤል ሆይ ለራሴ የመረጥኩህ አንተን ብቻ ነው።

ሲ. ኢ. ቢ. ክራንፊልድ እንደሚናገረው፣ የሮሜ 8፥29 ቅድመ ዕውቀት፣ “ግለሰብን በልዩነት የሚወስድበት ዕውቀት ነው፤ ይህም የሚመርጥ የእግዚአብሔር ጸጋ ነው።” እንዲህ ዐይነቱ ቅድመ ዕውቀት ከምርጫ ጋር አንድ ዐይነት ነው፤

“አስቀድሞ ያወቃቸውን (ማለትም የመረጣቸውን) የልጁን መልክ እንዲመስሉ አስቀድሞ ወሰናቸው።”

ስለሆነም ይህ ግሩም ክፍለ ምንባብ (ሮሜ 8፥28-33) እግዚአብሔር የሕዝቡን ቤዝዎት ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ ድረስ በርግጠኝነት እንደሚፈጽመው ያስተምረናል። ዓለም ከመፈጠሩ አስቀድሞ ሰዎችን ለራሱ አውቋል (ማለትም መርጧል)፤ እነዚህ ሰዎች የልጁን መልክ እንዲመስሉ አስቀድሞ ወስኗል፤ እነርሱንም በእምነት አማካኝነት ወደ ራሱ ይጠራቸዋል፤ በዚያ እምነት ብቻ ያጸድቃቸዋል፤ በስተመጨረሻም ያከብራቸዋል። እነርሱን ለዘላለም ዓለም በክርስቶስ ኢየሱስ ካለ ከእግዚአብሔር ፍቅር ምንም ሊለያቸው አይችልም (ሮሜ 8፥39)። ምስጋናና ክብር ሁሉ ለእርሱ ይሁን!

በክርስቶስ የምታምን ከሆንክ፣ አንተ ከዘላለም በእግዚአብሔር ተወደሃል። ዓለም ሳይፈጠር በፊት ምሕረቱን በአንተ ላይ አድርጓል። ረዳት አልባ በሆንክበት ሁኔታ ውስጥ እንዳለህ ዐይቶ፣ ያለ ምንም ቅድመ ሁኔታ ለራሱ መርጦሃል። በመመረጣችን ልንመካ አይገባም። ይህ ሁኔታ አልባነትን ፈጽሞ አለመረዳት ነው። ራሳችንን ለእግዚአብሔር ለማስገዛት በየትኛውም መንገድ አንዳች ሳናደርግ፣ እርሱ ግን ምሕረቱን በልግስና በእኛ ላይ አኖረ።

እግዚአብሔር እኛን የመረጠን እስራኤላውያንን በመረጠበት መንገድ ነው፤ “እግዚአብሔርም እናንተን የወደዳችሁና የመረጣችሁ ከሌሎች ሕዝቦች ሁሉ በቍጥር ስለ በዛችሁ አይደለም፤ ነገር ግን … እግዚአብሔር እናንተን ስለ ወደዳችሁ ነው” (ዘዳ. 7፥7-8)። ክፍሉን በጥንቃቄ አንብቡት፤ የወደዳችሁ ስለወደዳችሁ ነው። ይህን ለማድረግ የመረጠው ከዘላለም ነው። እርሱ ለእናንተ ያለው ፍቅር መነሻ ስለሌለው ማቆሚያም ሊኖረው አይችልም። በዚህ መጽሐፍ እያጠናን ያለነው ነገር፣ እግዚአብሔር በታሪክ ውስጥ የእርሱ የሆኑትን ለማዳን እና እኛን ወደ ራሱ ዘላለማዊ ደስታ ለማምጣት ዘላለማዊ ፍቅሩን ያሳየበትን መንገድ ነው። ይህን አስደናቂ ሉዓላዊ ጸጋ በጥልቀት ወደ መለማመድ እግዚአብሔር ያስገባችሁ።

# የቅዱሳን ጽናት

የእግዚአብሔር ሕዝብ እስከ መጨረሻው እንደሚጸኑ እና እንደማይጠፉ በቀደመው ምዕራፍ ተመልክተናል። አስቀድሞ የታወቁት አስቀድሞ ተወስነዋል፤ አስቀድሞ የተወሰኑት ተጠርተዋል፤ የተጠሩት ጸድቀዋል፤ የጸደቁት ከብረዋል (ሮሜ 8፥30)። ከዚህ ቡድን የሚጠፉ አንድም ሰው የለም። የዚህ ሕዝብ አካል መሆን የዘላለም ዋስትና ነው።

ነገር ግን የቅዱሳን ጽናት አስተምህሮ ስንል ከዚህ ያልፋል። ቅዱሳን *በእምነት እና ከእምነት በሆነ መታዘዝ እስከ መጨረሻው ይጸናሉ፤ ደግሞም የግድ ይጸናሉ* እያልን ነው። ምርጫ ቅድመ ሁኔታ የሌለው ነው፤ መክበር ግን እንዲህ አይደለም። ከክርስቶስ ጋር የማይጣበቁ ሰዎች በመጨረሻ እንደሚጠፉ በርካታ የቅዱሳት መጻሕፍት ምንባቦች ማስጠንቀቂያዎችን ይሰጡናል።

የሚከተሉት ስምንት ዝርዝር ነጥቦች፣ የዚህ አስተምህሮ የእኔ ማጠቃለያዎች ናቸው።

## 1. መዳን ካለብን፣ እምነታችን እስከ መጨረሻው ድረስ መጽናት አለበት።

ይህ ማለት እምነትን ለማስጀመር እና እምነትን ለመጠበቅ ወንጌል የእግዚአብሔር መሣሪያ ነው። በእኛ እይታ አንድ ሰው ከፋው ከሚደርስበት ክልል ውጪ እንደሆነ ያረጋገጥን ይመስል፣ በክርስቶስ አምናለሁ ስላለ ብቻ ለቅዱሳን ጽናት ጥሪ ግድ የለሾች አንሆንም። ልንጋደለው የተገባን የእምነት ገድል አለ። ይህን ገድል የተመረጡት ሁሉ ይጋደሉታል። ደግሞም በእግዚአብሔር ሉዓላዊ ጸጋ ያሸንፉታል። እንድን ዘንድ የግድ እስከ መጨረሻው በእምነት መጽናት አለብን።

በ1ኛ ቆሮንቶስ 15፥1-2 ጳውሎስ የጽናትን አስፈላጊነት ያሳያል፤ “*አሁንም፣ ወንድሞች ሆይ፤ የሰበክሁላችሁንና የተቀበላችሁትን ደግሞም ጸንታችሁ የቆማችሁበትን ወንጌል ላሳስባችሁ እወዳለሁ፤ የሰበክሁላችሁን ቃል አጥብቃችሁ ብትይዙ፣ በዚህ ወንጌል ትድናላችሁ፤ አለዚያ ያመናችሁት በከንቱ ነው።*” ይህ “አጥብቃችሁ ብትይዙ” የሚለው በክርስትና ሕይወት የሐሰት ጅማሬ እንዳለ ያሳየናል። ኢየሱስ የመሬቶቹን ምሳሌ የተናገረው ከእንደነዚህ ዐይነት የሐሰት ጅማሬዎች ለማስጠንቀቅ ነው።

> በድንጋያማ መሬት ላይ የተዘራው፣ ቃሉን ሰምቶ ወዲያውኑ በደስታ የሚቀበለውን ሰው ይመስላል። ነገር ግን ሥር መስደድ ባለመቻሉ ብዙ አይቈይም፤ በቃሉ ምክንያትም መከራ ወይም ስደት ሲመጣ ወዲያውኑ ይሰናከላል። በእሾኽ መካከል የተዘራው ዘር ቃሉን ሰምቶ ለዚህ ዓለም በመጨነቅና በብልጽግና ዐሳብ በመታለል ታንቆ ያላፈራውን ሰው ይመስላል። (ማቴዎስ 13፥20-22)

በሌላ አነጋገር ጳውሎስ በ1ኛ ቆሮንቶስ 15፥2 ላይ፣ “*አለዚያ ያመናችሁት በከንቱ ነው።*”—የውሸት እምነት እንደሚለው ነው። እንዲህ ያለው እምነት፣ እግዚአብሔርን መውደድን እና ኀጢአትን መጥላትን በማያካትቱ ሌሎች ምክንያቶች ወደ ክርስቶስ መምጣት ነው። ጳውሎስ የተናገረው የእውነተኛ እምነት ማረጋገጫ “ቃሉን አጥብቆ መያዝ” ነው፤ ማለትም መጽናት ነው።

በተመሳሳይ ጳውሎስ በቈላስይስ 1፥21-23፣ “ከክፉ ባሕርያችሁ የተነሣ ቀድሞ ከእግዚአብሔር የተለያችሁ በአሳባችሁም ጠላቶች ነበራችሁ። አሁን ግን ነውርና ነቀፋ የሌለባችሁ ቅዱሳን አድርጎ በእርሱ ፊት ሊያቀርባችሁ፣ በክርስቶስ ሥጋ በሞቱ በኩል አስታረቃችሁ፤ ይህም የሚሆነው በእምነታችሁ ተመሥርታችሁና ተደላድላችሁ በመቆም ከሰማችሁት የወንጌል ተስፋ *ሳትናወጡ ጸንታችሁ ብትኖሩ* ነው። እናንተ የሰማችሁትና ከሰማይ በታች ላለ ፍጥረት ሁሉ የተሰበከውም ወንጌል ይኸው ነው፤ እኔም ጳውሎስ ለዚህ ወንጌል አገልጋይ ሆንሁ።” እንዲሁም በ2ኛ ጢሞቴዎስ 2፥11-12፣ “እንዲህ የሚለው ቃል የታመነ ነው፤ ከእርሱ ጋር ከሞትን፣ ከእርሱ ጋር ደግሞ በሕይወት እንኖራለን። *ብንጸና፣ ከእርሱ ጋር ደግሞ እንነግሣለን።*” ይላል።

ጳውሎስ በእነዚህ ምንባቦች የኢየሱስን ትምህርት እየተከተለ ነው። ጌታችን ኢየሱስ በማርቆስ 13፥13፣ *"እስከ መጨረሻው የሚጸና ግን ይድናል"* ብሏል። ከትንሣኤው በኋላም በዮሐንስ ራዕይ ለተጠቀሱት አብያተክርስቲያናት እንዲህ ብሏል፣ "ድል ለሚነሣ በእግዚአብሔር ገነት ካለው ከሕይወት ዛፍ እንዲበላ አደርገዋለሁ" (ራዕ. 2፥7)። *"እስከሞት ድረስ ታማኝ ሁን እኔም የሕይወትን አክሊል እሰጥሃለሁ።"* (ራእይ 2፥10፤ 2፥17፣ 25-26፤ 3፥5፣ 11-12፣21)። ይህ እስከ መጨረሻ ልንጸና ይገባናል በማለት የገለጽነው የጽናትን አስፈላጊነት ያሳየናል።

ነገር ግን ማብራራት ያስፈልጋል። በእምነት መጽናት ማለት ቅዱሳን በጥርጣሬ፣ በመንፈሳዊ ሕይወት ድካም፣ በእግዚአብሔር መልካምነትና በሰጠው ተስፋ ባለማመን ፈተና ውስጥ አያልፉም ማለት አይደለም። *"አምናለሁ፤ አለማመኔን ርዳው!"* (ማር. 9፥24) ማለት የሚጋጭ ጸሎት አይደለም። ምክንያቱም ያለማመን ፈተና ከእውነተኛ እምነት ጋር በአንድ ላይ ሊኖር ይችላል።

ስለዚህ የሚያድን እምነት እስከ መጨረሻው ይጸናል ስንል እያልን ያለነው፣ በልበ ደንዳናነት ክርስቶስን ወደ መካድ ልንደርስ አንችልም ነው፤ ካልሆነ ግን ባመንነው እምነት ግብዞች እንደሆንን እንመሰክራለን። ለዚህ ዐይነት ድንዳኔ ምሳሌ የሚሆነን ኤሳው ነው።

> ከእናንተ ማንም የእግዚአብሔር ጸጋ እንዳይጐድልበት ደግሞም መራራ ሥር በቅሎ ችግር እንዳያስከትልና ብዙዎችን እንዳይበክል ተጠንቀቁ። ለአንድ ጊዜ መብል ሲል ብኵርናውን እንደ ሸጠው እንደ ዔሳው ማንም ሴሰኛ ወይም እግዚአብሔርን የማያከብር ሆኖ እንዳይገኝ ተጠንቀቁ። በኋላም ይህንኑ በረከት ሊወርስ በፈለገ ጊዜ፣ እንደ ተከለከለ ታውቃላችሁ፤ በረከቱን በእንባ ተግቶ ቢፈልግም መልሶ ሊያገኘው አልቻለም። (ዕብ. 12፥15-17)

ኤሳው ለዚህ ዓለም ባለው ፍቅር መንፈሰ ደንዳና እና ቈዳው የደደረ ሆኗል፤ ከዚህ የተነሣ ንስሓ ለመግባት በሞከረ ጊዜ አልቻለም።

ይልቁን ማድረግ የቻለው ከእግዚአብሔር የተሰጠውን ብኩርና በምስር ወጥ በመለወጡ፣ ለእግዚአብሔር ያሳየውን ዐመፅ እና ኀጢአቱን ከመጥላት ይልቅ በሞኝነቱ ስለደረሰበት ነገር ማልቀስ ብቻ ነው።

በሌላ በኩል በኀጢአት መጽናትን እና መድከምን አንድ አድርገን በማሰብ ተስፋ እንዳልቈረጥን ለማረጋገጥ ዐዲስ ኪዳን ይተጋል። ንስሓ እና መመለስ ይቻላል። በኀጢአት መውደቅ እና በንሰሓ የመመለስ ሂደት በ"ቅዱሳን ጽናት" የተካተተ ነው። ለምሳሌ ያዕቆብ እንዲህ ይላል፣ "ይህን አስተውሉ፤ ኀጢአተኛን ከተሳሳተበት መንገድ የሚመልስ ሰው ነፍሱን ከሞት ያድነዋል፤ ብዙ ኀጢአትንም ይሸፍናል" (ያዕቆብ 5፥20)። እንዲሁም ዮሐንስ እንዲህ ይላል፣ "ማንም ሰው ወንድሙ ለሞት የማያበቃ ኀጢአት ሲያደርግ ቢያየው ይጸልይ፤ እግዚአብሔርም ለሞት የማያበቃ ኀጢአት ላደረጉት ሕይወትን ይሰጣል። ለሞት የሚያበቃም ኀጢአት አለ፤ ስለዚህኛው ግን ይጸልይ አልልም። ዐመፅ ሁሉ ኀጢአት ነው፤ ለሞት የማያበቃም ኀጢአት አለ" (1ኛ ዮሐንስ 5፥16-17)። እዚህ ጋር የዮሐንስ ዐላማ፣ ተስፋ በመቍረጥ ፈተና ውስጥ ላሉት፣ እንዲሁም እነርሱን ለሚወዷቸው እና ለሚጸልዩላቸው ተስፋን መስጠት ነው። ዮሐንስ መልእክቱን በጨረሰበት በተመሳሳይ መንገድ መልዕክቱን እንዲህ ሲል ይጀምራል፣ "ኀጢአት የለብንም ብንል፣ ራሳችንን እናስታለን፤ እውነትም በእኛ ውስጥ የለም። ኀጢአታችንን ብንናዘዝ ኀጢአታችንን ይቅር ሊለን፣ ከዐመፃ ሁሉ ሊያነጻን እርሱ ታማኝና ጻድቅ ነው።" (1ኛ ዮሐንስ 1፥8-9)

ስለዚህ ስለ ቅዱሳን ጽናት አስፈላጊነት (እና ርግጠኝነት) ስናነሣ፣ ፍጹምነት ማለታችን አይደለም። በሕይወታችን ምንም ዐይነት ትግል እና ያለማመን ፈተና አይኖርም ማለት አይደለም። ቀደም ሲል በዚህ መጽሐፍ የተመለከትነውን ማስታወስ አለብን። የክርስቶስ መሆን፣ በእግዚአብሔር የሚደረግ እና በእርሱም የሚጠበቅ ልዕለ ተፈጥሯዊ ሐቅ ነው (ኤር. 32፥40)። ቅዱሳን በአብዛኛው የሚታወቁት በሚያደርጉት ሳይሆን በማንነታቸው ነው። እነርሱ ዳግመኛ የተወለዱ ናቸው። ዐዲስ ፍጥረት ናቸው። ከዚህ ዐዲስነት ወደ ውጭ እና ወደ ውስጥ አይመላለሱም። ይህም የእግዚአብሔር ግብር ስለሆነ አይለወጥም።

ነገር ግን የዚህ ዐዲስ ማንነት ፍሬ፣ በእምነትና በመታዘዝ እስከ መጨረሻው ድረስ መታገል ነው። የቅዱሳን ጽናት ትምህርት እንዲህ ይላል፤ ትግሉን እንታገላለን፤ በስተመጨረሻም አንሸነፍም።

## 2. መታዘዝ፣ ከእግዚአብሔር ዘንድ የሆነን ውስጣዊ መታደስ በማረጋገጥ፣ ለመጨረሻው ድነት አስፈላጊ ነው።

እግዚአብሔር ከእኛ ፍጽምናን ይፈልጋል ለማለት አይደለም። ዐዲስ ኪዳን በእምነት በክርስቶስ ኢየሱስ የሆኑት፣ በስተመጨረሻ ለመዳን ኀጢአት አልባ ፍጹማን ሆነው ሊኖሩ ይገባል እንደማይል ከፊልጵሲዩስ 3፥12 ግልጽ ይሆናል። “ይህን ሁሉ አግኝቻለሁ ወይም ፍጹም ሆኛለሁ ማለት አይደለም፤ ነገር ግን ክርስቶስ ኢየሱስ እኔን የራሱ ያደረገበትን ያን፣ እኔም የራሴ ለማድረግ እጣጣራለሁ።” (በተጨማሪም 1ኛ ዮሐንስ 1፥8-10 እና ማቴዎስ 6፥12 ይመ.)። ይሁን እንጂ ዐዲስ ኪዳን በግረገብ ተለውጠን፣ በዐዲስ ሕይወት እንድንራመድ ያዘናል። ለምሳሌ፡-

- “ከሰው ሁሉ ጋር በሰላም ለመኖር የሚቻላችሁን ሁሉ አድርጉ፤ ለመቀደስም ፈልጉ፤ ያለ ቅድስና ማንም ጌታን ማየት አይችልም” (ዕብራውያን 12፥14)
- *“እንደ ሥጋ ብትኖሩ ትሞታላችሁና፤ ከፉ የሆነውን የሥጋ ሥራ በመንፈስ ብትገድሉ ግን፣ በሕይወት ትኖራላችሁ፤”* (ሮሜ 8፥13)
- *“የሥጋ ሥራ ግልጽ ነው፡- ይኸውም ዝሙት፣ ርኩሰት፣ መዳራት፣ ጣዖትን ማምለክ፣ ሟርት፣ ጥላቻ፣ ጠብ፣ ቅናት፣ ቍጣ፣ ራስ ወዳድነት፣ መለያየት፣ አድመኝነት፤ ምቀኝነት፣ ስካር፣ ዘፋኝነት፣ እንዲሁም እነዚህን የመሰለው ነው። አስቀድሜ እንዳልሁ፣ አሁንም አስጠነቅቃችኋለሁ፤ በእንዲህ ሁኔታ የሚኖሩ ሁሉ የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርሱም።”* (ገላ. 5፥19-21። በተጨማሪ ኤፌሶን 5፥5 እና 1ኛ ቆሮንቶስ 6፥10)

- “ትእዛዛቱን ብንፈጽም እርሱን ማወቃችንን በዚህ ርግጠኞች እንሆናለን። “እርሱን ዐውቃለሁ” እያለ ትእዛዙን የማይፈጽም ግን ሐሰተኛ ነው፤ እውነትም በእርሱ ውስጥ የለም። ነገር ግን ማንም ቃሉን ቢጠብቅ፣ በእውነት የእግዚአብሔር ፍቅር በእርሱ ፍጹም ሆኖአል። በእርሱ መሆናችንን የምናውቀው በዚህ ነው፤ ማንም በእርሱ እኖራለሁ የሚል፣ ኢየሱስ እንደ ተመላለሰ ሊመላለስ ይገባዋል።” (1ኛ ዮሐንስ 2፥3-6 በተጨማሪ 1ኛ ዮሐንስ 3፥4-10፣ 14፤ 4፥20)
- “ኢየሱስም በእርሱ ያመኑትን አይሁድ እንዲህ አላቸው፤ “በትምህርቴ ብትጸኑ እናንተ በእውነት ደቀ መዛሙርቴ ናችሁ።”” (ዮሐንስ 8፥31 በተጨማሪ ሉቃስ 10፥28፤ ማቴዎስ 6፥14-15፤ 18፥35፤ ዘፍ. 18፥19፤ 22፥16-17፤ 26፥4-5፤ 2ኛ ጢሞቴዎስ 2፥19)

በድጋሚ እነዚህን ምንባቦች ማንም በፍጽምና አቅጣጫ እንዳይወስድ ጥንቃቄ ሊደረግ ይገባል። የመጀመሪያው የዮሐንስ መልእክት የተጻፈው እዚህ ላይ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሚዛናችንን ለማስጠበቅ ነው። በአንድ በኩል፣ “ከእግዚአብሔር የተወለደ ሁሉ ኀጢአትን አያደርግም፤ የእርሱ ዘር በውስጡ ይኖራልና፤ ከእግዚአብሔር ስለ ተወለደም ኀጢአትን ሊያደርግ አይችልም” (1ኛ ዮሐንስ 3፥9) ይለናል። በሌላ በኩል ደግሞ፣ “ኀጢአት የለብንም ብንል፣ ራሳችንን እናስታለን፤ እውነትም በእኛ ውስጥ የለም።” (1ኛ ዮሐንስ 1፥8) እንዲሁም *“ልጆቼ ሆይ፤ ይህን የምጽፍላችሁ ኀጢአት እንዳትሠሩ ነው፤ ነገር ግን ማንም ኀጢአት ቢሠራ፣ በአብ ዘንድ ጠበቃ አለን፤ እርሱም ጻድቁ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው”* (1ኛ ዮሐንስ 2፥1) ይለናል።

የቅዱሳን ጽናት አስተምህሮ ለፍጽምና ዋስትና አይደለም፤ ይልቁንም ኀጢአትን እንድንጠላ፣ ከኀጢአት ጋርም ምንም ዐይነት ዘላቂ ሰላም እንዳይኖረን ለማድረግ፣ የእምነትን ውጊያ እየተዋጋን እንድንቀጥል ያደርገናል።

## 3. የእግዚአብሔር ምርጦች ሊጠፉ አይችሉም።

በዚህ ምክንያት ነው በዘላለማዊ ዋስትና፣ ማለትም በምርጦቹ ዘላለማዊ ዋስትና የምናምነው። የሚያመለክተውም፣ እግዚአብሔር ለዘላለም ድነት የመረጣቸውን እነዚያን እስከ መጨረሻው በእምነት እንዲጸኑ እና ለዐዲስ ዐይነት ሕይወት የሚያስፈልጉ ነገሮችን በመንፈስ ቅዱስ ኀይል እንዲያሟሉ እግዚአብሔር በእነርሱ ውስጥ ይሠራል ማለት ነው።

ቀደም ብለን በሮሜ 8፥30 ላይ ያለውን ሰንሰለታማውን የመለኮት ግብር ተመልከተናል፤ "አስቀድሞ የወሰናቸውን ጠራቸው፤ የጠራቸውን አጸደቃቸው፤ ያጸደቃቸውን አከበራቸው።" ከዚህ ቍጥር ግልጽ የሚሆነው ነገር፣ እነዚያ ወደ ድነት ተስፋ በውጤታማነት የተጠሩ በርግጥም እስከ መጨረሻው ይጸናሉ፤ ደግሞም ይከብራሉ። ከዚህ ሰንሰለት አቋርጠው የሚወጡ የሉም። ቀደም ብለን እንደተመከትነው፣ እነዚህ ከሁሉም በፊት በሁኔታ አልባ ምርጫ፣ በሉዓላዊው፣ በሚለውጠው እና በሚያጸናው ጸጋ ውስጥ የተተከሉ የእግዚአብሔር የተስፋ ቃሎች ናቸው። የዚህ ሰንሰለት ቀለበቶች የማይሰበሩ ናቸው፤ ምክንያቱም የእግዚአብሔር የማዳን ሥራ የማይሻር ነው፤ ለዐዲሱ ኪዳን ያለውም ታማኝነት የማይቀለበስ ነው።

በድጋሚ፣ ጳውሎስ የጌታውን ትምህርት እየተከተለ ነው፤

> "በጎቼ ድምፄን ይሰማሉ፤ እኔ ዐውቃቸዋለሁ፤ እነርሱም ይከተሉኛል፤ እኔ የዘላለም ሕይወት እሰጣቸዋለሁ፤ ከቶ አይጠፉም፤ ከእጀም ሊነጥቃቸው የሚችል ማንም የለም። እነርሱን የሰጠኝ አባቴ ከሁሉ ይበልጣል፤ ከአባቴም እጅ ማንም ሊነጥቃቸው አይችልም። እኔና አብ አንድ ነን።" (ዮሐንስ 10፥27-30 በተጨማሪ ኤፌሶን 1፥4-5)

የኢየሱስ በግ መሆን ማለት በእግዚአብሔር መመረጥ እና ለወልድ መሰጠት እንደሆነ ቀደም ሲል ተመልከተናል። በሌላ አገላለጽ፣ ከበጎቹ ማንም እንደማይጠፋ ኢየሱስ የሰጠው ተስፋ፣ የእግዚአብሔር ልጅ ነፍሱን ያኖረላቸውን የምርጦቹን እምነት ለመጠበቅ የገባው ሉዓላዊ ኪዳን ነው።

## 4. የአማኞች መውደቅ አለ፤ ነገር ግን ውድቀታቸው ከጸና፣ እምነታቸው እውነተኛ እንዳልነበረ እና እነርሱም ከእግዚአብሔር እንዳልተወለዱ ያሳያል።

1ኛ ዮሐንስ 2፥19 እንዲህ ይላል፣ "ከእኛ መካከል ወጡ፤ ይሁን እንጂ ከእኛ ወገን አልነበሩም፤ ከእኛ ወገን ቢሆኑማ ኖሮ ከእኛ ጋር ጸንተው በኖሩ ነበር። ነገር ግን ሁሉም ከእኛ ወገን እንዳልነበሩ ይታወቅ ዘንድ ከእኛ ተለዩ።" በተመሳሳይ በሉቃስ 8፥9-14 የተፈታው የአራቱ መሬቶች ምሳሌ የሚገልጻቸው ሰዎች "በድንጋያማ ቦታ ላይ የወደቀውም ቃሉን ሲሰሙ በደስታ የሚቀበሉ ናቸው፤ እነዚህ ለጊዜው ያምናሉ እንጂ ሥር ስለሌላቸው በፈተና ጊዜ ፈጥነው የሚክዱ ናቸው።"

እንዲህ ያለው ነገር የሚቻል በመሆኑ ምክንያት ነው ምዕመናን በእምነት እንዲጸኑ፣ ኩነኔን ከሚያስከትሉ አሰናካይ ነገሮች ጋር እንዳይጣበቁ፣ በሁሉም አጥቢያ ቤተ ክርስቲያናት የወንጌል አገልግሎት ላይ በርካታ ማሳሰቢያዎችን እና ምክሮችን ማካተት የሚገባው። መጋቢዎች ከአድማጮቹ መካከል የትኞቹ መልካም፣ የትኞቹ ደግሞ መጥፎ መሬት እንደሆኑ በትክክል ሊያውቁ አይችሉም። የእነርሱ ማስጠንቀቂያዎች እና ምክሮች ቅዱሳን በእምነት እንዲጸኑ የሚረዳበት መንገድ ነው። እነርሱም ማስጠንቀቂያዎቹን ይሰማሉ፤ ይቀበላሉ፤ በዚህም ትሑትና መልካም የእምነት ልብ እንዳላቸው ያረጋግጣሉ።

## 5. እግዚአብሔር የሚያጸድቀን በመጀመሪያው እምነት ነው፤ ነገር ግን እምነት የሚጸና እና "በእምነት መታዘዝ" ፍሬ የሚያፈራ ነው።

ከላይ አጽንዖት የተሰጠባቸው የእምነት መጽናት እና የመታዘዝ አስፈላጊነት፣ እግዚአብሔር በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ውስጥ በመሆናችን ሙሉ በሙሉ መጽደቃችንን ከማወጁ አስቀድሞ መጽናታችንን እና መታዘዛችንን ይመለከታል ማለት አይደለም። ሮሜ 5፥1 *"በእምነት ስለ ጸደቅን"* ይላል። ይህ በዐላፊ ጊዜ የተገለጸ ድርጊት ነው። መጀመሪያ በኢየሱስ ክርስቶስ ባመንን ጊዜ ከእርሱ ጋር አንድ ሆነናል። ከእርሱ ጋር ባለን አንድነት፣ የእርሱ ጽድቅ በዚያች ቅጽበት ለእኛ ተቈጥሮልናል።

ጳውሎስ ዐላማውን እንዲህ ይገልጻል፣ “ሕግ በመጠበቅ የሚገኝ የራሴ ጽድቅ ኖሮኝ ሳይሆን፣ በክርስቶስ በማመን ይኸውም ከእግዚአብሔር የሚመጣ፣ ከእምነትም በሆነ ጽድቅ በእርሱ ዘንድ እንድገኝ ነው” (ፊል. 3፥9)።

በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት የማግኘታችን መሠረት ክርስቶስ ብቻ ነው— የእርሱ ደምና ጽድቅ ነው። “እኛ በእርሱ ሆነን የእግዚአብሔር ጽድቅ እንድንሆን፣ ኀጢአት የሌለበትን እርሱን እግዚአብሔር ስለ እኛ ኀጢአት አደረገው።” (2ኛ ቆሮንቶስ 5፥21) “በአንዱ ሰው መታዘዝ ደግሞ ብዙዎች ጻድቃን ይሆናሉ።” (ሮሜ 5፥19) የእምነታችን ሚና ድነትን ከእግዚአብሔር ሊያሸልሙ የሚችሉ መልካም ሥራዎችን መሥራት አይደለም። ይልቁንም እምነት፣ እኛ የማንችለውን የኀጢአታችንን ቅጣት ተሸክሞ ጽድቅን ያስገኘልንን ክርስቶስ መቀበል ነው። እምነት ተቀባይነት የማግኘታችን መሠረት አይደለም፤ ነገር ግን በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት የማግኘታችን ብቸኛ ምክንያት ከሆነው ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር የምንተባበርበት መንገድ ወይም መሣሪያ ነው።

በጽደቃችን ውስጥ የመታዘዝ ሚና፣ እምነታችን እውነተኛ መሆኑን ማሳየት ነው። የፍቅር ተግባሮች በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት ለማግኘታችን የመጀመሪያም የመጨረሻም መሠረት አይደሉም። የእነዚህ ድርጊቶች ዋነኛ ጥቅም ዐዲስ ልደት የሰጠንን እና የእምነትን ዐዲስ ልብ የፈጠረልንን ሉዓላዊውን የእግዚአብሔርን ሥራ ማረጋገጥ እና መግለጥ ነው። ጳውሎስ ይህን እንዲህ ያስቀምጠዋል፣ “በክርስቶስ ኢየሱስ ከሆኑ፣ መገረዝ ወይም አለመገረዝ አይጠቅምምና፤ የሚጠቅመውስ በፍቅር የሚገለጽ እምነት ብቻ ነው” (ገላ. 5፥6)። በመጽደቅ ውስጥ እግዚአብሔር የሚቈጥረው፣ በፍቅር የሚሠራን እምነት ነው። እግዚአብሔር ሙሉ ለሙሉ ለእኛ እንዲሆን ያደረገው ፍቅራችን አይደለም። በክርስቶስ ባለን እምነት እርሱ በሙሉ ለእኛ በመሆኑ ነው እርሱን እንድንወደው ያስቻለን። ፍቅር የመንፈስ ፍሬ ነው። ይህን መንፈስ በመጀመሪያው የእምነት ተግባር ተቀብለናል (ገላ. 3፥2)።

ስለዚህ በእምነት የመጽናት እና ለመጨረሻው መዳን የመታዘዝ አስፈላጊነት፣ እግዚአብሔር እኛን ከመቀበል፣ ልጆቹ ከማድረጉ እና ከመቀበሉ አስቀድሞ እስከ መጨረሻው ይጠብቃል ማለት አይደለም።

የእምነትን ውጊያ የምንዋጋው እግዚአብሔር ሙሉ በሙሉ ለእኛ እንዲሆን ለማድረግ አይደለም። መጀመሪያ በክርስቶስ ኢየሱስ ስናምን ይህ ተከስቷል። ይልቁንም የምንዋጋው ሙሉ በሙሉ እርሱ ለእኛ ስለሆነ ነው። ጳውሎስ በፊል 3፥12 እንዲህ አስቀምጦታል፣ "ይህን ሁሉ አግኝቻለሁ ወይም ፍጹም ሆኛለሁ ማለት አይደለም፤ ነገር ግን *ክርስቶስ ኢየሱስ እኔን የራሱ ያደረገበትን ያን*፣ እኔም የራሴ ለማድረግ እጣጣራለሁ።" ክርስቶስ የራሱ አድርጎናል። የምንዋጋው እንዲህ ነው። ሁሉም እንደየሥራው በሚቀበልበት በመጨረሻው ፍርድ፣ በፍርድ ዙፋኑ ፊት ከጽድቅ ጋር ተያይዞ የምንመዘንበት መልካም ሥራ ዋና ዐላማ፣ በውስጣችን ያለውን የማይታየውን እምነት እና ከክርስቶስ ጋር ያለንን አንድነት ለመግለጥ ብሎም ለማረጋገጥ ነው። ያኔም ቢሆን ተቀባይነት የምናገኝበት ብቸኛ መሠረት ክርስቶስ ይሆናል።

## 6. እግዚአብሔር የመረጣቸውን ለማጽናት ይሠራል።

በእምነት ለመጽናት ከኀጢአት ጋር በምናደርገው ውጊያ፣ እኛ ለራሳችን አልተተውንም። የመጽናታችን ማረጋገጫ የተመሠረተው፣ የተጠራንበትን ዐላማ እንድንፈጽም በሚስያችለን በሉዓላዊው የእግዚአብሔር ፍቅር ነው። ከዚህ ተከትሎ የምንመለከታቸው ምንባቦች ሁሉ በምዕራፍ ዐምስት ላይ የተመለከትነው የዐዲሱ ኪዳን መገለጫዎች ናቸው። ኢየሱስ ደሙን ሲያፈስ እግዚአብሔር የገባልንን የተስፋ ቃሎች ሁሉ አስገኝቶልናል (ሉቃስ 22፥20፤ 2ኛ ቆሮንቶስ 1፥20)።

ከእነዚህ ውስጥ አንዱ፣ ዐዲሱን ኪዳን እስከ መጨረሻው ሊያጸናን ከሚተጋው ከእግዚአብሔር ፍጹም መስጠት ጋር ያገናኘዋል። "መልካምን ነገር ለእነርሱ ከማድረግ እንዳልቈጠብና *ከእኔም ፈቀቅ እንዳይሉ መፈራቴን በውስጣቸው ላኖር* ከእነርሱ ጋር የዘላለም ቃል ኪዳን እገባለሁ" (ኤር. 32፥40)። ይህ ተስፋ በብዙ አስደናቂ አገላለጾች በዐዲስ ኪዳን ውስጥ ይደጋገማል፣

- *"እናንተም በመጨረሻው ዘመን ሊገለጥ የተዘጋጀው ድነት እስኪመጣ ድረስ በእምነት አማካይነት በእግዚአብሔር ኀይል ተጠብቃችኋል።"* (1ኛ ጴጥ. 1፥ 5)
- *"እንዳትወድቁ ሊጠብቃችሁና ያለ ነቀፋና በደስታ በክብሩ ፊት ሊያቀርባችሁ ለሚችለው፣ እርሱ ብቻ አዳኛችን ለሆነው አምላክ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ከዘመናት ሁሉ በፊት፣ አሁንና እስከ ዘላለምም ድረስ ክብር፣ ግርማ፣ ኀይልና ሥልጣን ይሁን፤ አሜን"* (ይሁዳ 24-25)
- *"የሰላም አምላክ ራሱ ሁለንተናችሁን ይቀድስ፤ መንፈሳችሁ፣ ነፍሳችሁና ሥጋችሁ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሚመጣበት ጊዜ ያለ ነቀፋ ይጠበቁ። የጠራችሁ የታመነ ነው፤ እርሱም ያደርገዋል።"* (1ኛ ተሰ. 5፥23-24)
- *"በእናንተ መልካምን ሥራ የጀመረው እርሱ እስከ ክርስቶስ ኢየሱስ ቀን ድረስ ከፍጻሜው እንደሚያደርሰው ርግጠኛ ነኝ። "* (ፊል. 1፥6)
- *"በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ቀን ያለ ነቀፋ እንድትገኙ እርሱ እስከ መጨረሻው ድረስ አጽንቶ ይጠብቃችኋል። ወደ ልጁ፣ ወደ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ኅብረት የጠራችሁ እግዚአብሔር የታመነ ነው።"* (1ኛ ቆሮ. 1፥8-9)
- *"በዘላለም ኪዳን ደም የበጎች ታላቅ እረኛ የሆነውን ጌታችን ኢየሱስን ከሞት ያስነሣው የሰላም አምላክ፣ ፈቃዱን እንድታደርጉ በመልካም ነገር ሁሉ ያስታጥቃችሁ፤ ደስ የሚያሰኘውንም በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል በእኛ ያድርግ፤ ለእርሱ እስከ ዘላለም ድረስ ክብር ይሁን፤ አሜን።"* (ዕብ. 13፥ 20-21)

አንዳንድ ጊዜ ሰዎችን እንዲህ ስል እጠይቃለሁ። ነገ ጠዋት ከእንቅልፍህ ክርስቲያን እንደሆንህ እንደምትነቃ ለምን ታምናለህ? ነገ ስትነቃ የሚያድነው እምነት በውስጥህ እንደሚኖር ብለህ ለምን ታስባለህ? ይህን ጥያቄ የማቀርበው፣ አንድ ሰው ስለ ቅዱሳን ጽናት ምን ዐይነት አመለካከት እንዳለው ለማወቅ ነው።

ለዚህ ጥያቄ መጽሐፍ ቅዱሳዊው መልስ፣ ነገ ጠዋት ለማመን እንደምመርጥ ስለማውቅ ነው፤ ለኢየሱስ እጅግ የተሰጠሁ ትጉህ ነኝ የሚል አይደለም። ይህ እጅግ ደካማ በራስ መተማመን ነው።

ትክክለኛው መልስ ከላይ በቀረቡት ምንባቦች ውስጥ ይገኛል። እግዚአብሔር የታመነ ነው። እግዚአብሔር በእኔ ውስጥ ይሠራል። እግዚአብሔር ይጠብቀኛል። እግዚአብሔር በእኔ የጀመረውን ሥራ ከፍጻሜ ያደርሰዋል። መልሱ፣ "ቀጣይነት ያለው የእኔ ትጋት ሳይሆን፣ ቀጣይነት ያለው የእግዚአብሔር ሥራ ነው" የሚል ነው። ይህን ጥያቄ ስጠይቅ፣ የዘላለም ዋስትናን እንደ ክትባት የሚመለከቱ ካሉም አጣራለሁ። "በተለወጥንበት ወቅት ያለማመን ክትባታችንን አግኝተናል፤ ስለሆነም ባለማመን በሽታ አንያዝም።" ይህ ወደ ስሕተት የሚመራ አገላለጽ ነው፤ ምክንያቱም የቅዱሳን ጽናት ሂደት ቀጣይነት ካለው ከታላቁ ሐኪም ሥራ ውጭ አውቶማቲክ እንደሆነ አድርጎ ያቀርባል። የቅዱሳን ጽናት እንደ ክትባት አይደለም፤ ታላቁ ሐኪም ሁልጊዜ ከእኛ ጋር የሚሆንበት የሕይወት ዘመን ሕክምና ነው። እርሱ ፈጽሞ አይተወንም (ዕብ. 13፥5)። የምንጸናው በዚህ መንገድ ነው። ርግጠኝነትም የምናገኘው እንዲህ ባለ መንገድ ነው።

## 7. መጠራታችንን እና መመረጣችንን ለማጽናት ቀናተኛ መሆን አለብን።

2ኛ ጴጥ 1፥10-11 እንዲህ ይላል፣ "ስለዚህ ወንድሞች ሆይ፤ መጠራታችሁንና መመረጣችሁን ለማጽናት ከፊት ይልቅ ትጉ፤ ምክንያቱም እነዚህን ብታደርጉ ከቶ አትሰናከሉም፤ በዚህም ወደ ጌታችንና አዳኛችን ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ ዘላለማዊ መንግሥት መግባት በሙላት ይሰጣችኋል።" የጴጥሮስ ዐሳብ፣ መመረጣችን እና መጠራታችን ተሰባሪ ስለሆኑ ድጋፍ ይፈልጋሉ የሚል አይደለም። ለምሳሌ በሮሜ 8፥29-30 መመረጣችንና መጠራታችን የማይሻሩ እውነታዎች መሆናቸውን ተመልክተናል። እነዚህ በማይበጠሰው የደኅንነት ሰንሰለት ቀለበት ናቸው።

ጴጥሮስ እያለ ያለው ይህን ነው፤ መመረጣችሁንና መጠራታችሁን ለማጽናት ትጉ፤ ከመመረጣችሁና ከመጠራታችሁ በሚመነጭ ደስታ በመመላለስ በቀጣይነት አረጋግጡ።

በቀደሙት ቍጥሮች ይህን ያብራራል፤ እግዚአብሔር “በገዛ ክብሩና በበጎነቱ የጠራንን እርሱን በማወቅ ለሕይወትና ለእውነተኛ መንፈሳዊነት የሚያስፈልገንን ሁሉ የመለኮቱ ኀይል ሰጥቶናል” (2ጴጥ. 1፥3)። መመረጣችንንና መጠራታችንን እንድናረጋግጥ ለራሳችን አልተወንም።

በመለኮቱ ኀይል በእምነት፣ በበጎነት፣ በዕውቀት፣ ራስን በመግዛት፣ በመጽናት፣ እግዚአብሔርን በመምሰል፣ በወንድማማች መዋደድ እና በፍቅር እናድጋለን። (2ኛ ጴጥሮስ 1፥5-7) በሌላ አገላለጽ፣ በመንፈስ ቅዱስ ኀይል በእኛ ሕይወት ኀጢአት እንደሞተ፣ ደግሞ የፍቅር ግብ በደስታ በእኛ እንደተፈለገ(pursued) የሚገልጸውን፣ የእግዚአብሔርን ኀይል እና የተስፋ ቃሎቹን ከልባችን ለማመን እንተጋለን። በፍቅር የሚሠራ እምነት (ገላትያ 5፥6) መጠራታችንን እና መመረጣችንን የምናረጋግጥበት መንገድ ነው።

## 8. መጽናት የማኅበር ሥራ ነው

እግዚአብሔር የእምነትን ተጋድሎ ለብቻችሁ ታገሉ አላለንም። አንዳችን ለአንዳችን እንታገላለን። ጳውሎስ ስለተመረጡት በእምነት መጽናት ከተናገራቸው አስደናቂ ምንባቦች ውስጥ 2ኛ ጢሞቴዎስ 2፥10 አንዱ ነው፤ “ስለዚህ በክርስቶስ ኢየሱስ ያለውን መዳን ከዘላለም ክብር ጋር እነርሱም ያገኙ ዘንድ፣ ለተመረጡት ስል ሁሉንም በመታገሥ እጸናለሁ።” ይህ ለብዙዎች አስደናቂ ነው። የተመረጡት በክርስቶስ ያለውን መዳን ከዘላለም ክብር ጋር እንደሚያገኙ ርግጥ አይደለም እንዴ? ርግጥ ነው። ያጸደቃቸውን እነዚህን ደግሞ አከበራቸው።

ጥያቄው፣ ይህ የመጨረሻው ነጥብ ሊያጠፋ የሚያስበውን ወሳኝ እሳቤ ይከዳል፤ ይኸውም አንዳንድ የተረጋገጡ ውጤቶች ወደእነርሱ መልፋት አስፈላጊ እንዳልሆነ ያመለክታሉ የሚል ነው። ይህ እሳቤ ስሕተት ነው። ድነት ለእግዚአብሔር ምርጦች ርግጥ ነው። ሊጨናገፍ አይችልም። እግዚአብሔር ርግጥ ያደረገበት መንገድ ደግሞ ሰውን በኀይል አስታጥቆ ለእምነት በሚደረገው ተጋድሎ ውስጥ እንዲተባበር በማድረግ ነው። ጳውሎስ የቃሉን አገልግሎት የሚመለከተው፣ ለተመረጡት መጽናት አስፈላጊ እንደሆነ አድርጎ ነው።

ቀላል ምሳሌ ተመልከቱ። ጣውላ ላይ ምስማር ተመቶ እንዲገባ እግዚአብሔር ወስኗል እንበል፤ ይህ እንደሚሆን ርግጥ ነው። እግዚአብሔር አምላክ ነው፤ ይህን ደግሞ አቅዶታል። ታዲያ ይህ ማለት መዶሻውን ያገለለ ነው? አይደለም። ምስማሩ በመዶሻ ተመቶ ወደ እንጨቱ የሚገባበትንም መንገድም እግዚአብሔር ወስኗል።

በተመሳሳይ፣ የተመረጡት በዘላለማዊው ክብር በመጨረሻ እንደሚድኑ ርግጥ ነው። እግዚአብሔር የተመረጡትን ያለ ቃሉ ስብከት ወደዚያ ያስገባቸዋል ማለት ነው? አይደለም። እግዚአብሔር ይህን ወሳኝ አድርጎታል። ይህ የድነትን ርግጠኝነት የማያሳንስበት ምክንያት፣ እግዚአብሔር በፍጻሜ ላይ ሉዓላዊ እንደሆነው ሁሉ፣ በመንገዱም ላይ ሉዓላዊ በመሆኑ ነው።

ይህ እውነት በዕብራውያን 3፥12-13 ለሁላችን እንደሆነ እንመለከታለን፤ “ወንድሞች ሆይ፤ ከእናንተ ማንም ከሕያው እግዚአብሔር የሚያስኰበልል፣ ኀጢአተኛና የማያምን ልብ እንዳይኖረው ተጠንቀቁ። ነገር ግን ከመካከላችሁ ማንም በኀጢአት ተታሎ ልቡ እንዳይደነድን፣ ‘ዛሬ’ እየተባለ ሳለ በየቀኑ እርስ በርሳችሁ ተጽናኑ።” ከመረጣቸው ውስጥ አንዳቸውም እንዲጠፉ እግዚአብሔር አይፈቅድም፤ ነገር ግን እንዳንጠፋ የሚጠብቅበት መንገድ ሕይወታችንን በሌሎች አማኞች በማበርታት ነው። ይህ ለቤተ ክርስቲያን ሊከፈሉ ከሚችሉ ትልቅ ዋጋዎች አንዱ ነው። እግዚአብሔር ምርጦቹን እስከ መጨረሻው የሚጠብቅበት መሳሪያ የክርስቶስ አካል እንድትሆን ወስኗል።

እስከ መጨረሻው የሚያጸናንን የእግዚአብሔር ጸጋ በጥልቀት እንደምትረዱት ተስፋ በማድረግ እና በጸሎት ይህን ምዕራፍ እንዘጋለን። ይህን እውነት ካሰላሰላችሁት እና ወደ ውስጣችሁ ካሰረጋችሁት፣ የዘላለም ዋስትናን ውጫዊ እና እንደ ክትባት አንዴ የሚሆን አድርገው ከሚያቀርቡት አመለካከቶች ይልቅ፣ ኪዳኑንን የሚጠብቀው የእግዚአብሔር ጸጋ በጣም የላቀ፣ ጠንካራ እና ጣፋጭ የርግጠኝነት መሠረት ሆኖ ታገኙታላችሁ።

እግዚአብሔር እንደመረጣችሁ፣ እንደጠራችሁ፣ እምነትን እንደሰጣችሁ፣ ፈጽሞ እንደማይተዋችሁ፣ እስከ መጨረሻው እንደሚያጸናችሁ እና በታላቅ ደስታ በክብሩ ዙፋን ፊት ያለ ነውር እንደሚያቀርባችሁ በማወቅ ርግጠኛ መሆን በምንም ነገር የማይበገር ደስታ፣ ጥንካሬ እና ትጋት ወደ ሕይወታችሁ ያመጣል። የሚያጸናውን መለኮታዊ ጸጋ በጥልቀት ወደመረዳት እግዚአብሔር ያስገባችሁ።

# የግል ምስክርነት

## (ዐምስቱ አዕማድ አስተምህሮች በሕይወቴ ያሳደሩት ተጽእኖ)

የሚከተሉት ዐሥር ነጥቦች የካልቪኒዝምን ዐምስቱን ነጥቦች፣ ማለትም የጸጋ አስተምህሮች ማመን ስለሚያሳድረው ተጽእኖ የግል ምስክርነቴ ናቸው።

### 1. እነዚህ እውነቶች እግዚአብሔርን በመፍራት እንድቆም እና እግዚአብሔርን ማዕከል ወዳደረገ እውነተኛ አምልኮ ይመሩኛል።

በ1970ዎቹ መገባደጃ ላይ በቤቴል ኮሌጅ የኤፌሶንን መልእክት ሳስተምር፣ ሁሉንም የእግዚአብሔር ሥራዎች ግብ የሚገልጽ፣ የሦስትዮሽ ዐረፍተ ነገር ለመጀመሪያ ጊዜ የተመለከትኩበትን ጊዜ አስታውሳለሁ፤ እንዲህ ይላል፣ “ክቡር የሆነው ጸጋው እንዲመሰገን ነው።” (ኤፌሶን 1፥6፡12፡14)

ለእግዚአብሔር ምንም መጨመር እንደማንችል እና የእርሱ ክብር ደምቆ የሚበራው፣ *አስፈልጎቶቹን* ለማሟላት በመሞከር ሳይሆን፣ በእርሱ መርካትን የሥራዎቻችን ማዕከል ስናደርግ እንደሆነ ወደ መመልከት መርቶኛል። “ሁሉም ከእርሱ፣ በእርሱ፣ ለእርሱ ነውና፤ ለእርሱ ለዘላለም ክብር ይሁን፤ አሜን።” (ሮሜ 11፥36) አምልኮ በራሱ ግብ ይሆናል።

ይህ መረዳት ለእግዚአብሔር ያለኝ ፍቅር ምን ያህል ዝቅተኛና አነስተኛ መሆኑ እንዲሰማኝ አድርጎኛል፤ ከዚህ የተነሣ የናፍቆት መዝሙሮች ሕይወት ዘርተው አምልኮዬ ጥልቅ ሆኗል።

### 2. እነዚህ እውነቶች ከመለኮታዊ ነገሮች ጋር ከመጋጨት እንድጠበቅ ይረዱኛል።

ተለምዷዊነት፣ አማላይነትና ጮሌነት ከባህላችን መርገሞች መካከል ናቸው።

ለተጠናወተን የአስመሳይነት እና የርባና ቢስነት ሥሣችን ቴሌቪዝን ዋነኛው አስቀጣይ ነው። እግዚአብሔር በዚህ ተወግዷል፤ ከዚህ የተነሣ ከመለኮታዊ ነገሮች ጋር ግብ ግብ ወደ መግጠም እናዘነብላለን።

በእኛ ዘመን ልከኝነት እንደ ልብ የሚገኝ ነገር አይደለም። አንድ ጊዜ ሊገኝ ይችል ይሆናል። ርግጥ ነው ዛሬ ላይ መዝናናትና ስለ ዐየር ሁኔታ ማውራት በማይችሉ በተወሰኑ ሰዎች ላይ ሚዛናዊነት ማጣት አለ። ለእኔ ግን በዘመናችን እጅግ የላቀው ኀዘን፣ በቀላሉ አክባሪ መሆን ያልቻሉ ሰዎች ናቸው። በእግዚአብሔር ታላቅነት ተደንቀው የሚያውቁ አይመስሉም። አንድ ዐይነት ግንኙነት ብቻ ነው የሚያውቁት፤ ድንገተኛ ግንኙነት። ይህ አሳዛኝ እና የሚያደኸይ ዐቅመ ቢስነት ነው።

> ሮበርትሰን ኒኮል ስለ ስፐርጅን እንዲህ ይላል፣
>
> “በቀልድ የተዋዛው የወንጌል ሰበካ ዐይነት [ዘመናዊ፣ ደስ የሚል፣ የሚያዝናና፣ ዘመኑን የተረዳ ልንል እንችል ይሆናል] ብዙዎችን ይስብ ይሆናል፤ ነገር ግን ነፍስን ዐመድ ላይ የሚጥል እና የሃይማኖትን ዘር የሚደመስስ ነው። ቻርለስ ስፐርጅን ስብከቶቹን በአግባቡ በማያውቁ ሰዎች ዘንድ የሚያስቅ ሰባኪ እንደሆነ ይታሰባል፤ እንደ እውነታው ግን እንደ እርሱ በድምፀቱ ሁልጊዜ ቅን፣ በአክብሮት የተሞላና ኮስታራ ሰባኪ አልነበረም።[12]”

በጸጋ አስተምህሮ ደምቆና ጐልቶ የሚቀርበው የእግዚአብሔር ትልቅነት፣ ጀልባዬን የሚያጸና ክብደት ነው። ታላቅ ደስታን ይሰጠኛል፤ ልቤንም ከሞኝነት መቅሰፍት ይጠብቃል።

---

[12] Iain Murray, The Forgotten Spurgeon (Edinburgh: Banner of Truth Trust, 1973) ገጽ 38 ላይ የተጠቀሰ።

## 3. እነዚህ እውነቶች በመዳኔ እንድደነቅ ያደርጉኛል።

ጳውሎስ በኤፌሶን ምዕራፍ አንድ ላይ፣ እግዚአብሔር ያከናወነውን ታላቁን የድነት ግብር ከገለጸ በኋላ፣ በምዕራፉ መገባደጃ ላይ የዚህ ነገረ መለኮት ውጤት ልባችንን እንዲያበራ ከዚህም የተነሣ *"...የመጥራቱ ተስፋ ምን እንዲሆን ...የርስት ክብር ባለ ጠግነት ምን እንዲሆን ለምናምን ከሁሉ የሚበልጥ የኀይሉ ታላቅነት ምን እንዲሆን"* (ኤፈሶን 1፥18-19) በማወቅ እንድንደነቅ ይጸልያል። በሌላ አገላለጽ፣ እርሱ የጸለየው አስቀድሞ ያስተማረውን ነገር እንድንለማመድ ነው። ይህም ልባችን ምን እንደተደረገለት በትክክል እንዲረዳው ነው።

ማንኛውም የትምክሕት መሠረት ተወግዷል። ከተሰበረ ልብ የሚመነጭ ደስታና ምስጋና ይንሰራፋል።

የጆናታን ኤድዋርድስ ቅድስና ማደግ ይጀምራል። እግዚአብሔር የእርሱን ግርማ እና የራሳችንን ክፋት ሲያቀምሰን፣ የክርስቲያን ሕይወት ከተለመደው ሃይማኖተኝነት እጅግ ልዩ ይሆናል። ይህን ዐሳብ ኤድዋርድስ ውብ አድርጎ በዚህ መልክ ይገልጸዋል፤

> "የቅዱሳን መሻቶች እጅግ ልከኛ ቢሆኑም ትሑት ናቸው፤ ተስፋቸውም፣ ደስታቸውም ትሑት ነው። ምንም እንኳን የማይነገርና የከበረ ቢሆንም፣ ከትሑት ልብ የሚመነጭ ትሑት ሐሤት፣ ክርስቲያኖችን በመንፈስ ድኽነት የሚያኖር፣ እንደ ሕፃን ልጅ የሚያደርግ እና ለሁለተናዊ የባሕርይ ትሕትና ያጋለጠ ነው።[13]"

## 4. እነዚህ እውነቶች፣ ለምሥራቹ ዜና ምትክ ተደርገው የሚቀርቡ ሰው ተኮር ትምህርቶችን እንድለይ አንቅተውኛል።

The Pleasures of God [ዘ ፕሌዠርስ ኦፍ ጎድ][14] በተሰኘው መጽሐፌ፣ በዐሥራ ስምንተኛው ክፍለ ዘመን በነበረው ኢንግላንድ ከእግዚአብሔር ሉዓላዊነት መንሸራተታቸው ወደ አርሚኖሳዊነት፣ ከዛም ወደ መላለማዊነት

---

[13] Religious Affections, New Haven: Yale University Press, 1959 ፣ ገጽ 339-340

[14] John Piper, The Pleasures of God, (Colorado Springs, CO: Multnomah Books) ፣ ገጽ 129 ፣ 2012 ዕትም

(Universalism)፣ ከዚያም ወደ አሃዳዊነት (Unitarianism) እንደመራቸው ገልጬአለሁ። ከስፐርጅን በኋላ በ20ሥራ ዘጠነኛው ክፍለ ዘመን በኢንግላንድ ተመሳሳይ ነገር ሆኗል።

የኤይን ሙሬይ Jonathan Edwards: A New Biography [ጆናታን ኤድዋርድስ፣ ዐዲሱ የሕይወት ታሪክ] ተመሳሳይ ነገር ይዘግባል፤ "በሰሜን አሜሪካ ካልቪናዊ እምነቶች ተዳክመዋል። ጆናታን ኤድዋርድስ አስቀድሞ በትክክል እንደተናገረው፣ በዚህ የውድቀት ሂደት ከታላቁ መነቃቃት በኋላ አርሜኖሳዊነትን የተቀበሉ የኒው ኢንግላንድ አብያተ ክርስቲያናት፣ በሂደት በቻርልስ ቼንሲ እየተመሩ ወደ ሁለተናዊነት (Universalism) እና አሃዳዊነት (Unitarianism) ገብተዋል።"[15]

በተጨማሪም በጄ. አይ. ፓከር "Quest for Godliness" በተሰኘው መጽሐፍ፣ ሪቻርድ ባክስተር እነዚህን ትምህርቶች እንዴት እንደተወ እናም በኬደርሚንስተር፣ የባክስተር ቤተ ክርስቲያን ቀጣዩ ትውልድ እንዴት መጥፎ ነገር እንዳጨደ ማንበብ ትችላላችሁ።[16]

የጸጋ አስተምህሮ፣ ጠንካራና ተወዳጅ እየመሰሉ ቤተ ክርስቲያንን በሂደት ከሚበክሉ እና ከውስጥ ከሚያዳክሟት ሰው ተኮር ትምህርቶች የሚከልል ግንብ ጋሻ ነው። በትክክል የተማረችው የሕያው እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን፣ "የእውነት ዐምድና መሠረት" (1ኛ ጢሞቴዎስ 3፥15) እንድትሆን ነው። ለእኔ እነዚህ እውነቶች የሚያረጋግጡልኝ ይህን ነው።

## 5. እነዚህ እውነቶች ስለማይገለጸው ዓለማዊ በሽታችን፣ እግዚአብሔርን ስለሚያቃልል ባህላችን እንዳቃስት ያደርጉኛል።

እግዚአብሔር እንደ ጐደለባቸው ሽክም ሳይሰማኝ፣ ጋዜጣዎችን ወይም የጉግል ዜና መጣጥፎችን ማንበብ፣ የቲቪ ማስታወቂያዎችንና ሰሌዳዎችን መመልከት አቸገራለሁ። እግዚአብሔር የአጽናፈ ዓለሙ ዋነኛ ተጨባጭ እውነታ ሆኖ ሳለ፣

---

[15] Iain Murray, Jonathan Edwards: A New Biography (Edinburgh: Banner of Truth, 1987) ፣ ገጽ 454

[16] J. I. Packer, Quest for Godliness (Wheaton, IL: Crossway Books, 1990) ፣ ገጽ 160

የማይጨበጥ ተደርጎ በመታሰቡ የሚከማቸውን የእግዚአብሔርን ቍጣ ሳስብ እንቀጠቀጣለሁ፤ እስካሁን ድረስ እደነግጣለሁ። እናንተስ? ብዙ ክርስቲያኖች እንደ ዓለማውያኑ ሁሉ፣ እግዚአብሔርን ችላ በማለት ዕፅ ደንዝዘዋል። አንዳንዶች እግዚአብሔር ችላ መባሉን ክብር አድርገው ያስባሉ፤ ከእንያንዳንዱ ነገር ጋር አያይዘው ስለ እግዚአብሔር ለሚያወሩ ሰዎች የፉገራ ስም ያወጡላቸዋል። እነዚህ አስተምህሮች፣ እንዲህ ላለው ቸልተኝነትና ፉገራ ፍቱን ማርከሻ ናቸው።

ክርስቲያኖች የሚኖሩት የእግዚአብሔርን ተጨባጭነት ለማስረገጥና በሕያዋን ሁሉ ላይ የእርሱን ልህቀት ለማወጅ ነው። ስለዚህ ታላቅ መነቃቃት ያስፈልገናል። እነዚህ እውነቶች ይህን እንድገነዘብና ለዚህም እንድጸልይ ይገፋፉኛል። ይህን እውን ሊያደርግ የሚችለው የእግዚአብሔር ሉዓላዊ ሥራ ብቻ ነው።

## 6. እነዚህ እውነቶች እግዚአብሔር ለመላ ዓለሙም ሆነ ለግል፣ ያቀደውንና የጀመረውን ሥራ ከግብ እንደሚያደርስ እንድተማመን ያደርጉኛል።

እግዚአብሔር ሉዓላዊ ኀይሉን በመጠቀም እኔን ለራሱ መጠበቁ፣ እጅግ ውድ የሆነ እውነት ነው። እኔ ልቤን ዐውቃለሁ። ለራሱ ከተተወ፣ ልቤ ትምክተኛና ራስ ተኮር እንዲሁም የጣዖት ማምረቻ ነው። ጥቂት ጸሎቶች ይበልጡን አስፈላጊ ናቸው፤

ኦ ለጸጋ እንዴት ያለ ታላቅ ባለ ዕዳ ነኝ

በየዕለቱ ራሴን ላስገዛለት የሚገባኝ!

ቸርነትህ እንደ ብረት ማሰሪያ ይሁን፤

ቅብዝብዙን ልቤን ከራስህ አጣብቀው።

ከርታታ ነኝ፤ ጌታ ሆይ ዐውቃለሁ፤

የምወደውን አምላክ ልተው የተጋለጥሁ ነኝ፤

ይኸው ልቤን ውሰድና አትመው፤

ለአንተው ለላይኛው መንግሥትህ አትመው።

አዎን፤ በየዕለቱ ከራሱ እንዲያጣብቀኝ ያስፈልገኛል፤ ደግሞም እፈልጋለሁ። አትመኝ፤ ያዘኝ፤ ጠብቀኝ፤ በእጅህ አድርገኝ። እናም የጸጋ አስተምህሮ ለእነዚህ መሻቶች ፍጹም የሆነ እርካታ ናቸው። ይህ በትክክል እግዚአብሔር ሊያደርግልኝ የገባው ቃል ነው። “መልካምን ነገር ለእነርሱ ከማድረግ እንዳልቈጠብና ከእኔም ፈቀቅ እንዳይሉ መፈራቴን በውስጣቸው ላኖር ከእነርሱ ጋር የዘላለም ቃል ኪዳን እገባለሁ” (ኤር. 32፥40)። “እኔ ከአንተ ጋር ነኝና አትፍራ፤ አምላክህ ነኝና አትደንግጥ። አበረታሃለሁ፤ እረዳሃለሁ፤ በጽድቄም ቀኝ እጄ ደግፌ እይዝሃለሁ” (ኢሳ. 41፥10)። ጠዋት ደኅንነቱ የተጠበቀ አማኝ ሆኜ እንደምነቃ በመተማመን ሲመሽ ወደ መኝታዬ የምሄደው፣ በራሴ ነጻ ፈቃድ ሳይሆን በእግዚአብሔር ነጻ ጸጋ ነው። ይህ ከሚሊዮን ዶላሮች ይልቅ ዋጋ አለው።

## 7. እነዚህ እውነቶች እያንዳንዱን ነገር ከእርሱ፣ በእርሱና ለእርሱ ከሆነው፣ ለእርሱም ከዘላለም እስከ ዘላለም ክብር ከሚገባው፣ ከእግዚአብሔር ሉዓላዊ ዐላማ አንጻር እንድመለከት ያደርጉኛል።

በእነዚህ አስተምህሮች መነጽር እያንዳንዱ የሕይወት ነገር ከእግዚአብሔር ጋር እንደሚዛመድና እርሱ የሁሉ ነገር መጀመሪያ፣ እኩሌታ እና መጨረሻ ነው። እርሱ በጣም አስፈላጊ ያልሆነበት አንዳች የሕይወት ክፍል የለም። ለእያንዳንዱ ነገር ትርጒም የሚሰጠው እርሱ ነው (1ኛ ቆሮንቶስ 10፥31)።

በቅዱሳት መጻሕፍት የተገለጠውን የእግዚአብሔርን ሉዓላዊ ዐላማ መመልከት፣ እንዲሁም ጳውሎስ በኤፌሶን 1፥11፣ "ሁሉን በፈቃዱ ምክር መሠረት እንደሚሠራው" ያለውን መስማት፣ ዓለምን በዚህ መንገድ እንድመለከት ያደርገኛል። ተጨባጭ እውነታ በእግዚአብሔር ዘንድ እጅግ የላቀ ይሆናል። በሚሆነው ሁሉ እርሱ ሁሉን የሚያጥለቀልቅ ክብር ነው። ሁሉ ከእርሱና ለእርሱ ነው። የጆናታን ኤድዋርድስ ቃላት ያስደምሙኛል፤ ምክንያቱም የጸጋ አስተምህሮን ምልከታ እጅግ ውብ አድርገው ይገልጻሉ፤

> ፍጥረታት እግዚአብሔርን ሲያውቁ፣ ሲያከብሩ፣ ሲወድዱ፣ ሲደሰቱ እና ሲያመሰግኑ፣ የእግዚአብሔር ክብር *ይገለጣል* ደግሞም *ይታወቃል*፤ የእርሱ ምልዓት ቅቡል እና ምላሽ የሚያገኝ ነው። እዚህ ጋር *ፍንጣቂው* እና *ነጸብራቁ* አሉ። ፍንጣቂው፣ በፍጥረታቱ ላይና ወደ ፍጥረታቱ ውስጥ ያበራል፤ ከዚያ ወደ ምንጩ ያንጸባርቃል። ከእግዚአብሔር የሚመጡ የከብሩ ጨረሮች ከእርሱ ይገኛሉ፤ እንደገናም ተመልሰው ወደ ቀደመው ምንጫቸው ይሄዳሉ። ስለዚህ ሁሉም **ከ**እግዚአብሔር፣ **በ**እግዚአብሔር እና **ለ**እግዚአብሔር ነው። እርሱ መጀመሪያ፣ እኩሌታ እና መጨረሻ ነው።[17]

---

[17] Jonathan Edwards, The End for Which God Created the World, p. 275, in John Piper's, God's Passion for His Glory, (Wheaton, Illinois: Crossway Books, 1998) ፣ ገጽ 248

## 8. እነዚህ እውነቶች ለሰዎች ለውጥ የሚደረገውን ጸሎት ለመመለስ እግዚአብሔር ፈቃደኛ፣ ባለ ሥልጣንና ኀያል በመሆኑ በተስፋ እንድሞላ ያደርጉኛል።

የጸሎት ዋስትና፣ እግዚአብሔር ሳያስፈቅድ ነገሮችን ይለውጣል—የሰዎችን ልብ ጭምር—የሚል ነው። እርሱ ፈቃድ ማሸከርከር ይችላል። "ስምህ ይቀደስ" (ማቴዎስ 6፥9) ማለት፣ ስምህን የማይቀድሱትን እንዲቀድሱ አድርጋቸው ማለት ነው። "የጌታ ቃል በፍጥነት እንዲሠራጭና እንዲከበር" (2ኛ ተሰሎንቄ 3፥1) ማለት፣ የሰዎችን ልብ እግዚአብሔር ለወንጌሉ ክፍት እንዲያደርግ ማለት ነው። እግዚአብሔር ለእኔ ይህን ያደረገው፣ ለወላጆቼ ጸሎት ምላሽ በመስጠት ነው። እኔ አሁን ለሌሎች በደስታ የማደርገው ይህን ነው።

የዐዲሱ ኪዳን ተስፋዎች፣ በእያንዳንዱ ሰው ሕይወት እና እስከ ዓለም ዳርቻ ሁሉ ውጤታማ ይሆን ዘንድ ተማጽኖዬን ወደ እግዚአብሔር አደርሳለሁ። በዚህ መልክ የምጸልይበት ምክንያት፣ እርሱ ይህን ሁሉ የማድረግ ሥልጣንና ኀይል ስላለው ነው። የትኛውም ዐይነት ራስ ገዝነት በእርሱ ፊት ቆሞ ሊገታው አይችልም።

> *"የማያወላውል ልብ እሰጣቸዋለሁ፤ ዐዲስ መንፈስ በውስጣቸው አኖራለሁ፤ ድንጋዩን ልብ ከውስጣቸው አወጣለሁ፤ ሥጋ ልብም እሰጣቸዋለሁ።" (ሕዝ. 11፥ 19)*
> *"አምላክህ እግዚአብሔር (ኤሎሂም ያህዌ) የአንተንና የዘርህን ልብ ይገርዛል።" (ዘዳ. 30፥ 6)*
> *"መንፈሴን በውስጣችሁ አሳድራለሁ፤ ሥርዐቴን እንድትከተሉና ሕጌን በጥንቃቄ እንድትጠብቁ አደርጋለሁ" (ሕዝ. 36፥ 27)*
> *"እውነትን ወደ ማወቅ ይደርሱ ዘንድ፣ እግዚአብሔር ንስሓን እንደሚሰጣቸው ተስፋ በማድረግ የሚቃወሙትን በየዋህነት የሚያቃና መሆን ይኖርበታል፤" (2ኛ ጢሞ. 2፥25)*
> *"ጌታም፣ ጳውሎስ የሚናገረውን በማስተዋል ትሰማ ዘንድ፣ ልቧን ከፈተላት።" (ሐዋ. 16፥14)*

ጸሎት፣ አብዛኛው ክርስቲያን እንደ ካልቪናዊ የሚሆንበት ቦታ ነው። ትሑት ልብ ያላቸው ክርስቲያኖች ሲጸልዩ፣ እግዚአብሔር ሥልጣንና ኀይል ያለው፣ የሰውን አካላዊ ደዌ ለመፈወስ፣ ተፈጥሯዊ የሆኑ ኑባሬዎችን ለመቀየር ብቻ ሳይሆን፣ ሉዓላዊ በሆነ መንገዱ የሰውንም ልብ ሊቀይር እንደሚችል በማሰብ ነው። በሌላ አገላለጽ፣ ጸሎት የተመሠረተው እግዚአብሔር የሰዎችን ተቃውሞ ለማሸነፍ ባለው ችሎታ ላይ ነው። እርሱ እንዲያደርግልን የምንጠይቀው ይህንኑ ነው። ይህ ማለት እንዲድኑ ለተማጸንኩላቸው ሰዎች ሕይወት፣ የማይቋቋሙት ጸጋ ለተመለሱት ጸሎቶች ትልቅ ተስፋ ነው።

## 9. ሰዎች ወደ ክርስቶስ እንዲመጡና እንዲድኑ እንዲሁም ሰዎችን ወደ እምነት በመምራት ረገድ ወንጌል እጅግ በጣም አስፈላጊና የላቀ ሚና እንዳለው፣ ነገር ግን የአላማኙ መለወጥ በእኔም ሆነ በግለሰቡ የልብ ድንዳኔ መጠን ላይ እንደማይመሠረት እነዚህ እውነቶች ያስታውሱኛል።

እነዚህ የጸጋ አስተምህሮች፣ ስብከተ ወንጌልን በመንፈስ በሞቱ ኀጢአተኞች ዘንድ እንዲቻል ያደርጋሉ። ያለ እግዚአብሔር ሉዓላዊ ጸጋ፣ በመቃብር ስፍራ እየሰበክን ልንገኝ እንችላለን፤ ምክንያቱም እየሰበክን ያለነው በመቃብር ሰፈር ነው። ይህ ዓለም እንደዚህ ነው። የአጠቃላይ ውድቀት ጭብጥ ይኸው ለተፈጥሯዊው ሰው የመስቀሉ ቃል ሞኝነት መሆኑ ነው፤ “ከእግዚአብሔር መንፈስ የሆነውን ነገር ሊቀበል አይችልም፤ ምክንያቱም እንዲህ ያለው ነገር ለእርሱ ሞኝነት ነው፤ በመንፈስም የሚመረመር ስለ ሆነ፣ ሊረዳው አይችልም” (1ኛ ቆሮንቶስ 2፥14)። ስለዚህ የወንጌል ስብከት ትርጉም የሚኖረው በጸጋ አስተምህሮ ብርሃን ሲታይ ብቻ ነው። እግዚአብሔር የሞተውን እንደሚያስነሣ እናምናለን።

ይህን ለመከወን እግዚአብሔር ሰዎችን ይጠቀማል። “ዳግመኛ የተወለዳችሁት ከሚጠፋ ዘር ሳይሆን፣ ሕያው በሆነና ጸንቶ በሚኖር፣ በእግዚአብሔር ቃል አማካይነት ከማይጠፋ ዘር ነው” (1ኛ ጴጥሮስ 1፥23)። ለሙታን ዐዲስን ሕይወት በመስጠት የእግዚአብሔር ሉዓላዊ ሥራ “በሕያውና ለዘላለም በሚኖር በእግዚአብሔር ቃል” ነው።

ጴጥሮስ ይህን ይጨምራል፤ "የጌታ ቃል ግን ለዘላለም ጸንቶ ይኖራል። የተሰበከላችሁም የምሥራች ቃል ይህ ነው" (1ኛ ጴጥሮስ 1፥25)። እርሱም ወንጌሉ ነው። ይህ የእግዚአብሔር ኀይል ለማዳን ነው (ሮሜ 1፥16)።

ስለዚህ የጸጋ አስተምህሮ እጅግ አስቸጋሪ በሆኑ ሁኔታዎች፣ ለወንጌል ስብከት ተስፋን ይሰጣል። ሙት ሙት ነው። ሙስሊሞች ቢሆኑ ሂንዱዎች ወይም የደነደኑ የአውሮፓ ድኅረ-ክርስትና ዓለማዊያን [Post-Christian Secularist] ቢሆኑ፣ ከሌላው "ተፈጥሯዊ ሰው" በላይ የወደቁ አይደሉም። እግዚአብሔር የማይቻለውን ያደርጋል። እርሱ ሙታንን ያስነሣል (ኤፌሶን 2፥1-6)። ኢየሱስ የወጣቱን ባለጠጋ ልበ ደንዳናነት በተመለከተ ጊዜ እንዲህ ብሏል፣ "ይህ በሰው ዘንድ አይቻልም፤ በእግዚአብሔር ዘንድ ግን ሁሉም ነገር ይቻላል" (ማቴዎስ 19፥ 26)።

ወንጌል ያልተሰበከበትን የተቀረውን ዓለም ስመለከት ተስፋ አልቆርጥም። ይልቁንም ኢየሱስ የተናገረውን እሰማለሁ፤ "ከዚህ ጉረኖ ያልሆኑ ሌሎች በጎች አሉኝ፤ እነርሱንም ማምጣት አለብኝ። እነርሱም ድምፄን ይሰማሉ፤ አንድ መንጋም ይሆናሉ፤ እረኛውም አንድ"(ዮሐንስ 10፥16)። ሊሰሙ ይችሉ ይሆናል አላለም፤ ነገር ግን ድምፄንም ይሰማሉ ነው ያለው። ስለዚህ እንዲህ እላለሁ፤ ይህ በፍጹም ሊሻር አይችልም። የጸጋ አስተምህሮ በእነ ዊልያም ኬሪ፣ ዴቪድ ሊቪንግተን፣ አዶኒራም ጁድሰን፣ ሄንሪ ማርቲን፣ ጆን ፓተን እና በሌሎች ሺዎች ሕይወት የወንጌል ተልእኮን አቀጣጥሏል። እስከ ዓለም ዳርቻ ወንጌልን በማስተዋወቅ ሂደት እኔም የበኩሌን አስተዋፅዖ እንዳደርግ፣ ይህ የጸጋ አስተምህሮ ተጽእኖ አሳድሮብኛል።

## 10. በመጨረሻም፣ እግዚአብሔር ድል እንደሚያደርግ እነዚህ እውነቶች ርግጠኛ ያደርጉኛል።

"የጥንቱን፣ የቀደመውን ነገር አስታውሱ፤ እኔ አምላክ ነኝ፤ ከእኔም በቀር ሌላ የለም፤ እኔ አምላክ ነኝ፤ እንደ እኔ ያለ የለም።የመጨረሻውን ከመጀመሪያው፣ ገና የሚመጣውንም ከጥንቱ ተናግሬአለሁ፤ 'ዐላማዬ የጸና ነው፤ ደስ የሚያሰኘኝንም ሁሉ አደርጋለሁ' እላለሁ" (ኢሳ. 46፥9-10)።

የጉዳዩ ሁሉ ድምር እግዚአብሔር አምላክ መሆኑ ነው። እርሱ ፍጹም ሉዓላዊ ነው። እርሱ ከሰዎች አስደናቂ ምሳሌ በላይ ቸር ነው። ዓለሙን በኀጢአቱ ፈጽሞ እንዲጠፋ ከቶ አልተወውም። ለሕዝቡ እና ለፍጥረቱ ደኅንነትን ዐቅዷል፤ ዕቅዱንም በመፈጸም ላይ ነው፤ ደግሞም ከግብ ያደርሰዋል። ይህንንም ወደር በሌለው ፍቅሩና ጥበቡ አድርጓል። ማለትም ይህን ያደረገው እርሱ በእኛ እንዲከብር፣ እኛ በእርሱ ብቻ እንድንደሰት ነው። ምክሩ ደግሞ ፈጽሞ ሊሻር አይችልም። “የእግዚአብሔር ዐሳብ ግን ለዘላለም ይጸናል፤ የልቡም ዐሳብ ለትውልድ ሁሉ ነው” (መዝ. 33፥11)።

# ማጠቃለያ ምስክርነቶች

የዚህ መጽሐፍ ዋና ዐላማ፣ አእምሮን ሁሉ ለቅዱሳት መጻሕፍት ርቱዕ አስተምህሮ መማረክ እና የእግዚአብሔርን ሉዓላዊ ጸጋ በጥልቀት እንዲለማመድ ማንቃት ነው። ያዕቆብ 2፥19 ላይ፣ "አጋንንትም ይህንኑ ያምናሉ፤ በፍርሀትም ይንቀጠቀጣሉ።" የሚለውን አስደንጋጭ እውነት ሁልጊዜ አስባለሁ። በሌላ አገላለጽ፣ በተወሰነ ደረጃ ለእውነት ተማርኮ፣ የተማረከለትን እውነት ጣዕም በሌላ ደረጃ አለመለማመድ ይቻላል ማለት ነው። ጆናታን ኤድዋርድስ በጠርሙስ የተቀመጠውን የሚጣበቅ ቡናማ ነገር፣ ጣፋጭ መሆኑን የምንለይበት ሁለት መንገዶች አሉ ይለናል። የመጀመሪያው፣ በዕቃ ውስጥ የተቀመጠው ቡናማ ቀለም እና ቅርጽ በማየት ወይም በማሽተት ካገኛችሁት መረጃ በመነሣት ጣፋጭ ነገር እንደሆነ በመረዳት ማር ነው ማለት ትችላላችሁ፤ በሌላ በኩል ደግሞ በመቅመስ ማር መሆኑን ልታረጋግጡ ትችላላችሁ። የእኔ ጸሎት የእግዚአብሔር ግሩምና ጣፋጭ ሉዓላዊ ጸጋ በእይታ እንዲገመት ብቻ ሳይሆን እንዲቀመስ ነው።

በእነዚህ እውነቶች ታላቅ ምቾት ውስጥ በማረፍ፣ በሕይወታችሁ ጣፋጭ ልምምድ እንደሚኖራችሁ ተስፋ አደርጋለሁ። ከዚህ እውነት የተነሣ ለፍቅር፣ ለጽድቅ እና ለአስፈሪ የወንጌል ተልእኮ ድፍረትን ለማግኘት እጅግ ትልቅ መበረታታት እንዲሰማችሁ እፈልጋለሁ። የእግዚአብሔርን ሉዓላዊ ጸጋ መረዳታችሁና ማመናችሁ፣ እግዚአብሔርን በሕይወታችሁ እንዲያከብር ጸሎቴ ነው።

በመጨረሻም፣ ይህ እውነተኛ አስተምህሮ ለቀደምት ክርስቲያኖች የነበረውን ትርጒም የሚያሳዩ ምስክርነቶችን አሰባስቤ ዐቅርቤአለሁ። የጸጋውን አስተምህሮች ጠንቅቀው ለተረዱ፣ ትምህርቶቹ ባዶ ጽንሰ ዐሳብ አይደሉም፤ ነገር ግን ለአእምሮ እና ለሕይወት ዐቅም ናቸው።

## የሂፖው አውግስጢኖስ (354-430)

ከተሐድሶው አንድ ሺህ ዓመት በፊት፣ አውግስጢኖስ የጸጋን ሉዓላዊነት በሕይወቱ አጣጥሟል። አውግስጢኖስ መላ ቅጡ የጠፋው ሕይወት ሲመራ ከቆየ በኋላ፣ በእግዚአብሔር ሉዓላዊ ጸጋ አማካኝነት በርግጥም ተለውጧል። ኑዛዜ በተሰኘው መጽሐፉም (ምዕራፍ 10፣ 40) ላይ እንዲህ ሲል ጽፏል፤

> *"እጅግ ታላቅ ከሆነው ያንተ ምሕረት ውጭ ሌላ ተስፋ የለኝም። አንተ ያዘዝከውን ስጠኝ፤ ፈቃድህንም እዘዘኝ። ራሳችንን እንድንገዛ አዘኸናል። … በቡራቡሬነት ከተበታተንበት፣ ራስን በመግዛት ወደ አንድነት መጥተናል። አንተን ለአንተነትህ የማይወድህ፣ ከአንተ ጋር ሌላን ነገር የሚወድ ሰው፣ ላንተ ያለው ፍቅር ትንሽ ነው። አቤት ሁልጊዜ የሚነድ እና የማይጠፋ ፍቅር! አቤት ለጋስነት፣ አምላኬ ሆይ፤ አቀጣጥለኝ! ራሳችንን እንድንገዛ አዘሃል። ያዘዝከውን ስጠኝ፤ ፈቃድህንም እዘዘኝ።[18]"*

የእግዚአብሔርን ሉዓላዊ ጸጋ እውነት በርግጥም የሚወድ ሰው ቃላት ናቸው፤ ምክንያቱም ያለ ጸጋው እንደሚጠፋ ያውቃል። የአስተምህሮ ይዘት ባላቸው መልእክቶቹም፣ አውግስጢኖስ ይህን ተወዳጅ እውነት ይተነትናል (217ተኛው መልእክት ለቫይታሊስ)፣

> *"እንደ አንተ ላስብ ብል እንኳ፣ የማያምኑ የእግዚአብሔርን ሕግና ትምህርት የሚቃወሙና የማይቀበሉ እንዲያምኑ፣ እውነተኛውን መንገድ እንዲከተሉ እንደ ልማዳችን ልመናችንን ወደ እግዚአብሔር በማድረስ እኛ ግዴታችንን እየተወጣን እንዳለን መቼም ትስማማለህ። ሰዎች በሚለወጡበት ወይም እውነተኛውን መንገድ መከተል በጀመሩበት ወቅት፣ እንደ ልማዳችን እግዚ አብሔርን በማመስገን ግዴታችንን እየተወጣን እንዳለን በማሰባችን ከእኛ ጋር ከተስማማህ…በርግጠኝነት የሰዎቹን ፈቃድ በዋነኝነት እግዚአብሔር በጸጋው አማካኝነት እንደለወጠውና ሰዎቹ አስቀድሞ ሲገፉት የነበረውን*

---

[18] Documents of the Christian Church, ed. by Henry Bettenson [London: Oxford University Press, 1967] ፣ ገጽ 54

መልካም ነገር፣ አሁን እንዲፈልጉና እንዲቀበሉ ያደረገው እግዚአብሔር እንደሆነ ታምናለህ፤ ምክንያቱም ወደ እምነት እንዲያደርሳቸው የለመንነው እግዚአብሔርን ነው። እግዚአብሔር ሰዎቹን ወደ ራሱ እንደሳበ ስለምናውቅ፣ ለእርሱ ደግሞ ምስጋናን እናቀርባለን።”

የጠፉ ሰዎች እንዲድኑ ወደ እግዚአብሔር በሚያቀርበው ልመና እና ወደ እምነት ሲደርሱ በሚያቀርበው ምስጋና፣ የማይቋቋሙት ጸጋ አስተምህሮ ለአውግስጢኖስ የጸሎቱ መሠረት ነው።

## ጆናታን ኤድዋርድስ (1703—1758)

ታላቁ የኒው ኢንግላንድ ሰባኪና የሥነ መለኮት ምሁር የሆነው ጆናታን ኤድዋርድስ፣ ለእነዚህ እውነቶች ጥልቅ ፍቅር ነበረው። የእግዚአብሔርን ሉዓላዊ ጸጋ ስለተረዳበትና ስለወደደበት ቀን በሃያ ስድስት ዓመቱ እንዲህ ሲል ጽፏል፤

“ከዚያ ቀን አንሥቶ እስከ ዛሬ ድረስ፣ የእግዚአብሔር ሉዓላዊነት አስተምህሮን በተመለከተ በአእምሮዬ ግሩም ለውጥ ሆኗል። …በዐይኖቼ ከምመለከታቸው ከማናቸውም ነገሮች ይልቅ፣ አእምሮዬ በእግዚአብሔር ፍጹም ሉዓላዊነት ርግጠኛ ነው። ይህ አስተምህሮ ሁልጊዜ እጅግ አስደሳች፣ ብሩህ እና ጣፋጭ ሆኖ ይታየኛል። ፍጹም ሉዓላዊነት በእግዚአብሔር ልመለከተው የምወደው ነው። የእግዚአብሔር ሉዓላዊነት ታላቅ የክብሩ አካል ሆኖ ይታየኛል። ወደ እርሱ መቅረብና እንደ ሉዓላዊ ጌትነቱ እርሱን መውደድ ሁልጊዜ ደስታዬ ነው።[19]”

---

[19] “Personal Narrative,” quoted in Jonathan Edwards, Selections [New York: Hill & Wang, 1935] , ገጽ 59

## ጆርጅ ዊትፊልድ (1714—1770)

ጆርጅ ዊትፊልድ በቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ ሲሰብክ ኤድዋርድስ በግልጽ አለቀሰ፤ ምክንያቱም የሰበከውን መልእክት በጣም ስለወደደው ነው። ዊትፊልድ ታላቅ ወንጌላዊ ነበር እናም እንዲህ ብሏል፣ "በካልቪናዊ አስተምህሮ ማዕቀፍ ውስጥ የሆንኩት በካልቪን ምክንያት አይደለም፤ ነገር ግን ኢየሱስ ክርስቶስ ስላስተማረኝ ነው።"[20]

የካልቪኒዝምን አስተምህሮች እንዳይቃወም ጆን ዌስሊን እንዲህ ሲል ተማጽኖታል፤

> አንተን የመቃወም ዐሳብ መሸከም አልችልም። ነገር ግን (ወንድምህ ቻርልስ በአንድ ወቅት እንደተናገረው) ጆን ካልቪንን ከብሪስቶል ብታስወጣው፣ ትምህርቱን ከውስጤ እንዴት ላስወግደው እችላለሁ። ካልቪን የጻፈውን አንዳች አላነበብኩም፤ አስተምህሮቼን የተቀበልኩት ከክርስቶስና ከሐዋሪያቱ ነው። የተማርኩት ከእግዚአብሔር ነው።[21]

ለወንጌል ምስክርነት በቅዱስ ቅናት የሞላው ይኸው እምነቱ ነው፤

> የመመረጣችን እና በክርስቶስ ኢየሱስ በነጻ የመጽደቃችን አስተምህሮ፣ ዕለት ዕለት በልቤ ላይ ይከብዳሉ። ነፍሴንም በቅዱስ እሳት ይሞላሉ፤ በአዳኜ አምላክ ላይ ትልቅ ትምክሕት ይሰጡኛል።
>
> እርስ በርስ መቀጣጠል፣ ጌታ ኢየሱስን ከፍ የሚያደርግና ሰውን የሚያዋርድ ቅዱስ ፉክክር በመካከላችን እንደሚኖር ተስፋ አደርጋለሁ። ይህን ማድረግ የሚችሉት ተሐድሶአዊ አስተምህሮች ብቻ ናቸው።
>
> ሌሎቹ ሁሉ ነጻ ፈቃድን ለሰው አሳልፈው በመስጠት፣ ሰውን ቢያንስ በከፊል የራሱ አዳኝ ያደርጉታል። ነፍሴ ሆይ፤ እንዲህ ያለውን ምስጢር

---

[20] Arnold Dallimore, George Whitefield, Vol. 1 (Edinburgh: Banner of Truth Trust, 1970), ገጽ 406

[21] ዝኒ ከማሁ ፣ ገጽ 574

> የሚያስተምሩትን አትቅረቢአቸው ... ክርስቶስ ሁሉ በሁሉ እንደሆነ ዐውቃለሁ።

ሰው ኢምንት ነው፤ ወደ ሲኦል ለመሄድ ነጻ ፈቃድ አለው፤ ነገር ግን ፈቃደኛ እንዲሆን እና በጎ ፈቃዱን እንዲያደርግ በእርሱ ውስጥ እግዚአብሔር ካልሠራ ወደ መንግሥተ ሰማይ ለመሄድ ነጻ ፈቃድ የለውም።

> አቤት የሁኔታ አልባ ምርጫ አስተምህሮ እና የቅዱሳን ጽናት ልህቀት! ሰው እነዚህን ወሳኝ እውነቶች ወደ ማመን እና ወደ መረዳት ካልመጣ ከራሱ ላይ ዐይኑን ሊነቅል እንደማይችል ተረድቻለሁ፤ ነገር ግን እነዚህን እውነቶች ሲያምን እና ተግባራዊነታቸውን ለልቡ ሲያረጋግጥ፣ የምር በእምነት ይጓዛል።[22]

## ጆርጅ ሙለር (1805–1898)

ጆርጅ ሙለር ባቋቋማቸው የሕፃናት ማሳደጊዎችና ስለ እግዚአብሔር መግቦት በሚጸልይበት አስደናቂ እምነቱ ይታወቃል። ብዙ ሰዎች ይህን ታላቅ አገልግሎት ከሥር መሠረቱ ደግፎ የያዘውን ሥነ መለኮት አያውቁም። በሃያዎቹ አጋማሽ ላይ (1829) የነበረውን ተመክሮ፣ በኋላ ላይ እንደሚከተለው አስፍሮታል፤

> ከዚህ ጊዜ በፊት [መጽሐፍ ቅዱስን ብቸኛ የእውነት መመዘኛ አድርጌ ወደ መሾም ስመጣ]፣ የሁኔታ አልባ ምርጫ፣ የውሱን ቤዝዎት እና የቅዱሳን ጽናት አስተምህሮችን እጅግ ተቃውሜ ነበር። አሁን ግን እነኚህን ድንቅ አስተምህሮች በእግዚአብሔር ቃል ወደ መመዘን ደርሻለሁ። በኀጢአተኞች መለወጥ ለራሴ ክብርን የማልወስድ በመሆን፣ ራሴን እንደ መጠቀሚያ ብቻ እቈጥራለሁ። ቅዱሳት መጻሕፍት የሚሉትን ለመቀበል ፈቃደኛ ተደርጌ፣ ስለ እነዚህ አስተምህሮች በዐዲስ ኪዳን የተዘገበውን በልዩነት በማጣቀስ ከመጀመሪያው አንብቤአለሁ።

---

[22] ዝኒ ከማሁ ፣ ገጽ 407

በአስደናቂ ሁኔታ ስለ ሁኔታ አልባ ምርጫ እና ስለ ቅዱሳን ጽናት በግልጽ የሚናገሩ የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባቦች፣ ከእነዚህ እውነቶች በተቃራኒ የቆሙ ከሚመስሉት አራት ዕጥፍ ያህል ነበሩ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ተቃራኒ የሚመስሉትን ምንባቦች ስመረምራቸውና ስረዳቸው፣ የላይኞቹን አስተምህሮች ለማጽናት ተጠቀምኳቸው።

በእነዚህ ትምህርቶች ላይ ያለኝ እምነት በእኔ ላይ ካሳደረው ተጽእኖ የተነሣ፣ ምንም እንኳን እጅግ ደካማ ብሆንም፣ ለእግዚአብሔር ክብር መኖር ችያለሁ። ይህ ማለት ግን ለሥጋ ምኞች፣ ለዐይን አምሮትና ለትዕቢት ሙሉ ለሙሉ ሞቼ፣ የሚጠበቅብኝን ሕይወት እየኖርኩኝ ነው ማለት አይደለም፤ ነገር ግን በእግዚአብሔር ጸጋ ርዳታ ከዚያን ጊዜ አንሥቶ ወደ እርሱ ይበልጥ ቀርቤአለሁ። ሕይወቴ የሚወላውል አልነበረም፤ እናም ከቀደሞው ይልቅ በሕይወቴ ለእግዚአብሔር ክብር ኖሬአለሁ ማለት እችላለሁ።[23]

## ቻርልስ ስፐርጅን (1834–1892)

ቻርልስ ስፐርጅን በጆርጅ ሙለር ዘመን የኖረ፣ በለንደን የሜትሮፖሊታን ታበርናክል መጋቢ ሲሆን፣ በጊዜው ታዋቂ ሰባኪ እና መጥምቃዊ [Baptist] ነበር። የእርሱ ስብከት ነፍሳትን ለክርስቶስ ለማሸነፍ ኀይል ነበረው። ታዲያ በየሳምንቱ ሺዎችን አጥብቆ የያዘው፣ ብዙዎችንም ወደ አዳኙ የሳበው ወንጌል ምንድነው?

> በአሁኑ ጊዜ ካልቪኒዝም ተብሎ የሚጠራውን ትምህርት ካልሰበክን፣ የተሰቀለውን ክርስቶስ መስበክ የሚባል ነገር የለም የሚል የግል እይታ አለኝ። ካልቪኒዝም የወንጌሉ ቅጽል ስም ነው። ካልቪኒዝም ወንጌል ነው፤ ሌላ አይደለም። በጸጋ ዕደላው የእግዚአብሔርን ሉዓላዊነት ካልሰበክን፣ መራጩን፣ ለዋጩን፣ ዘላለማዊውን፣ አይለወጤውን የያህዌ ፍቅር ሳናወሳ ወንጌል መስበክ እንችላለን ብዬ አላምንም፤ ክርስቶስ በመስቀል ላይ የሞተው ለምርጦቹ—ለተመረጠው ሕዝብ በልዩነት ውስን ቤዝዎት በመፈጸሙ ላይ

[23] Autobiography (London: J. Nisbet & Co., 1906), ገጽ 33-34

ካልተመሠረትን ወንጌልን መስበክ አንችልም፤ እንዲሁም ቅዱሳን ከተጠሩ በኋላ ፈጽመው እንዲጠፉ የሚተዋቸው ወንጌል ሊገባኝ አይችልም።[24]

ስፐርጅን እነዚህን ነገሮች ያምንም ነበር፤ በዐሥራ ስድስት ዓመቱ እነዚህን እውነቶች እንዴት እንዳገኘ ይተርካል፤

ስወለድ፣ ሁላችንም በተፈጥሮ እንደነበርነው፣ አርሜኖሳዊ ሆኜ ነው። ከምስባክ በተከታታይ በሰማኋቸው የድሮ ነገሮች ውስጥ፣ የእግዚአብሔር ጸጋ እንዳላየሁባቸው አሁንም ድረስ አምናለሁ። ወደ ክርስቶስ ስቀርብ ራሴ እንዳደረኩት ዐስብ ነበር፤ ጌታን በትልቅ አክብሮት ብመለከተውም እርሱ እንደሚፈልገኝ አላውቅም ነበር። … እነዚህን እውነቶች በነፍሴ የተቀበልኩበትን ቀንና ሰዓት አስታውሳለሁ፤ ጆን በንያን እንደሚለው፣ በጋለ ብረት የመነካት ያህል በውስጤ ነደደ። …

በአንድ የአዘቦት ምሽት በቤተ ክርስቲያን ተቀምጬ ሳለሁ ሰባኪው የሚሰብከውን ስላላመንኩበት፣ ስለ ስብከቱ እምብዛም እያሰብኩ አልነበረም። እንዲህ የሚል ዐሳብ ወጋኝ፣ "እንዴት ክርስቲያን ሆንክ?" ጌታን ፈለግሁት። "ነገር ግን ጌታን ወደ መፈለግ እንዴት መጣህ?" እውነቱ በአእምሮዬ ድንገት ብልጭ አለ—እርሱን እንድፈልግ አስቀድሞ በልቡናዬ ላይ ተጽእኖ ባይደረግ፣ እርሱን አላገኘውም ነበር። ስለ ጸለይኩኝ ይሆን? ራሴን እንዲህ ስል ጠየኩኝ፣ "እንዴት መጸለይ ቻልኩ?" ቅዱሳት መጻሕፍትን ሳነብ እንድጸልይ ስላዘዘኝ ነው። ቅዱሳት መጻሕፍትን እንዴት ላነብ ቻልኩ? በቃ አነበብኩኝ፤ ግን እንዳነብ ያደረገኝ ነገር ምንድር ነው? ይህን በማስብበት ቅጽበት፣ የሁሉም ነገር መሠረት እግዚአብሔር እንደሆነ ተረዳሁ። እርሱ የእምነቴ ደራሲ ነው። ስለዚህ አጠቃላዩ የጸጋ አስተምህሮ ያን ጊዜ ተገለጠልኝ፤ እስከ ዛሬ ድረስ ከዚህ አስደናቂ እውነት አልተለየሁም።

---

[24] Autobiography, Vol. 1 (Edinburgh: Banner of Truth Trust, 1962, orig. 1897), ገጽ 168

ይህንን የሁልጊዜ ምስክርነቴ ማድረግ እፈልጋለሁ፤ “የእኔ ለውጥ ሙሉ ከእግዚአብሔር ነው።”[25]

ስፐርጅን፣ በቤተ ክርስቲያን ብቁ አስተማሪ ለመሆን ቊልፉ እነዚህን የጸጋ አስተምህሮች መረዳት መሆኑን ዐላማ ያደረገ የመጋቢያን ኮሌጅ አስጀምሮ ነበር።

አርሚኖሳዊነት አስተምህሮችን የማምታታት ጥፋት ነው፤ ቅዱሳት መጻሕፍትንም በግልጽ ለመረዳት እንቅፋት ነው። ምክንያቱም የእግዚአብሔርን ዘላለማዊ ዕቅድ አሳስቶ ያቀርባል አሊያም ችላ ይላል፤ ጠቅላላውን የቤዝዎት ዕቅድ ትርጒም ያንሸዋርረዋል። ከዚህ መሠረታዊ እውነት [ከሁኔታ አልባ ምርጫ] ከተለዩ፣ ግራ መጋባት ፈጽሞ የማይቀር ነው።

ያለ እርሱ፣ የዐሳብ አንድነት ይጓደላል፤ እና በአጠቃላይ ስለ ሥነ መለኮት ደርዝ ምንም ዐሳቡ የላቸውም። ከዚህ [የምርጫ አስተምህሮ] እስካልጀመርክ፣ አንድን ሰው ሥነ መለኮተኛ[26] ማድረግ አትችልም።

አንድን አማኝ ወጣት በሥነ መለኮት ኮሌጅ ለዓመታት ማቆየት ትችል ይሆናል፤ ነገር ግን ይህን የዘላለማዊው ኪዳን መሠረታዊ ዕቅድ ካላሳየኸው፣ ጥቂት እርምጃ ብቻ ነው የሚጓዘው። ምክንያቱም ትምህርቶቹ አይጣጣሙለትም፤ አንዱ እውነት ከሌላው ጋር እንዴት እንደሚጋጠም እና ሁሉም እውነቶች እንዴት በጋራ እንደሚዋሓዱ አይመለከትም። ...

የትኛውንም የኢንግላንድ አገር ተመልከት፤ ከትምህርት ተቋማት እና ከኮሌጆች ከሚወጡት አንድ ሁለተኛ ይልቅ፣ የተሻለ የሥነ መለኮት ዕውቀት ያላቸውን ድኾች ሲያጥሩ እና ሲቈፍሩ ታገኛቸዋለህ። ምክንያቱም እኚህ ሰዎች በወጣትነት ዕድሜአቸው ሁኔታ አልባ ምርጫን ማዕከል ያደረገ የሥነ መለኮት ሥርዐት

[25] ዝኒ ከማሁ ፣ ገጽ 164-165
[26] Theologian

ተምረዋል። ከዚያም የሕይወት ልምምዳቸው ከትምህርቱ ጋር ተጣጥሞ አግኝተዋል።[27]

[27] Charles Spurgeon, "Effects of Sound Doctrine," sermon delivered on Sunday evening, April 22, 1860, at New Park Street Chapel.

# መውጫ

የእነዚህ አስተምህሮች ዘላለማዊ ደራሲ የሆነውን ድንቁን ክርስቶስ እንዲቀበል አንባቢውን በመጠየቅ፣ በጸጋ አስተምህሮች ላይ የተዘጋጀውን ይህን ዐጭር መጽሐፍ መቋጨት ተገቢ ነው። በዘመናችን የእነዚህ እውነቶች ታላቅ ጠበቃ የሆነው ጄ አይ ፓከር ላቀረበው ውብ ተማጽኖ ትኩረት ስጥ፤

"እድን ዘንድ ምን ላድርግ?" ለሚለው ጥያቄ አሮጌው ወንጌል [ካልቪኒዝም] እንዲህ ሲል ምላሽ ይሰጣል፣ "በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እመን።" በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ማመን ምን ማለት ነው? መልሱ ይህ ነው፤ የራስን ኀጢአተኝነት፣ ኢየሱስ ክርስቶስ ለኀጢአተኞች በመስቀል እንደሞተ መረዳት፣ የራስን ጽድቅና በራስ መተማመንን ሁሉ ማራገፍ እና ለይቅርታና ሰላም ራስን ሙሉ በሙሉ እርሱ ላይ መጣል ነው። በተጨማሪም በእግዚአብሔር ላይ ማመፅንና ተፈጥሯዊ ጠላትነትን፣ በቅዱስ መንፈስ ልቡናን በመታደስ፣ ለክርስቶስ ፈቃድ ፍጹም ታዛዥ በሆነ መንፈስ መለወጥ ነው።

ጥያቄዎቹን ስንቀጥል፣ "በተፈጥሮ የማመን ዝንባሌ ከሌለኝ፣ እንዴት በክርስቶስ ላምን እና ንስሓ ልገባ እችላለሁ?" ለሚለው ጥያቄ መልሱ፣ ሳታስመስል ወደ ክርስቶስ ተመልከት፤ ለእርሱ ተናገር፤ ወደ እርሱ ጩኽ፤ ኀጢአትህን፣ ትዕቢትህን፣ አለመታመንህን ፣ አለማመንህን ተናዘዝ፣ ራስህን በምሕረቱ ላይ ጣል፤ በውስጥህ እውነተኛ ንስሓ እና ጽኑ እምነት በመሥራት ዐዲስን ልብ እንዲሰጥህ ጠይቀው፤ ከእርሱ ሸሽተህ እንዳትሄድ፣ የማያምነውን ክፉ ልብ ከውስጥህ እንዲያስወጣ እና ሕጉን በልቡናህ እንዲቀርጽ ጠይቀው። ወደ እርሱ ዘወር በልና በተቻለህ ዐቅም ሁሉ በእርሱ ታመን፣ ይበልጥ ወደ እርሱ ዘወር እንድትልና ወደ እርሱ እንድትቀርብ ጸጋን ተማጸን። አንተ ወደ ክርስቶስ መቅረብ በምትፈልገው ልክ ወደ ራሱ ሲያቀርብህ፣ ክርስቶስን ለመመልከት የጸጋ መሣሪያዎችን ተጠቀም፤ ቃሉን ተመልከት፤ አንብብ፤ ጸልይ፤ የእግዚአብሔርን ቃል አድምጥ፤ አምልክ፤ ከቅዱሳን ጋር ኅብረት አድርግ። በውስጥህ ከጥርጣሬ

ነጻ ሆነህ የተቀየረ ሰው፣ እውነተኛ አማኝ እና የተለወጠ ልብ በአንተ ውስጥ መኖሩን እስከታውቅ ድረስ በእኚህ ሁሉ ጽና።[28]

ቻርለስ ስፐርጅንን በጸሎት ተከተል፤

በዚህ ሰዓት ከእኔ ጋር በጸሎት እንድትሳተፍ እጠይቅሃለው። ቃላትን በአንደበትህ ሳደርግ በመተባበር ከእኔ ቀጥለህ በላቸው፤ "ጌታ ሆይ እኔ ራሴን ማዳን የማልችል፣ የአንተ ቍጣ የሚገባኝ ኀጢአተኛ ነኝ። ጌታ ሆይ ራሴን ማዳን አልችልም። ዐዲስ ልብና እውነተኛ መንፈስ እንዲኖረኝ እሻለሁ፤ ግን ምን ማድረግ እችላለሁ? ጌታ ሆይ እኔ ምንም ማድረግ አልችልም፤ እንዳምንና በጎ የሆነው ፈቃድህን ማድረግ እንድችል መጥተህ በእኔ ሥራ።

እንደ እኔ ያለውን ጐስቋላ ለማዳን፣

ዐቅም ያለህ አንተ ብቻ እንደሆንህ ዐውቃለሁ፤

ከአንተ ዘንድ ርቄ፣

ወደማን ወይስ ወዴት እሄዳለሁ?

አሁን ግን እኔ ከልቤ ስምህን እጠራለሁ። በመንቀጥቀጥ፣ ግን በእምነት፣ ሙሉ በሙሉ ራሴን በአንተ ላይ እጥላለሁ። ጌታ ሆይ የውድ ልጅህን ደምና ጽድቅ እተማመናለሁ። ...ስለ ኢየሱስ ስትል ዛሬ አድነኝ።" [29]

---

[28] J. I. Packer, The Quest for Godliness (Wheaton: Crossway, 1994), ገጽ 144
[29] Quoted in Iain Murray, The Forgotten Spurgeon (Edinburgh: Banner of Truth Trust, 1973), ገጽ 101-102

# ዲዛየሪንግ ጋድ

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የቀረበውን የእግዚአብሔርን ዕቅድና ሕይወት በበለጠ ለመረዳት ከወደዱ፣ ዲዛየሪን ጋድ እርስዎን ሊያገለግል ይወዳል። ለኢየሱስ ክርስቶስ ባሎት ፍቅር እንዲበለጥጉ፣ ይህንን ፍቅር ለሌሎች እንዲያካፍሉ የሚያግዞ በሺዎች የሚቈጠሩ አጋዥ ሥራዎች አሉን። desiringGod.org ላይ ከስድሳ በላይ መጻሕፍትን ጨምሮ ጆን ፓይፐር የጻፈውንና ያስተማረውን ያገኛሉ። ከሠላሳ ዓመታት በላይ የጆን ፓይፐርን ስብከቶች እንዲያነብቡ፣ እንዲያደምጡ እና አውርደው እንዲጠቀሙ በነጻ እንዲያገኙ በኦንላይን ላይ አድርገናል።

ከዚህ በተጨማሪ በሙቶዎች የሚቈጠሩ መጣጥፎችን ማግኘት ይችላሉ። ይህ ብቻ ሳይሆን፣ ጆን ፓይፐር የት እንደሚሰብኩና ስለ ጉባኤዎቻችን ማወቅ ይችላሉ። ዲዛየሪንግ ጋድ ውስን ዐቅም ላላቸው ግለሰቦች “whatever-you-can-afford” የተሰኘ ፖሊሲ አለው። ስለዚህ ፖሊሲ የበለጠ መረጃ ለማግኘት ከወደዱ ከታች ባለው አድራሻና ስልክ ቊጥር ያግኙን። ዐላማችን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን እና ወንጌሉን ከሁሉ ይልቅ ሀብትዎ ማድረግ ይችሉ ዘንድ እርሶን ማገዝ ነው። ምክንያቱም እኛ በእርሱ ስንረካ፣ እርሱ በእኛ ይከብራል። እርሶን እንዴት ማገልገል እንደምንችል ያሳውቁን።

# ዲዛየሪንግ ጋድ

ፖ.ሣ.ቊ 2901 / ሚኒያፖሊስ ፣ ሚኖሶታ 55402

888.34604700 mail@desiringGod.org

# ክርስቲያን ፎከስ ፐብሊኬሽን

ተልእኮ

ታማኝነት

በእግዚአብሔር ላይ በመደገፍ፣ ፍጹም ለሆነው ቃሉ ታማኝ በሆኑ ሥነ ጽሑፎች ዓለም ላይ በጎ ተጽእኖ ማሳደር። ዐላማችን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለኀጢአት ይቅርታ፣ ረብ ላለው አኗኗር እና የሚመጣውን ዓለም አስቀድሞ ለመመልከት ብቸኛ ተስፋ ሆኖ መገለጹን ማረጋገጥ ነው።

መጻሕፍታችን በአራት ሕትመቶች ይታተማሉ

**CHRISTIAN FOCUS**

popular works including biographies, commentaries, basic doctrine and Christian living.

**CHRISTIAN HERITAGE**

books representing some of the best material from the rich herit-age of the church.

**MENTOR**

books written at a level suitable for Bible College and seminary students, pastors, and other serious readers. The imprint includes commentaries, doctrinal studies, examination of current issues and church history.

**CF4·K**

children's books for quality Bible teaching and for all age groups: Sunday school curriculum, puzzle and activity books; personal and fa ily devotional titles, biographies an inspirational stories – Because you are never too young to know Jesus

Christian Focus Publications Ltd,

Geanies House, Fearn, Ross-shire,

IV20 1TW, Scotland, United Kingdom.

www.christianfocus.com

blog.christianfocus.com



# JOHN PIPER

መጋቢ ዮሐንስ ፓይፐር (PHD) ለበርካታ ዓመታት የክርስቶስን ወንጌል በታማኝነት ያገለገሉ ተወዳጅ ሰባኪ ናቸው። ከሰብከት አገልግሎታቸው በተጨማሪ በጽሑፍ ሥራቸውም ይታወቃሉ። የጻፏቸው መጻሕፍት እና አጫጭር መጣጥፎች ለእግዚአብሔር እና ለቃሉ እንዲሁም ለእግዚአብሔር ሕዝብ ያላቸውን ጥልቅ ፍቅር ፍንትው አድርገው የሚያሳዩ ናቸው። ከጽሑፎቻቸው እና ከሰብከቶቻቸው ዘወትር የማይታጣ አባባላቸውም፦ " እኛ በእግዚአብሔር ይበልጡን ስንረካ፤ እግዚአብሔር በእኛ እጅግ ይከብራል።" የሚል ነው። ግንባር ቀደም ተጠቃሽ በሆነው መጽሐፋቸው 'Desiring God' በተሰየመ አገልግሎታቸውም በመላው ዓለም ብዙዎችን አንጸውበታል። በቤተልሔም ባፕቲስት ቤተክርስቲያን ከሠላሳ ዓመታት በላይ በመጋቢነት ያገለገሉ ሲሆን አሁን ከባለቤታቸው ኖኤል ጋር በምድረ አሜሪካ ይኖራሉ።

ESTM 223-76-49894-32-7

4 293142 1928462